
# ምዕራፍ ፡ ፲፪ ።

## ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ በስደት ፡ ስለመሄድ ፤

### ግርማዊና ፡ ግርማዊት ፤

### እስከ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ድረስ ፡ የተከተሉ ።

ልዑል መርዕድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፤
» መኰንን ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ መስፍን ፡ ሐረር ፡
» ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፤
ብፁዕ እጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡
ልዑል ራስ ፡ ካሣ ፡ ኃይሉ ፡
ክቡር ፊታውራሪ ፡ ብሩ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ (በኋላ ፡ ራስ) ፡
» ራስ ፡ ጌታቸው ፡ አባተ ፤ ከኢየሩሳሌም ፡ ከድተው ፡ ለጠላት ፡ ገቡና ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ተመለሱ ፤



ደጃዝማች ፡ ይገዙ ፡ በሀብቴ ፡

ክቡር ደጃዝማች ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፤ አባይነህ ፡
» ደጃዝማች ፡ ይገዙ ፡ በሀብቴ ፡
» ደጃዝማች ፡ አደፍርሰው ፡ ይናዱ ፡
» ደጃዝማች ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው ፡
» ደጃዝማች ፡ አምደ ፡ ሚካኤል ፡ ሀብተ ፡ ሥላሴ ፡



» ደጃዝማች ፡ አበበ ፡ ዳምጠው ፡ (ሚጀር ፡ ጀኔራል) ፡
» ደጃዝማች ፡ ሃብተ ፡ ሚካኤል ፡ ይናዱ ፤ ጂቡቲ ፡ ቆይተው ፡ ከጠላት ፡ ተላልከው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ገቡ ።
» ደጃዝማች ፡ ነሲቡ ፡ ዛማኑኤል ፤ ስዊስ ፡ ላይ ፡ ታመው ፡ ሞቱ ፡
ክቡር ደጃዝማች ፡ ወልደ ፡ አማኑኤል ፤ ጅቡቲ ፡ ቆይተው ፡ ከጠላት ፡ ተላልከው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ገብተው ፡ በጠላት ፡ ተገደሉ ።
ክቡር ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ ታመው ፡ ሞቱ ፡
ክቡር ጸሐፊ ፡ ትእዛዝ ፡ ኃይሌ ፡ ወልደ ፡ ሩፌ ፤
» አቶ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ወልደ ፡ ዮሐንስ ፡ (ጸሐፊ ፡ ትእዛዝ) ፡
» አቶ ፡ ሎሬንሶ ፡ ታዕዛዝ ፡



ቀኛዝማች ፡ ደገፋ ፡ በልሁ ፡

አቶ ፡ በሻህ ፡ ውረድ ፡ ሃብተ ፡ ወልድ ፡ በልጆቹ ፡ ምክንያት ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ተመልሶ ፡ በጠላት ፡ ተገደለ ፤
አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡ (አሁን ፡ ደጃዝማች) ፡
ቀኛዝማች ፡ በልሁ ፡ ደገፋ ፤ በመልእክት ፡ ወደ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ በጠላት ፡ ተይዞ ፡ ተገደለ ፤

ልጅ ፡ አርአያ ፡ አበበ ፡
ልጅ ፡ ታደለ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ከነራስ ፡ ጌታቸው ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ተመለሰ ፤
በጅሮንድ ፡ አባትሁን ፡ ወርቅነህ ፡
በጅሮንድ ፡ ረታ ፡ ገብረ ፡ አምላክ ፡
ልጅ ፡ አስፋው ፡ ከበደ ፡
ልጅ ፡ ታምራት ፡ ይገዙ ፡

## በሴቶች ፡ በኩል ፡ የተሰደዱት ።

ልዕልት ተናኘ ፡ ወርቅ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፤
ልዕልት ወለተ ፡ እሥራኤል ፡ ሥዩም ፡ ከአባታቸው ፡ ጋራ ፡ ተላልከው ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ተመልሰዋል ፤
ልዕልት የሻሸ ፡ ወርቅ ፡ ይልማ ፡
ልዕልት ፀሐይ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፤
ወይዘሮ ጽጌ ፡ በሻህ ፤ የልዑል ፡ ራስ ፡ ካሣ ፡ ባለቤት ፡
ወይዘሮ ብዙነሽ ፡ ካሣ ፡
ወይዘሮ ከበደች ፡ ሥዩም ፤ በአርበኝነት ፡ ቆይተው ፡ በሱዳን ፡ በኩል ፡ አቋርጠው ፡ ከግብጽ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጡ ።
ልዕልት አይዳ ፡ ደስታ ፡
እመቤት ሂሩት ፡ ደስታ ፡
እመቤት ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ደስታ
ልዕልት እጅጋየሁ ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡
እመቤት ሶፍያ ፡ ደስታ ፡
ወይዘሮ ወሰንየለሽ ፡ መንገሻ ፤ የደጃዝማች ፡ አበበ ፡ ዳምጠው ፡ ባለቤት ፡
ወይዘሮ ሙሉመቤት ፡ አበበ ፡
ወይዘሪት ፡ እምዩ ፡ አበበ ፡ (በኋላ ፡ ልዕልት ፡ መደፈሪያሽ ፡ ወርቅ ፡ አበበ) ፤
ወይዘሪት ፡ እክለወግ ፡ አበበ ፡
ወይዘሪት ፡ ፍቅርተ ፡ ብሩ ፡
ወይዘሮ ጽጌ ፡ ገብረ ፡ ሩፋኤል ፡ የራስ ፡ እምሩ ፡ ባለቤት ፡
ወይዘሮ የምሥራች ፡ እምሩ ፡
ወይዘሪት ፡ ማርታ ፡ እምሩ ፡
» ዮዲት ፡ እምሩ ፡
» ሂሩት ፡ እምሩ ፡
» እሌኒ ፡ እምሩ ፡
» ቱቱ ፡ እምሩ ፡
» ዓለም ፡ ሰገድ ፡ ፈቃደ ፡ ሥላሴ ፡



ወይዘሮ ቀለመ ፡ ወርቅ ፡ ጥሩነህ ፤ ከአሩሲ ፡ በኬንያ ፡ በኩል ፡ መጥተው ፡ ከባላቸው ፡ ከደጃዝማች ፡ አምደ ፡ ሚካኤል ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተገናኙ ፤
ወይዘሪት ፡ ምህረት ፡ ጳውሎስ ፡ በኋላ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ መጥታ ፡ እንደገና ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በመዘዋወር ፡ ቆየች ፤

## በትምህርት ፡ ላይ ፡ የነበሩ ።

ልጅ አሥራት ፡ ካሣ ፡
» አምሐ ፡ ደስታ ፡
» ዘውዴ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡ እናቱ ፡ ልዕልት ፡ ወለተ ፡ እሥራኤል ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ሲመለሱ ፡ አብሮ ፡ ተመልሷል ።
» አምሐ ፡ አበራ ፡
» ሚካኤል ፡ እምሩ ፡
» ታሪኩ ፡ አበራ ፡
» እስክንድር ፡ ደስታ ፡
» ክፍሌ ፡ አደፍርሰው ፡
» ኃይሉ ፡ ደስታ ፡
» ኃይሉ ፡ ጎሩይ ፡

በየጊዜው ፡ እየተሰደዱ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በግብጽ ፡ ከስደተኛው ፡ የተቀላቀሉ ።

ፊታውራሪ ፡ ተሰማ ፡ ባንቴ ፡ ግብፅ ፡ ላይ ፡ በስደት ፡ እንዳሉ ፡ ሞቱ ፤
ፊታውራሪ ፡ በዕደ ፡ ገብሬ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ በስደት ፡ እንዳሉ ፡ ሞቱ ፤
ቀኛዝማች ፡ ሙሉጌታ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በስደት ፡ እንዳሉ ፡ ሞቱ ፡
አቶ ፡ ዓለሙ ፡ ቸኮል ፡ ፓሪስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ለጋሲዮን ፡ ጸሐፊ ፡ ነበር ፤ በኋላ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጥቶ ፡ ከስደተኞቹ ፡ ጋራ ፡ በአገልግሎት ፡ ቆየ ፤

ፊታውራሪ ፡ ታፈሰ ፡ ሃብተ ፡ ሚካኤል ፡ ካይሮ ፤ ኢየሩሳሌም ፡ ፓሪስ ፡ ሎንዶን ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ቆዩ ፤

ልጅ ፡ መንበረ ፡ ያየህይራድ ፤ በኢየሩሳሌም ፡ በካይሮ ፡ እየተመላለሱ ፡ የቆዩ

ልጅ ፡ ተድላ ፡ ታምራት ፤ ለሕክምና ፡ ሶርያ ፡ ሄዶ ፡ እዚያው ፡ እንዳለ ፡ ሞተ ፤

አቶ ፡ በፈቃደ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፤ ለጠላት ፡ ገብቶ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ተመለሰ ፡

አቶ ፡ ማርቆስ ፡ ጳውሎስ ፤ የኢየሩሳሌም ፡ ቆንስላ ፡ ጸሐፊ ፡ ለጠላት ፡ ገብቶ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ተመለሰ ፤

ልጅ ፡ ለገሥ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ ከእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ታሞ ፡ ሞተ ፡ ልጅ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡ ግዛው ፡ (ብሪጋዲዬር ፡ ጄኔራል) ፡ ከጅቡቲ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጥቶ ፡ በአገልግሎት ፡ ላይ ፡ ቆይቶ ፡ በኋላም ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ ጋራ ፡ በወታደራዊ ፡ አገልግሎት ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ መጣ ።

## አለመተባበር ፡ የሚያስከትለውን ፡ ጉዳት ፡ ለማስረዳት ።

እያለፍኩ ፡ የመጣሁትን ፡ ይህን ፡ የታሪክ ፡ ማስታወሻ ፡ ስጽፍ ፡ ወገን ፡ የሚነካ ፡ የሚያሰቅቅና ፡ የሚያሳፍርም ፡ መሆኑን ፡ አንዳንዶችም ፡ የወገኖቻቸው ፡ ስም ፡ የተጠቀሰባቸው ፡ ሰዎች ፡ ቅር ፡ እንደሚላቸውና ፡ ጠቅላላ ፡ ጦሩ ፡ ድል ፡ የሆነበትን ፡ ምክንያት ፡ በመግለጹ ፡ ጸሐፊውን ፡ ሳይወቅሱትና ፡ ሳያዝኑበት ፡ እንደማይቀሩ ፡ አምናለሁ ።

ነገር ፡ ግን ፡ እውነቱን ፡ ተናግሮ ፡ በመሸበት ፡ ያድሯል ፡ እንደሚባለው ፡ ሁሉ ፡ በእኔ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ስሜት ፡ ድል ፡ የሆንበት ፡ ታውቆ ፡ ለወደፊቱ ፡ እንዲታሰብበት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከአቅማችን ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ በቦንብ ፡ የጭስ ፡ መርዝ ፡ የተጠቃን ፡ መሆኑ ፡ ሳልዘነጋ ፡ ጠላት ፡ አስቀድሞ ፡ መተባበር ፡ እንዲጠፋና ፡ የአንድነት ፡ ኃይል ፡ እንዲቀነስ ፡ አድርጎ ፡ እንደነበረ ፡ ለማሳሰብ ፡ ስል ፡ የጻፍኩት ፡ ማስረጃ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አገርና ፡ ወገንን ፡ ለመንቀፍ ፡ የጻፍኩት ፡ አይደለም ።

ለማስረጃ ፡ ያህል ፡ የምገልጸው ፡ በቦንብ ፡ መሣሪያነትና ፡ የጭስ ፡ መርዝን ፡ በመጣል ፡ መሣሪያ ፡ አድርጎ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ጠላታችን ፡ ያጠቃበት ፡ መሣሪያ ፡ መሆኑ ፡ የሚካድ ፡ አይደለም ። ነገር ፡ ግን ፡ ጥቃቱና ፡ ውርደቱ ፡ ተሰምቶት ፡ ከልቡ ፡ አስቦ ፡ ለአገሩና ፡ ለነፃነቱ ፡ እያለ ፡ የሚከላከል ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ብዙውን ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ እላይ ፡ እስከ ፡ ጠቀስኩት ፡ መሣሪያው ፡ ጥቂቶች ፡ ነፃነትና ፡ የሀገር ፡ ፍቅር ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ክብር ፡ ያዘዛቸው ፡ አርበኞች ፡ ድል ፡ እያደረጉ ፡ መድረሻ ፡ ያሳጡት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ግልጥ ፡ ብሎ ፡ ታይቷል ። ይህ ፡ የመተባበር ፡ መንፈስ ፡ በመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ጠላት ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ያገኘው ፡ ድልና ፡ አገር ፡ መያዝ ፡ ባልተቻለም ፡ ነበር ።

ስለዚህ ፡ በላይኛው ፡ መስመር ፡ እንዳስረዳሁት ፡ አለመተባበር ፡ በባዕድ ፡ ስብከት ፡ መታለልና ፡ ለወሬ ፡ አለመመከት ፡ መሠረት ፡ ለሌለው ፡ ለጊዜው ፡ ማባበያና ፡ ማታለያ ፡ ለሚደረገው ፡ ገንዘብ ፡ መኳኳት ፡ የሚያስከትለውን ፡ ለማስረዳትና ፡ ያለፈው ፡ ለሚመጣው ፡ ትምህርት ፡ ሆኖ ፡ እንዲጠበቅ ፡ ለማስታወሻ ፡ እንዲሆን ፡ ነው ።

አሁንም ፡ ደግሜ ፡ የማስረዳው ፡ ወገንን ፡ ለመንቀፍ ፡ የጻፍኩት ፡ አለመሆኑን ፡ ነው ፡ ከነቀፋው ፡ የማልለይ ፡ አንዱ ፡ ተነቃፊ ፡ መሆኔንም ፡



አምናለሁ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በሽታው ፡ ካልታወቀ ፡ መድኃኒቱ ፡ አይገኝለትም ፡ እንደሚባለው ፡ ሁሉ ፡ ምክንያቱ ፡ ከታወቀ ፡ ሁሉም ፡ ያስብበታል ፡ በማለት ፡ ነው ። እውነቱ ፡ ተገልጾ ፡ መድኃኒቱ ፡ ተገኝቶለት ፡ የሚድነው ፡ በሽታ ፡ በይሉኝታ ፡ ፍርሐት ፡ ተጋርዶ ፡ ብንደብቀው ፡ በሽታው ፡ አመርቅዞ ፡ የሚጎዳን ፡ እኛኑ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ታማሚ ፡ አይፈልግምና ፡ አንዱን ፡ ሰው ፡ ጎድቶ ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ ለመጥቀም ፡ ሳይሆን ፡ የመተሳሰብና ፡ የመተባበር ፡ አንድነት ፡ ጥቅሙ ፡ ራስን ፡ በራስ ፡ ለመርዳት ፡ ስለሆነ ፡ እንደ ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ ሰምቶ ፡ የሚታለፍ ፡ አይደለምና ፡ አጥብቆ ፡ የሚታሰብበት ፡ መሆኑን ፡ አለመዘንጋት ፡ ነው ።

እኔም ፡ ይህችን ፡ የታሪክ ፡ ማስታወሻ ፡ ልጽፍ ፡ ያሰብሁት ፡ ፈሪ ፡ የያዘውን ፡ ከወረወረ ፡ ፈሪ ፡ አያስኘውም ፡ እንደሚባለው ፡ ሁሉ ፡ ለእኔም ፡ የተሰማኝና ፡ በሕሊናዬ ፡ ውስጥ ፡ የሚጉላላውን ፡ ለወገን ፡ ለማካፈል ፡ ስለሆነ ፡ ለአንባቢ ፡ ቢያጠግበውም ፡ ባያጠግበውም ፡ ሕሊናዬ ፡ እንዳይወቅሰኝ ፡ ከኔ ፡ ወጣልኝ ። እንግዲህ ፡ ማመዛዘን ፡ ያንባቢው ፡ ፈንታ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

## በስደት ፡ ዘመን ፡ በኢየሩሳሌም ።

በ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ኢጣሊያ ፡ በግፍ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በወረረችበት ፡ ዘመን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በዘመቱበት ፡ በዋናው ፡ የጦር ፡ ግንባር ፡ ዘምቼ ፡ የጦር ፡ ኃይል ፡ በቦምብ ፡ በጢስ ፡ ጋዝና ፡ መርዝ ፡ ተጠቅቶ ፡ መመለስ ፡ ግድ ፡ ሆኖበት ፡ ሲመለስ ፤ ይህንኑ ፡ የጭካኔ ፡ ሥራ ፡ ለዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ለማመልከት ፡



በስደት ፡ ዘመን ፡ በኢየሩሳሌም ።

ወደ ፡ አውሮፓ ፡ሲሰደዱ ፡ ግርማዊነታቸውን ፡ ተከትዬ ፡ እስከ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ድረስ ፡ ሔጄ ፡ ነበረ ፤ ኢየሩሳሌምንም ፡ ያስተዳድሩ ፡ የነበሩት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የጊዜውን ፡ ፖለቲካ ፡ በመመልከት ፡ ለጠላታችን ፡ ረዳት ፡ ሆነው ፡ ይሠሩብን ፡ የነበረውን ፡ በጥቂቱ ፡ ልገልጸው ፡ እወዳለሁ ።



## በኢየሩሳሌም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ገዳም ፡ ንብረት ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ ደረሰው ፡ ችግር ፡

የመንግሥታችን ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ የነበሩት ፡ ሁሉ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሳይስለ ፡ ነበሩ ፤ እነሱን ፡ አስጨንቆ ፡ ከጠላት ፡ እየታረቁ ፡ እንዲገቡና ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የተሰደዱበትን ፡ ዓላማ ፡ ለማሳሳት ፡ በማሰብ ፡ ብዙ ፡ የማንገራበድና ፡ የማስፈራራት ፡ ሥራ ፡ ይሠሩ ፡ ነበር ። እንደዚሁም ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከተመለስንም ፡ በኋላ ፡ በጉዞም ፡ ላይ ፡ ሆነ ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ አንዳንድ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነገሮች ፡ ሳይገጥሙን ፡ አልቀሩም ፤ ለማስረጃ ፡ ያህል ፡ ጥቂቶቹን ፡ ነገሮች ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በሚገኘው ፡ መስመር ፡ እገልጻለሁ ።

በኢየሩሳሌም ፡ ያለውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ገዳም ፡ ጠላት ፡ እጅ ፡ ለማድረግ ፡ አስቦ ፡ በገዳሙ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ መነኮሳቶች ፡ በገንዘብ ፡ እያታለለ ፡ ጥቂቶችን ፡ የኤርትራ ፡ ተወላጆች ፡ የሆኑ ፡ መነኮሳቶች ፡ ወገን ፡ አድርጎ ፡ የገዳሙን፡ ፡ ዶኪማ ፡ ለማስወሰድ ፡ ቁልፍ ፡ ያዥ ፡ የነበሩትን ፡ አባ ፡ ዓለሙ ፡ የተባሉትን ፡ መነኩሴ ፡ በመጠጥ ፡ አስክሮ ፡ ለማታለል ፡ ወገን ፡ ባደረጋቸው ፡ መነኮሳት ፡ አማካይነት ፡ ሥራውን ፡ ጀመረ ። በመጠጥ ፡ ኃይል ፡ ሊያታልላቸው ፡ የተሞከሩት ፡ መነኩሴ ፡ የሰውነታቸውን ፡ መሸነፍ ፡ ሲገምቱ ፡ ዶኪማ ፡ ያለበትን ፡ ሳጥን ፡ ወስደው ፡ ለመምህሩ ፡ አስረከቡና ፡ ለጠላት ፡ የተሰበኩትንም ፡ መነኮሳቶች ፡ ሐሳባቸው ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ዘርዝረው ፡ ነገሩዋቸው ።

መምህሩም ፡ ይህንኑ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላሉ ፡ ስደተኞች ፡ ነገሩና ፡ በምክርና ፡ በማንኛውም ፡ ሐሳብ ፡ እንዲረዱዋቸው ፡ ጠየቁ ።

በብፁዕ ፡ እጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስና ፡ በደጃዝማች ፡ ይገዙ ፡ በሀብቱ ፡ ሰብሳቢነት ፡ አንድነት ፡ ተሰብስበው ፡ ፩ መክሩና ፡ ከመንግሥቱ ፡ ባለሥልጣን ፡ አንድ ፡ ዳኛ ፡ ተቀብለው ፡ ዶኪማ ፡ የሚገኝበት ፡ የገዳሙ ፡ ዕቃ ፡ ቤት ፡ እንዲታሸግና ፡ እንዲጠበቅ ፡ በማለት ፡ ስላማከሩዋቸው ፡ ከፓሊስታይን ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የታዘዘ ፡ አንድ ፡ የሐሳም ፡ አለቃ ፡ ፖሊስ ፡ ጋራ ፡ ከስደተኞችም ፡ አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡ አቶ ፡ ዓለሙ ፡ ቸኮል ፡ በጅሮንድ ፡ ረታ ፡ በጅሮንድ ፡ አባተሁን ፡ ከመምህሩ ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ እንዲያሽጉ ፡ ነገሯቸውና ፡ ለማሸግ ፡ ሄዱ ። በሚታሸግበትም ፡

፩ ከመኳንንቶቹ ፡ ፊታውራሪ ፡ ብሩ ፡ ደጃዝማች ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ አባይነህ ፡ ደጃዝማች ፡ እንዳልካቸው ፡ ደጃዝማች ፡ አምዴ ፡ ሚካኤል ፡ ደጃዝማች ፡ አበበ ፡ ዳምጠው ፡ ደጃዝማች ፡ አደፍርሰው ፡ ጸሐፊ ፡ ትእዛዝ ፡ ኃይሉ ፡ ወልደ ፡ ሩፊ ፡ በስብሰባው ፡ ላይ ፡ ነበሩ ።



ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡




ደጃዝማች ፡ ይገዙ ፡ በሀብቱ ።






ደጃዝማች ፡ ብሩ ፡ ወልደ ፡ ገብ
ርኤል ፡ (ራስ) ፡



ደጃማች ፡ አደፍርሰው ፡ (ራስ) ፡



ደጃዝማች ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ አባይነህ ፡



አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡





በጅሮንድ ፡ አባትሁን ፡ ወርቅነህ ።



በጅሮንድ ፡ ረታ ፡ ገብረ ፡ አምላክ ፡ (ፊታውራሪ) ፡

ጊዜ ፡ ለጊዜው ፡ ከመምህሩ ፡ በታች ፡ ሆኖ ፡ ሥራውን ፡ ይመራ ፡ የነበረ ፡ መጋቢ ፡ አባ ፡ ስብሐት ፡ ለአብ ፡ የሚባለው ፡ መነኩሴ ፡ ስለነበረ ፡ እንዳይ ታሸግ ፡ ለማድረግ ፡ እየተቅበጠበጠ ፡ አስቸግሮ ፡ ስለነበረ ፡ የማሸጉም ፡ ሥራ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ መምህሩ ፡ መምህር ፡ ክፍለ ፡ ገሪማ ፡ ለዕለት ፡ ገንዘብ ፡ መታለል ፡ የማይገባ ፡ መሆኑን ፡ መክረው ፡ አሁንም ፡ በጠላት ፡



አቶ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡ ግዛው ፡
(ብ/ጄኔራል) ።

ስብከት ፡ ተታሎ ፡ ለጠላት ፡ ያመነ ፡ ቢኖር ፡ እንዲመለስ ፤ ወደፊትም ፡ እንዳይሳሳት ፡ ገዘቻለሁ ፡ ብለው ፡ በሥልጣናቸው ፡ ሲያስሩ ፡ አባስብ ሐት ፡ ለአብ ፡ የተባለው ፡ መነኩሴ ፡ እኔም ፡ የመምህር ፡ ክፍለ ፡ ገሪማን ፡ ሐሳብ ፡ የተከተለ ፡ ገዝቻለሁ ፡ አለና ፡ ቀሚሱንም ፡ በእጁ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ ያዘና ፡ ወደ ፡ ኢጣሊያ ፡ ቆንስል ፡ እሄዳለሁ ፡ እናንተን ፡ አላ

---

፩ ልጅ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡ ግዛው ፡ ቀድሞ ፡ የቤቱ ፡ መንግሥት ፡ መኪና ፡ አውቶመቢል ፡ ነጅ ፡ ነበር ። በኋላ ፡ በስደት ፡ በጅቡቲ ፡ በኩል ፡ ወደኢየሩሳሌም ፡ መጥቶ ፡ በቆየበት ፡ ጊዜ ፡ ወደጠላት ፡ ከገቡት ፡ ውስጥ ፡ አባ ፡ ስብሐት ፡ ለአብ ፡ የተባለውን ፡ መነኩሴ ፡ በቆንስሉ ፡ ነው ፡ እናንተን ፡ አላውቅም ፡ በማለት ፡ ወደጠላት ፡ በሮጠበት ፡ ጊዜ ፡ ተከታትሎ ፡ ሲሮጥ ፡ እግሩን ፡ ጠልፎ ፡ ሲወድቅ ፡ ይዞ ፡ ከፖሊሱ ፡ ጋር ፡ ያመጣ ፡ ባለሙያ ፡ ነው ።



ውቅም ፡ ብሎ ፡ ሩጫውን ፡ ቀጠለ ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አቶ ፡ ኃይለማርያም ፡ ግዛው ፡ አሁን ፡ ብ/ጄኔራል ፡ በሩጫ ፡ ተከታትሎ ፡ ያዘውና ፡ ከፖሊሱ ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ አምጥተው ፡ ለመምህሩ ፡ አስረከቡ ፤ መምህሩም ፡ ይህ ንኑ ፡ ከዓተኛ ፡ መነኩሴና ፡ ተከታዮች ፡ የሆኑትን ፡ ሁለት ፡ መነኮሳት ፡ ጭምር ፡ እንዲታሠሩ ፡ አደረጉ ።

## የኢትዮጵያን ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፤ ከገዳሙ ፡ ላይ ፡ ለማውረድ ፡ የፖሊስ ፡ ኃይል ፡ ስለመላኩ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የማባበሉና ፡ የማታለሉ ፡ ገመድ ፡ ተበጥሶ ፡ ቁርጠኛ ፡ ጠብ ፡ ተጀመረ ። ጠላትም ፡ ከሀገሩ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ጋራ ፡ በመስማማት ፡ የኃይልና ፡ የግፍ ፡ አጥቂነት ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ጀመረ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ (ባንዲራ) ፡ ከቆንስላው ፡ እንዲወርድ ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ ስደተኛውም ፡ ሆነ ፡ መነኮሳቱ ፡ በተስፋ ፡ የሚመለከተው ፡ በገዳሙ ፡ ላይ ፡ የተሰቀለውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ባንዲራ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በመጀመሪያ ፡ የፖለስታይን ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የኢትዮጵያ ፡ (ባንዲራ) ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ በገዳሙም ፡ ላይ ፡ እንዳይታይ ፡ አውርዱ ፡ ሲሉ ፡ የእንግሊዝ ፡ ሹማምንቶች ፡ ለመምህሩ ፡ ትእዛዝ ፡ አስተላለፉ ። በጊዜው ፡ ላይ ፡ የነበሩት ፡ መምህር ፡ ክፍለ ፡ ገሪማ ብጹዕና ፡ ቆራጥነትም ፡ የነበራቸው ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ እኔ ፡ ነፃነቴ ፡ መኖሩን ፡ ስለማምን ፡ የነፃነት ፡ ምልክት ፡ የሆነ ውን ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ እንዲወገድ ፡ ማድረግ ፡ አልችልም ፡ ብለው ፡ መልስ ፡ ቢሰጡት ፡ በማስፈራራት ፡ እንዲያወርዱ ፡ የሚያስገድድ ፡ የፖሊስ ፡ ኃይል ፡ ተላከ ። የፖሊሱም ፡ ባለሥልጣን ፡ ሽጉጡን ፡ መዞ ፡ አሁንም ፡ አውርዱ ፡ ሲል ፡ በማስገደድ ፡ አዘዘ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ቁርጠኛው ፡ መነኩሴ ፡ ለማንገራበድ ፡ ለተመዘዘውም ፡ ሽጉጥ ፡ ሆነ ፡ በንግግሩም ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ሳይሸበሩና ፡ ሳይደነግጡ ፡ በኔ ፡ በኩል ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማው ፡ መኖር ፡ አለበት ፡ ብያለሁ ። እናንተ፡ ግን ፡ በኃይላችሁ ፡ የፈቀዳችሁትን ፡ አድርጋችሁ ፡ የነፃነታችንን ፡ ምል ክት ፡ የሰንደቅ ፡ ዓላማውን ፡ ጨርቅ ፡ ብታነሱትም ፡ በልባችን ፡ ውስጥ ፡ ነፃነታችን ፡ እርግጠኛ ፡ ሆኖ ፡ እንዳለ ፡ እናምናለን ። እናንተም ፡ አሁን ፡ ጊዜ ፡ አዝዛችሁ ፡ እንዳይታይ ፡ ከተሰቀለበት ፡ ብታወርዱት ፡ ደግሞ ፡ ጊዜው ፡ ሲያዛችሁ ፡ ልትሰቅሉት ፡ ትደክማላችሁ ፤ ስለዚህ ፡ ጠላታ

ችንም ፡ ሆነ ፡ ወዳጃችን ፡ ጊዜው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ አለመሆኑን ፡ ስለተረዳን ፡ ሳንበሳጭና ፡ ሳናማርረው ፡ በደስታ ፡ እንቀበለዋለን ፡ ሲሉ ፡ ለነፃነታቸው ፡ ሙሉ ፡ ተስፋ ፡ ያላቸው ፡ መሆኑን ፡ የሚያስረዳ ፡ መልስ ፡ ሰጡ ።



መምህር ፡ ገሪማ ፡ (ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ሚካኤል) ።

መልክተኛውም ፡ የፖሊስ ፡ ሹም ፡ ትእዛዙን ፡ መፈጸም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የማሻሻያ ፡ ሥልጣን ፡ የሌለው ፡ ስለሆነ ፡ ሽጉጡን ፡ እንደመዘዘ ፡ ዛሬ ፡ ጎን ፡ ለጎን ፡ ሆነው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ የሰቀሉትን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ የጊዜው ፡ መልክተኛ ፡ በነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ ከተሰቀለበት ፡ አወረዱት ። የቆራጡ ፡ መነኩሴ ፡ የመምህር ፡ ክፍለ ፡ ገሪማ ፡ ትንቢትም ፡ ሳይዘገይ ፡ በቶሎ ፡ በመፈጸሙ ፡ ተአምኖቱን ፡ ሳያወላውል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ የጣለ ፡ ሁሉ ፡ በተስፋ ፡ የሚጠብቀውን ፡ ነፃነት ፡ በርሱው ፡ ዕድሜ ፡ ለማየት ፡ ቻለ ።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ በገዳሙ ፡ ላይ ፡ የተሠራውን ፡ የግፍ ፡ ሥራ ፡ ጽፌ ፡ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ወደ ፡ ሎንደን ፡ ልኬ ፡ ነበር ። ከግርማዊነታቸውም ፡ የተጻፈልኝ ፡ መልስ ፡ በሃይማኖትና ፡ በተስፋ ፡ ለምንጠባበቀው ፡ ለሕሊናችን ፡ መጽናኛ ፡ ሆኖ ፡ ያቆየንን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ጽፌዋለሁ ።





ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ።

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡

ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡፡

ይድረስ ፡ ከባሻ ፡ ከበደ ፡

እንደምን ፡ ሰንብተሃል ፡ እኛ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን፡ ደህናነን ፡፡
በጥር ፡ ወር ፡ የጻፍከውን ፡ ደብዳቤ ፡ ተመለከትነው ፡ በሚቻልህ ፡ ሁሉ ፡ እንደዚሁ ፡ ብትጽፍልኝ ፡ በጣም ፡ የሚጠቅም ፡ ነገር ፡ ይገኝበታል ፤ በገዳሙ ፡ ላይ ፡ የሚሠራውን ፡ ግፍ ፡ አይቼ ፡ እጅግ ፡ አዘንኩ ፤ ምላሹም ፡ የዘገየው ፡ ምናልባት ፡ ተስፋ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ለመላክ ፡ ብለን ፡ በምኞታችን ፡ ተስፋ ፡ ስላልቆረጥን ፡ ነው ፡ በገዳሙ ፡ ላይ ፡ የሚሰቀለው ፡ ባንዲራ ፡ የሚያጎዳቸው ፡ ሆኖ ፡ አይደለም ፤ እንደዚህ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ አኳኋን ፡ ሲታይ ፡ የስደተኞቹና ፡ የገዳሙ ፡ አኳኋን ፡ እየታሰበኝ ፡ በጣም ፡ አዝናለሁ ፤ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ከሌለ ፡ ምን ፡ መከራ ፡ ይባላል ፤ በኢየሩሳሌም ፡ ስላለው ፡ ዕቃ ፡ ማቆያ ፡ በአባ ፡ ሐና ፡ በኩል ፡ ስለላክኸው ፡ ወዲያው ፡ መልሼ ፡ ማዘጋጀውን ፡ ጭምር ፡ ልኬ ፡ ነበር ፤ እንደምን ፡ እስካሁን ፡ ሳይደርስ ፡ ቀረ ፤ ስለ ፡ ገዳሙ ፡ ዕቃ ፡ ማቆያውን ፡ ቦታ ፡ ለሚቀበለው ፡ ሰው ፡ ለዚህ ፡ ዝርዝሩን ፡ ገልጠህ ፡ ጻፍልኝ ፡፡

ጥር ፡ ፲፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡

## ገዳሙን ፡ በጠላት ፡ እጅ ፡ ለማግባት ፡ ሙከራ ፡ ስለመደረጉ ፡

ይህ ፡ ሁሉ ፡ በኃይል ፡ የማንገራበድ ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ የሰንደቅ ፡ ዓላማውም ፡ እንዳይታይ ፡ መከልከል ፡ በልብ ፡ ውስጥ ፡ እንደእሳት ፡ የሚነደውን ፡ የነፃነት ፡ መንፈስ ፡ ሊያስወግደው ፡ ባለመቻሉ ፡ ጠላት ፡ ያቀደው ፡ የፖለቲካ ፡ ትግል ፡ ሁሉ ፡ ስለተበላሸበት ፡ መነኮሳቱን ፡ ገዳሙ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ስለሚሆን ፡ እናንተም ፡ ለኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ መታዘዝ ፡ አለባችሁ ፡ ብሎ ፡ የፓለስታይን ፡ መንግሥት ፡ እንዲያስገድድለት ፡ ለመነ ፡፡ የጊዜው ፡ መላክተኛ ፡ የፓለስታይን ፡ ገዥም፡ መምህሩን ፡ አቢሮው ፡ ድረስ ፡ ጠርቶ ፡ ራስ ፡ በመሳም ፡ የተላከውን ፡ መልእክት ፡ ለማድረስ ፡ በመቆጣትና ፡ በማስፈራራት ፡ ከኢጣልያ ፡ ቆንስል ፡ ሥር ፡ እንዲሆን ፡ ነገራቸው ፡፡ አሁንም ፡ ቆራጡ ፡ መነኩሴ ፡ የያዙትን ፡ መሥረት ፡ ሳይለቁ ፡ ከጠላት ፡ መስማማት ፡ የማይቻል ፡ መሆኑን ፡ ገልጠው ፡ በመንገር ፡ የሚገባ ፡ መልስ ፡ ስለሰጡት ፡ ሲገቡ ፡ በማስፈራራትና ፡ በንቀት ፡ ሀይን ፡ እየተመለከተ ፡ ከመቀመጫው ፡ ንቅንቅ ፡



ሳይል ፡ እየተቆጣ ፡ የተቀበላቸውን ፡ መነኩሴ ፡ ንግግራቸውን ፡ ጨርሰው ፡ በሚሄዱበት ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ መሆናቸውን ፡ ከተረዳ ፡ በኋላ ፡ ከመቀመጫው ፡ ተነስቶ ፡ እስከበር ፡ ውጭ ፡ እመኪናቸው ፡ እስኪወጡ ፡ ድረስ ፡ ሸኝቶ ፡ ተመለሰ ፡፡

ሁለተኛ ፡ በሌላ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ጠላት ፡ ተስብከው ፡ የገዳሙን ፡ ሥርዓት ፡ ያበላሹትን ፡ መነኮሳት ፡ ከገዳሙ ፡ ቢያስወጡ ፤ አታስወጡ ፡ ይግቡ ፡ ሲል ፡ በማስገደድ ፡ እንዲያስገባ ፡ አሁንም ፡ የፓለስታይን ፡ ፖሊስ ፡ ኃይል ፡ ታዝዞ ፡ መጣና ፡ አስገቡ ፡ አለ ፤ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ መምህሩ ፡ ከነማኅበሩ ፡ እናስገባም ፡ ሲሉ ፡ ተከላከሉ ፤ በብዙ ፡ ዓይነት ፡ ለማስገባት ፡ ቢፈትንም ፡ የማይቻል ፡ ሆነ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የወጡት ፡ ይሁን ፡ አይግቡ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እውስጥ ፡ ያሉትን ፡ እንዳታስወጡ ፡ ሲል ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጥቶ ፡ ሄደ ፡፡

ከዚህ ፡ ትእዛዝ ፡ በኋላ ፡ እውስጥ ፡ ያሉትና ፡ እውጭ ፡ ያሉት ፡ መነኖች ፡ በመችገራቸው ፡ እየተደበቁ ፡ ወጥተው ፡ ተጓደኞቻቸው ፡ ተገናኝተን ፡ እንመለሳለን ፡ እያሉ ፡ ሲወጡ ፡ ተአምኖቱን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ያደረገው ፡ የገዳሙ ፡ ማኅበር ፡ እኛ ፡ በግድ ፡ ውጡ ፡ አንበላችሁ ፡ እንጂ ፡ በፈቃዳችሁ ፡ ከወጡ ፡ እንመለስ ፡ ቢሉ ፡ አናስገባም ፡ እያሉ ፡ የወጡትን ፡ ከለከሏቸው ፡፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የጊዜ ፡ መላክተኛ ፡ ለሆነው ፡ ባለሥልጣን ፡ እየሄዱ ፡ አታስወጡ ፡ ካሉዋቸው ፡ በኋላ ፡ ከለከሉን ፡ እያሉ ፡ አቤቱታ ፡ ቢያቀርቡለት ፡ አርፋችሁ ፡ እዚያው ፡ እቦታችሁ ፡ መቀመጥ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ አላርፍ ፡ ብላችሁ ፡ ከወጣችሁ ፡ አስገቡ ፡ ብሎ ፡ ማዘዝ ፡ አይቻልም ፡ ወጊዱ ፡ እያለ ፡ ያባርራቸው ፡ ጀመር ፡ እንጂ ፡ እንደፈተኛው ፡ ሊረዳቸው ፡ አልቻለም ፤

## ወደጠላት ፡ በተሰበኩት ፡ መነኮሳት ፡ ስለደረሰ፡ ችግር ፡

የዚህ ፡ የማስገባትና ፡ የማስወጣት ፡ ክርክር ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ካረፈ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ድንገተኛ ፡ ፈተና ፡ ደረሰ ፡፡ ይኸውም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፈው ፡ ነው ፤ ወደ ፡ ጠላት ፡ ከተሰበኩት ፡ መነኮሳት ፡ ውስጥ ፡ እንዲቱ ፡ መነኩሲት ፡ በድንገት ፡ ታማ ፡ ስለሞተች ፡ ለፍትሐት ፡ ሬሳዋ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ቅጽር ፡ ግቢ ፡ እንዲገባ ፡ ጓደኞቿ ፡ ቢጠይቁ ፡ መምህሩ ፡ በግዝት ፡ የታሰረች ፡ ስለሆነ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሬሳዋ ፡ ገብቶ ፡ ፍትሐት ፡ ሊደረግ ፡ አይችልም ፡ ሲሉ ፡ ከለከሉ ፡፡

እንደ ፡ ልማዱ ፡ በኢጣሊያ ፡ ቆንስል ፡ አማካይነት ፡ የእንግሊዝ የፖሊስ ፡ ሹማምንቶች ፡ ከአገረ ፡ ገዢው ፡ ታዘልና ፡ እቤተ፡ ክርስቲያን፡ ሬሳዋ ፡ ገብቶ ፡ የፍትሐት ፡ ጸሎት ፡ እንዲደረግ ፡ ሲሉ ፡ አዘዙ ፡፡

መምህሩም ፡ ይህ ፡ ጉዳይ ፡ የሃይማኖት ፡ ነክ ፡ ስለሆነ ፡ የሥጋዊ ፡ አስተዳደር ፡ ገዢዎች ፡ ሊያዙበት ፡ አይችልም ፤ በውግዘት ፡ የተለየ ፡ ሰው ፡ ቢሞት ፡ እሬሳው ፡ እቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገብቶ ፡ እንዲፈታ ፡ የሃይማኖት ፡ ሥርዓታችን ፡ አይፈቅድም ፡ ሲሉ ፡ በማስረዳት ፡ ከለከሉ ፤ ባለሥልጣኖቹም ፡ በማንገራበድ ፡ አስፈራርቶ ፡ ለማስገባት ፡ ሞከሩ ። ነገር ፡ ግን ፡ በዚያ ፡ የሚገኙ ፡ መነኰሳትና ፡ ምዕመናኑም ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ለመከላከል ፡ የተዘጋጁ ፡ መሆናቸውን ፡ ስለ ፡ ተመለከተ ፡ ተልኰ ፡ የመጣው ፡ የፖሊስ ፡ ሹም ፡ ለላከው ፡ ያየውን ፡ ሂዶ ፡ ስለተናገረ ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ውዝግብ ፡ ውግዘቱ ፡ የደረሰበት ፡ሬሳ ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ካለፈው ፡ በኋላ ፡ የበላይ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገብቶ ፡ ለማስፈታት ፡ ካልተቻለ ፡ ሬሳው ፡ በጽዳት ፡ ሠራተኞች ፡ ተወስዶ ፡ በይሁዳ ፡ ገንዘብ ፡ ተገዛ ፡ እሚባለው ፡ ለእንግዳ ፡ መቃብር ፡ በተዘጋጀው ፡ ሥፍራ ፡ ሂዶ ፡ ይቀበር ፡ ተብሎ ፡ አዘዘና ፡ በ፫ኛው ፡ ቀን ፡ ሂዶ ፡ ተቀበረ ፤ የሀገሩም ፡ ባለሥልጣን ፡ ነገሩ ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ የጠነከረ ፡ መሆኑን ፡ ከተመለከተ ፡ በኋላ ፡ ለጠላት ፡ ያደርገው ፡ የነበረውን ፡ ዕርዳታ ፡ አቋርጦ ፡ ነገራችሁ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ይፈጸም ፡ እንጂ ፡ የአገረ ፡ ገዢ ፡ ሥልጣን ፡ በትእዛዝ ፡ ሊጨርሰው ፡ አልሆነም ፡ ብሎ ፡ አሰናበተ ።



ሚስተር ፡ ናታን ፡ ማሬን ።



ልዑል ፡ ራስ ፡ ካሳ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ ካሣ ፡ ኃይሉ ፡ ከለንደን ፡ ወደኢየሩሳሌም ፡ መጥተው ፡ ስለነበረ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ገዳም ፡ ጉዳይ ፡ በየጊዜው ፡ ከስደተኛው ፡ ማኅበር ፡ ጋር ፡ በስብሰባው ፡ ላይ ፡ ባይገኙም ፡ ጉዳዩ ፡



የሚመለከታቸውን ፡ መምሕሩንም ፡ ሆነ ፡ ሌሎችን ፡ ሰዎች ፡ እየጠሩ ፡ በማነጋገርና ፡ ምክርም ፡ ሀሳብም ፡ በመስጠት የጉዳዩ ፡ ተካፋይ ፡ እንደመሆናቸው ፡ መጠን ፡ ጠበቃውን ፡ ምስተር ፡ ናታን ማሬንም ፡ ሕግን ፡ ስለሚመለከተው ፡ ጉዳይ በየጊዜው ፡ እያስጠሩ ፡ በማነጋገር ፡ ሀሳብም ፡ ምክርም ፡ ይሰጡ ፡ ነበር ።

## የገዳሙ ፡ ነገር ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ መቅረቡ ።

ነገሩ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እመራና ፡ የኢጣሊያ ፡ ቆንስል ፡ ከሳሽ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ገዳም ፡ መምህር ፡ ተከሳሽ ፡ ሆነው ፡ በየጠበቃቸው ፡ ክርክራቸውን ፡ ቀጠሉ ። የገዳሙ ፡ ጉዳይ ፡ እስከዚህ ፡ ከደረሰ ፡ በኋላ ፡ በስደተኞች ፡ ላይ ፡ አዲስ ፡ ፈተና ፡ ተጀመረ ።

ለፈተናውም ፡ መነሻ ፡ የሆነው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ግርማዊት ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ምኒልክ ፡ ያሠሩት ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ቤት ፡ ነው ፤ ይህም ፡ ቤት ፡ ቀድሞ ፡ እንደተሠራ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በሚቀመጠው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቆንስል ፡ ጠባቂነት ፡ እየተሠራ ፡ ከገቢው ፡ ላይ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለሚኖሩ ፡ መናንያኖችና ፡ ምዕመናኖች ፡ መርጃ ፡ ተብሎ ፡ ይሰጥ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ከቆንስሉ ፡ ጠባቂነት ፡ ተዛውሮ ፡ ከገቢው ፡ የመናንያኖች ፡ ድርሻ ፡ እንዳለ ፡ ሆኖ ፡ የሚተርፈው ፡ ለስደተኞች ፡ መርጃ ፡ እንዲሆን ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ተፈቅዶና ፡ ታዞ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ያለው ፡ የስደተኞች ፡ ወኪል ፡ እንዲረከብ ፡ ተደረገ ፤ የቆንሲሉ ፡ ሥልጣን ፡ በዚህ ፡ ቤት ፡ የጥበቃ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ታግዶ ፡ በደጃዝማች ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው ፡ የበላይ ፡ ተጠባባቂነት ፡ እኔ ፡ ቤቱን ፡ ተረከብኩ ፡ በስደተኞች ፡ ስም ፡ እንድሠራ ፡ ታዘዝኩና ፡ ቤቱን ፡ ከተከራዮች ፡ የኰንትራት ፡ ውል ፡ ጋራ ፡ ተረከብኩ ፡ መሥራት ፡ እንደጀመርሁ ፡ ጠላታችን ፡ ኢጣልያ ፡ ሐሳቡ ፡ ስደተኞቹ ፡ ለኑሮዋቸው ፡ መረጃ ፡ የሚሆን ፡ ጥቅም ፡ ሲያጡና ፡ ሲቸገሩ ፡ እየታረቁኝ ፡ ወደ ፡ ሀገራቸው ፡ ይመለሳሉ ፡ ማለትን ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ የኢጣልያ ፡ ቆንስል ፡ ይህ ፡ ቤት ፡ ለስደተኞች ፡ መርጃ ፡ እንዲሆን ፡ ታስቦ ፡ የተሰጠውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ቤት ፡ ነውና ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የሆነው ፡ የኢጣልያ ፡ ንጉሥ ፡ ስለሆነ ፡ ይህን ፡ ቤት ፡ እንድረከብ ፡ ይታዘዝልኝ ፡ ሲል ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ በገዳሙ ፡ ላይ ፡ አልሞ ፡ የከሸፈበትን ፡ ሐሳብ ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ አዞሮ ፡ አንቀሳቀሰው ፡

እንዱን ፡ አስከፍቶ ፡ እንዱን ፡ ማስደሰት ፡ የፖለቲካ ፡ ጥቅም ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የያዘው ፡ ያገሩም ፡ ባለሥልጣን ፡ ቀድሞ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቆንስል ፡ ሆኖ ፡ ሲሠራ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የኢጣሊያ ፡ ንጉሥ ፡ መሆኑን ፡ ስለ ፡ አወቀ ፡ የኢትዮጵያ ፡

ልዩ ፡ ቆንስል ፡ በኢየሩሳሌም ፡ እንዲኖር ፡ አላስፈለገምና ፡ ቢሮው ፡ ይዘጋ ። ስንደቅ ፡ ዓላማውም ፡ እንዳይሰቀል ፡ ብሎ ፡ የከለከለውን ፡ ቆንስል ፡ የነበረውን ፡ አቶ ፡ ዓለሙ ፡ ቸኰልን ፡ ጠርቶ ፡ ይህ ፡ ቤት ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ስለሆነ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በኢጣልያ ፡ መንግሥት ፡ ሥር ፡ መሆኑን ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ስላወቀለት ፡ ቤቱን ፡ ለኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ቆንስል ፡ አስረክብ ፡ ሲል ፡ ጠርቶ ፡ በቃል ፡ አዘዘ ።



አቶ ፡ ዓለሙ ፡ ቸኰል ፡

አቶ ፡ ዓለሙ ፡ ቸኰልም ፡ ትእዛዙን ፡ ተቀብለው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩትን ፡ ስደተኞች ፡ ሰብስበው ፡ ከእንግሊዝ ፡ ባለሥልጣን ፡ የተነገራቸውን ፡ የትእዛዝ ፡ ቃል ፡ ካስረዱ ፡ በኋላ ፡ ቤቱን ፡ እንዳስረክብ ፡ እንድታዘዝ ፡ አስታወቁ ። ስደተኞቹም፡ ከፍ፡ ያለ ፡ ሐዘን፡ ቢሰማቸውም ፡ የሚከላከሉበትን ፡ ዘዴ ፡ ለጊዜው ፡ ሊያገኙለት ፡ ሊያስቡም ፡ አልቻሉም ፡



ነበርና ፡ የቤቱ ፡ ጠባቂ ፡ የነበርሁት ፡ ታምሜ ፡ ስለነበረ ፡ በስብሰባው ፡ ላይ ፡ ባለመገኘቴ ፡ ከስደተኛው ፡ ማኅበር ፡ ዘንድ ፡ ደጃዝማች ፡ አበበ ፡ ዳምጠው ፡ ተልከው ፡ መጡና ፡ ከዚያ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ ዶኪሜንትና ፡ ዕቃዎች ፡ አብረው ፡ ከቤቱ ፡ ጋራ ፡ እንዳይያዙ ፡ በቶሎ ፡ ይውጣ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ነገሩኝ ። እኔም ፡ ይህን ፡ ከማድረጌ ፡ በፊት ፡ ሕመሜ ፡ ጥቂት ፡ ተሽሎኛልና ፡ እዚያው ፡ መጥቼ ፡ እነጋገርበታለሁ ፡ ስል ፡ መልስ ፡ ሰጠሁና ፡ ለመሄድ ፡ ስዘጋጅ ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ደጃዝማች ፡ አደፍርስ ፡ ተልከው ፡ መጥተው ፡ ያንኑ ፡ የፊተኛውን ፡ ቃል ፡ ነገሩኝ ።



ልጅ ፡ ታምራት ፡ ይገዙ ።

እኔም ፡ አሁን ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ለመፈጸም ፡ አልችልም ፡ ምክንያቱም ፡ እውስጡ ፡ ከሚገኙት ፡ ዶኪማና ፡ ዕቃዎች ፡ የቤቱ ፡ መሄድና ፡ የፖለቲካችን ፡ መበላሸት ፡ ከፍ ፡ የሚል ፡ ስለሆነ ፡ ዕቃ ፡ አሽሽቶን ፡ የማስረክብ ፡ መልክ ፡ ከማሳየታችን ፡ በፊት ፡ ከጠበቃችን ፡ ምክር ፡ መጠየቅ ፡ ያስፈልገናል ፡ ይህ ፡ ሳይደረግ ፡ አንድም ፡ ነገር ፡ መሥራት ፡ አልችልም ፡ ለማንኛውም ፡ እኔ ፡ እዚያ ፡ እስብሰባው ፡ ቦታ ፡ ድረስ ፡ እመጣለሁ ፡ ብዬ ፡ መልስ ፡ ሰጠሁና ፡ ሄዱ ።

እኔም ፡ ወዲያው ፡ ተከታትዬ ፡ ሄድኩና ፡ የስደተኛው ፡ ማኅበር ፡ ተሰብስቦ ፡ እሚነጋገርበት ፡ ቦታ ፡ ደረስኩና ፡ እላይ ፡ እንዳመለከትኩት ፡ አሁንም ፡ ቢሆን ፡ ለጠበቃ ፡ ነግረን ፡ ጠበቃችን ፡ የሚመክረንን ፡ ሐሳብ ፡

ብንከተል ፡ ይሻላል ። እስከዚያ ፡ በእኛ ፡ በኩል ፡ ዕቃ ፡ የማሸሽና ፡ የማስረከብ ፡ መንፈስ ፡ ማሳየት ፡ አይገባንም ፡ ስል ፡ አስረዳሁ ። ጉባኤውም ፡ በሐሳቡ ፡ ስለ ፡ ተስማማ ፡ ደጃዝማች ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው ፡ አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡ ልጅ ፡ ታምራት ፡ ይገዙ ፡ ሄደው ፡ ጠበቃውን ፡ እንዲጠይቁ ፡ ተወሰነ ። ጠበቃውም ፡ እንዲጠየቅ ፡ የተወሰኑት ፡ ቃሎች ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፉት ፡ ናቸው ።

፩ኛ/ ቤቱን ፡ አስረክቡ ፡ በመባል ፡ የተላለፈልንን ፡ ትእዛዝ ፡ መቃወም ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ የሚያስከትልብን ፡ መሆን ፡ አለመሆኑን ፤
፪ኛ/ የቤቱ ፡ ዶኪማ ፡ ለክርክር ፡ የሚያበቃን ፡ የሚያዘልቅ ፡ መሆን ፡ አለመሆኑን ፤
፫ኛ/ ክርክር ፡ ቀጥለን ፡ ሳንረታ ፡ ብንቀር ፡ ኪሣራ ፡ መክፈል ፡ መኖር ፡ አለመኖሩን ፤
፬ኛ/ ኪሣራ ፡ መክፈል ፡ ኖሮ ፡ ለመክፈል ፡ ያልቻልን ፡ እንደሆነ ፡ ምን ፡ ያስከትላል ።

እነዚህን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፉትን ፡ ፬ት ፡ ጥያቄዎች ፡ ምስተር ፡ ናታን ፡ ማሬን ፡ ለተባሉት ፡ እሥራኤላዊ ፡ ጠበቃችን ፡ አቅርበን ፡ ጠየቅናቸው ። ከርሳቸው ፡ ያገኘነው ፡ መልስ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፈው ፡ ነው ።

ለ፩ኛ ፡ ጥያቄ ፡ መልስ ፤ ያንዱን ፡ ሰው ፡ መብት ፡ ማንኛውም ፡ ባለሥልጣን ፡ ያለፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ ምንም ፡ ለማድረግ ፡ ሕግ ፡ አይፈቅድምና ፡ መብታችንን ፡ ያለፍርድ ፡ አንለቅም ፡ ብትሉ ፡ ምንም ፡ የሚያሰጋችሁ ፡ ነገር ፡ የለም ።

ለ፪ኛ ፡ ጥያቄ ፡ መልስ ፤ ለመከራከሪያ ፡ የቀረበው ፡ ዶኪማ ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ እንረታበታለን ፡ ባንልም ፡ ጊዜ ፡ ለማስረዘም ፡ ይቻላልና ፡ እንዲያው ፡ ከመልቀቅ ፡ በዚሁ ፡ ክርክሩን ፡ መቀጠል ፡ ይጠቅማል ።

ለ፫ኛ ፡ ጥያቄ ፡ መልስ ፤ ሳንረታ ፡ ብንቀር ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፈል ፡ መጠየቁ ፡ አይቀርም ። ነገር ፡ ግን ፡ ኪሣራውን ፡ መክፈል ፡ ያልቻልን ፡ እንደሆነ ፡ በወኪሉ ፡ ላይ ፡ የእሥራት ፡ ፍርድ ፡ ይፈጸምበታል ። ሲሉ ፡ ለጥያቄዎቻችን ፡ መልስ ፡ ሰጡን ።

እኛም ፡ ይህንኑ ፡ ቃል ፡ ለስደተኛው ፡ ማኅበር ፡ ካስረዳን ፡ በኋላ ፡ የስደተኛው ፡ ማኅበር ፡ ከጥያቄዎቹ ፡ መልስ ፡ ሁሉ ፡ ኪሣራ ፡ መክፈል ፡ ያልቻለ ፡ እንደሆነ ፡ በወኪሉ ፡ ላይ ፡ እሥራት ፡ ይፈጸምበታል ፡ የተባለው፡ ከባድ ፡ መስሎ ፡ ታያቸውና ፡ በነገሩ ፡ ይግፋበት ፡ ለማለት ፡ ተቸገሩ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ወኪሉ ፡ እኔ ፡ ስለነበርኩ ፡ ነገሩ ፡ ፍሬ ፡ አጥቶ ፡ የእሥራት ፡ ፍርድ ፡ ቢፈረድም ፡ እኔ ፡ እቀበለዋለሁና ፡ አሁን ፡ ገና ፡ ይህ ፡ ይደርሳል ፡ በሚል ፡ ስጋት ፡ ያለክርክር ፡ መብታችንን ፡ እንልቀቅ ፡ ብዬ ፡ ስለገለጽኩ ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ክርክሩ ፡ እንዲገፋበት ፡ ተወሰነ ። ነገራችንን ፡ ያለፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ አንለቅም ፡ በማለት ፡ ላይ ፡ አርፎ ፡ ጉዳያችንን ፡ በሕግ ፡ መንገድ ፡ ለመፈጸም ፡ ብንዘጋጅም ፡ ጠላታችን ፡ የጊዜ




ውን ፡ የፖለቲካ ፡ ሁኔታ ፡ ረዳት ፡ አድርጎ ፡ ካገሩ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በመስማማት ፡ ጉዳዩ ፡ በትእዛዝ ፡ ብቻ ፡ እንዲፈጸም ፡ አሰበና ፡ የከተማው ፡ ሹም ፡ ሚስተር ፡ ማንቱራ ፡ የሚባለው ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ አገረ ፡ ገዢ ፡ ታዝዣለሁ ፡ ብሎ ፡ ከኢጣሊያን ፡ ቆንስል ፡ ጋራ ፡ ቤቱ ፡ እስከሚገኝበት ፡ ቦታ ፡ ድረስ ፡ መጥቶ ፡ ቁልፍ ፡ ያዡውን ፡ ብቻ ፡ ፈልጎ ፡ ለማስረከብ ፡ ተከራዮች ፡ ባሉበት ፡ ክፍል ፡ እየገባ ፡ ቁልፍ ፡ ያዡ ፡ ማነው ፡ የት ፡ ይገኛል ፡ እያለ ፡ ጠየቀና ፡ የቁልፍ ፡ ያዡውን ፡ መኖሪያ ፡ ክፍል ፡ ሲያሳዩት ፡ በቀጥታ ፡ ወደዚያ ፡ ክፍል ፡ ሄደና ፡ ተጣራ ።

በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ቁልፍ ፡ ያዡው ፡ አልተገኘም ፡ ሚስቱ ፡ ግን ፡ ነበረችና ፡ ጥሪውን ፡ ሰምታ ፡ ብቅ ፡ አለች ። ቁልፍ ፡ ያዡው ፡ የት ፡ ሄደ ፡ ብሎ ፡ ጠየቃት ፤ እሷም ፡ በፈቃድ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ሄደ ፡ ብላ ፡ መለሰችለት ፤ ባለሥልጣኑም ፡ ቁልፉን ፡ አምጭና ፡ ቤቱን ፡ ክፈች ፡ አላት ። ሴቲቱም ፡ ወይዘሮ ፡ በቀለች ፡ የአቶ ፡ ኪዳን ፡ ማርያም ፡ ባለቤት ፡ ለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ወንዶቹን ፡ ፈልገው ፡ ይነጋገሩ ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ አላውቅም ፡ አለችው ፡ ቆመው ፡ ሲነታረኩ ፡ እኔና ፡ ልጅ ፡ ታምራት ፡ ይርሰን ፡ ስለነበረ ፡ ራቅ ፡ ብለን ፡ ስናዳምጥ ፤ የቤቱ ፡ ኃላፊ ፡ እኔ ፡ ባቅራቢያው ፡ መገኘቴን ፡ ሚስተር ፡ ማንቱራ ፡ ተጠቁሞ ፡ ኖሮ ፡ ከሴቲቱ ፡ ጋራ ፡ ያለውን ፡ ንትርክ ፡ አቋረጠና ፡ እኛ ፡ ወዳለንበት ፡ መጣ ፤

እኛም ፡ አመጣጡን ፡ አይተን ፡ ወደሱ ፡ ሄድን ። በመሐል ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ስንገናኝ ፡ አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡ ማለት ፡ አንተ ፡ ነህን ፡ ሲል ፡ ጠየቀ ፤ እኔም ፡ አዎ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ አልኩት ። ከዚህ ፡ ጥያቄው ፡ በኋላ ፡ ይህ ፡ ቤት ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ቤት ፡ ስለሆነ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ሀብት ፡ የኢጣሊያ ፡ ንጉሥ ፡ መሆኑን ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ስላወቀለት ፡ ቤቱን ፡ ለኢጣሊያ ፡ ቆንስል ፡ እንዳስረክብ፡ ከአገረ፡ ገዢው ፡ ታዝዤ ፡ መጥቻለሁና ፡ አስረክብ ፡ ሲል ፡ አዘዘ ። እኔም ፡ አሁን ፡ የሚነግሩኝ ፡ እመንገድ ፡ ላይ ፡ ባጋጣሚና ፡ በቃልም ፡ ስለሆነ ፡ ይህ ፡ ቤት ፡ ትንሽ ፡ ነገር ፡ አይደለምና ፡ ማን ፡ ነገረኝ ፡ ማንስ ፡ አዘዘኝ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ የማስረክበው ፡ ስለዚህ ፡ ይህንኑ ፡ የቃል ፡ ትእዛዝዎ ፡ በጽሑፍ ፡ አድርገው ፡ ቢያዙኝ ፡ ደስ ፡ ባለኝ ፡ ነበር ፤ አሁን ፡ ግን ፡ እመንገድ ፡ ላይ ፡ በቃል ፡ ብቻ ፡ ነግረውኝ ፡ ለማስረከብ፡ አልችልም ፡ ስል፡ መልስ፡ ሰጠሁ።

ባለሥልጣኑም ፡ እኔ ፡ ራሴ ፡ መጥቼ ፡ ሳዝህ ፡ እንዴት ፡ በጽሑፍ ፡ ልታዘዝ ፡ ትላለህ ፡ ሲል ፡ እየጮኸ ፡ በመናገር ፡ ተቆጣና ፡ አሁንም ፡ ሂድ ፡ አስረክብ ፡ አለና ፡ አዘዘ ። መከራ ፡ ያደነዘዘውም ፡ ስደተኛ ፡ የሱን ፡ ጩኸትና ፡ ቁጣ ፡ ሳይሰጋ ፡ እርስዎን ፡ ማን ፡ እንደሆኑ ፡ አላውቅዎትምና ፡ የተገናኘነውም ፡ ድንገት ፡ እመንገድ ፡ ላይ ፡ ስለሆነ ፡ እኔ ፡ ይህን ፡ የቃል ፡ ትእዛዝ ፡ ተቀብዬ ፡ አላስረክብም ፤ እርስዎ ፡ ግን ፡ ባለሥልጣን ፡ ከሆኑ ፡ እኔን ፡ በሥልጣንዎ ፡ ከዚህ ፡ ቦታ ፡ አስወግደው ፡ የፈቃድዎን ፡ ማድረግ ፡ ይችላሉ ፡ ስል ፡ መልስ ፡ ስለሰጠሁ ፡ ባለሥልጣኑ ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ትእዛ

ሁን ፡ እቋረጠና ፡ እዚያው ፡ እመንገድ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ አሰበና ፡ አሁን ፡ ያለንበት ፡ ቦታ ፡ ፀሐይ ፡ ስለሆነ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ገብተን ፡ እንነጋገር ፡ ሲል ፡ ጠየቀ ። እኔም ፡ ለፀሐይ ፡ መጠለያ ፡ ብቻ ፡ የሚጠቅም ፡ መተላለፊያ ፡ እሆን ፡ ቦታ ፡ አስገባሁት ፤ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የኢጣሊያ ፡ ቆንስል ፡ አብሮት ፡ እንዳይገባ ፡ እውጭ ፡ በር ፡ ላይ ፡ አስከለከልሁት ። እውስጥ ፡ እንደገባን ፡ በእጁ ፡ አንድ ፡ የጽሑፍ ፡ ማስታወሻ ፡ ይዞ ፡ ስለነበረ ፡ ጻጻፈና ፡ የፈለግኸው ፡ በጽሕፈት ፡ መታዘዝን ፡ ስለሆነ ፤ ይኸው ፡ ጽፌልሃለሁና ፡ አስረክብ ፡ ሲል ፡ በብጣሽ ፡ ወረቀት ፡ የጻፈውን ፡ ሰጠኝ ። እኔም ፡ ጽሑፉን ፡ ተቀበልሁና ፡ ልጅ ፡ ታምራት ፡ በቃል ፡ ለማስተርጎም ፡ እንጂ ፡ የጽሑፉን ፡ መተርጎም ፡ ስለ ፡ ማይችል ፡ አማርኛ ፡ የሚያውቁ ፡ ቄስ ፡ ማቲው ፡ የተባሉ ፡ እንግሊዝ ፡ አሉና ፡ እሳቸውን ፡ ልጥራና ፡ ይተርጉሙና ፡ ያስረዱኝ ፡ ብዬ ፡ ጠየቅሁና ፡ ፈቀደልኝ ። ቄስ ፡



ቄስ ፡ ማቲው ።

ቄስ ፡ ማቲው ፡ ጠላት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ከመውረሩ ፡ በፊት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ይኖሩ ፡ የነበሩና ፡ ጠላት ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ያስወጣቸው ፡ እንግሊዛዊ ፡ ቄስ ፡ ናቸው ። ቀድሞ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የእንግሊዝ ፡ ሚኒስትር ፡ የነበሩት ፡ እነ ፡ ሰር ፡ ባርተን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ስደተኞች ፡ ለመርዳት ፡ አንድ ፡ ማኅበር ፡ ሎንዶን ፡ ላይ ፡ ባቋቋሙ ፡ ጊዜ ፡ ቄስ ፡ ማቲው ፡ የማኅበሩ ፡ አባል ፡ ሆነው ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምና ፡ ወደ ፡ ካይሮ ፡ እየተዘዋወሩ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ስደተኞች ፡ ይረዱ ፡ ነበር ። ጠላት ፡ ተባሮ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አንደ ፡ ጥንቱ ፡ በተቋቋመች ፡ ጊዜም ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተመልሰው ፡ መጥተው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በአፄ ፡ ንጉሥ ፡ ነሲቡ ፡ ሠፈር ፡ በንግሥት ፡ ኤልሳቤጥ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ የእንግሊዝን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሠርተው ፡ ያቋቋሙ ፡ ናቸው ። ቄስ ፡ ማቲው ፡ የካቲት ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፲፰፻፸፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተወለዱ ። በ፹፯ ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ ጥር ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፭ ፡ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሞተው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ጉለሌ ፡ ላይ ፡ ተቀበሩ ።



ማቲውም ፡ መጡ ፡ ጽሕፈቱን ፡ አዩና ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አላዘዘ ፡ በምን ፡ ሥልጣን ፡ ነው ፡ ይህን ፡ ትእዛዝ ፡ የጻፍከው ፡ ሲሉ ፡ ጠየቁት ። ሚስተር ፡ ማንቴራ ፡ ቤቱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ቤት ፡ ስለሆነና ፡ የኢጣሊያ ፡ ንጉሥ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መሆኑን ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ስላወቀለት ፡ ከአገረ ፡ ገዢው ፡ እንዳስረክብ ፡ ታዝዣለሁ ፡ አለ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ይረዱኛል ፡ ብዬ ፡ የጠራኋቸው ፡ ቄስ ፡ ማቲው ፡ ከአገረ ፡ ገዢው ፡ ታዝዣለሁ ፡ካለ ፡ ምን ፡ ታደርጋለህ ፡ አስረክብ ፡ እንጂ ፡ አሉኝ። እኔም ፡ ጽሑፉን ፡ ይገቡ ፡ ሳመንታ ፡ ረቂቅ ፡ አስቀርቼ ፡ ልስጥህ ፡ አልና ፡ ጽሑፉን ፡ ተቀበለኝና ፡ ገልብጦ ፡ ሲጨርስ ፡ እንግዲህ ፡ ይህን ፡ ጽሑፍ ፡ የምስጥህ ፡ አሁኑኑ ፡ ታስረክብ ፡ እንደሆን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ጠየቀኝ ። እኔም ፡ ነገሩን ፡ ቀርቀብ ፡ አደረግሁ ፡ አሰብሁና ፡ ከእኔ ፡ በላይ ፡ የሆኑ ፡ ደጃዝማች ፡ መኰንን ፡ ያሉት ፡ ኢያሪኮ ፡ ስለሆነ ፡ ጽሑፉን ፡ ወስጄ ፡ ካሳየኋቸው ፡ በኋላ ፡ እንደዚሁም ፡ ከሌሎች ፡ የሥራ ፡ ጓደኞቼ ፡ ጋራ ፡ ከተነጋገርን ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ የማስረክበው ፡ እንጂ ፡ አሁን ፡ ማስረከብ ፡ አልችልም ፡ አልኩት ። ቅድሙንም ፡ ጽሕፈቱን ፡ ከእጁ ፡ በተቀበለኝ ፡ ጊዜ ፡ ለማፈ ግፈግ ፡ መሆኑ ፡ ታውቋልና ፡ እንግዲህ ፡ አንተ ፡ በፍጹም ፡ እንቢተኛ ፡ ስለሆንክ ፡ ለአገረ ፡ ገዢው ፡ ሬፖርት ፡ እጽፋለሁ ፡ እስከዚያ ፡ በቤቱ ፡ ዙሪያ ፡ ፖሊሶች ፡ ቆመው ፡ እንዲጠብቁ ፡ አለና ፡ የሚገባና ፡ የሚወጣውን ፡ የማይከላከሉ ፡ ምንም ፡ የማይሠሩ ፡ በማንገራብድ ፡ ለማስፈራራት ፡ ብቻ ፡ ፲ ያህል ፡ ፖሊሶች ፡ በቤቱ ፡ ዙሪያ ፡ አቆመና ፡ ሄደ ።

እኔና ፡ ልጅ ፡ ታምራትም ፡ ወደሌላ ፡ ሳንሄድ ፡ ቀኑ ፡ ቅዳሜ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ጠበቃችን ፡ እሥራኤላዊ ፡ ስለነበረ ፡ ቢሮው ፡ ዝግ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሄድን ፡ ጠበቃችንም ፡ ወደ ፡ ቴልአቪብ ፡ ሄዶ ፡ ኖሮ ፡ እሱን ፡ አጣነውና ፡ ሚስቱን ፡ አገኘንና ፡ የመጣንበትን ፡ ምክንያት ፡ ነገርናት ። እሷም ፡ አለማስረከባችሁ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ሆኗል ፡ አሁን ፡ እኔ ፡ ሄጄ ፡ ሚስተር ፡ ናታን ፡ ማሬንን ፡ እጠራዋለሁ ፡ እስከዚያ ፡ እንዲሁ ፡ ጠብቁ ፡ ስላለችን ፡ ተመልሰን ፡ ሄደን ፤ የቤቱን ፡ የመጨረሻ ፡ ሁናቴ ፡ ስንጠባበቅ ፡ ቆየንና ፡ እንደገና ፡ በ፲ ፡ ሰዓት ፡ ወደ ፡ ሚስተር ፡ ናታን ፡ ማሬን ፡ ቤት ፡ ልንሄድ ፡ ስንነሳ ፡ ከባለቤቱ ፡ ጋራ ፡ አለንበት ፡ ድረስ ፡ መጡ ።

እኛም ፡ በዝርዝር ፡ ነገሩ ፡ የደረሰበትን ፡ አስረዳነው ። እሱም ፡ አለማስረከባችሁ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ነው ፡ የሆነው ፤ አስረክባችሁ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ በፍጹም ፡ መበላሸቱ ፡ ነበር ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ፖሊሶቹም ፡ እንዲነሱ ፡ አደርጋለሁ ። ነገራችንም ፡ ያለ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ ያገረ ፡ ገዢዎች ፡ ሥልጣን ፡ እንዲታገድ ፡ ለጠቅላይ ፡ ገዢው ፡ አቤቱታ ፡ አቀርባለሁ ፡ ሲል ፡ ተስፋ ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ነገረን ።

## በጠበቃችን ፡ አመልካችነት ፡ ፖሊስ ፡ ስለመወገዱ ።

ወዲያው ፡ ለፖሊሱ ፡ አዛዥ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሳያዝ ፡ ያንዱን ፡ ሰው ፡ መብት ፡ መያዝ ፡ ከሕግ ፡ ውጭ ፡ ስለሆነ ፡ እስከ ፳፬ ፡ ሰዓት ፡ ፖሊሶቹ ፡ ከዚያ ፡ ቦታ ፡ ካልተወገዱ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ማመልከት ፡ ግድ ፡ ይሆንብኛል ፡ ሲል ፡ ጻፈለት ።

የፖሊሱም ፡ አዛዥ ፡ ለጠበቃው ፡ መልሱን ፡ በ፳፬ ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ ፖሊሶች ፡ እዚያ ፡ ቦታ ፡ የሉም ፡ ሲል ፡ ጻፈለት ፤ ሁለተኛም ፡ ያለ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ የፓለስታይን ፡ የከተማ ፡ ሹማምንቶች ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሚገኙትን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ስደተኞች ፡ ልብ ፡ እንዲወርዳቸው ፡ በመጨቆን ፡ መብታቸውን ፡ እንዲያጡ ፡ ያስገድዷቸዋል ። ስለዚህ ፡ ከስደተኞቹ ፡ መብት ፡ ላይ ፡ ይገባኛል ፡ የሚል ፡ ቢኖር ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ እየከሰሰ ፡ ሲረታ ፡ እንዲወስድ ፡ እንጂ ፡ እንዲያው ፡ ያለሕግ ፡ በትእዛዝ ፡ ብቻ ፡ እንዳይገደዱ ፡ አመለክታለሁ ፡ ሲል ፡ በቴሌግራም ፡ አቤቱታውን ፡ ላከ ።

ከአገረ ፡ ገገርው ፡ ለጠበቃው ፡ ያለፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ በሹም ፡ ትእዛዝ ፡ ብቻ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ የከተማ ፡ ሹማምንቶች ፡ ምንም ፡ እንዳያደርጉ ፡ ትእዛዝ ፡ ተላልፎአል ፡ የሚል ፡ መልስ ፡ ደረሰው ፤ ሦስተኛ ፡ የከተማው ፡ ሹም ፡ ያለሕግ ፡ መብታችንን ፡ እንዲያዝ ፡ አድርጎብናልና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጥያቄ ፡ አድርጎ ፡ ሲገኝ ፡ ፍርድ ፡ እንዲሰጠኝ ፡ አላደረግሁም ፡ ቢል ፡ ማስረጃ ፡ እንዳቀርብ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዲፈቅድልኝ ፡ አመለክታለሁ ፡ ብሎ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ላቀረበው ፡ አቤቱታ ፡ ከስድስት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ እፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ መልስ ፡ እንዲሰጥ ፡ መደረጉን ፡ እንዲያውቀው ፡ ለጠበቃችን ፡ ተነገረው ፤

የከተማው ፡ ሹም ፡ ሚስተር ፡ ማንቴራ ፡ የመንግሥቱን ፡ ጠበቃ ፡ ይዞ ፡ ከሚስተር ፡ ናታን ፡ ማሬን ፡ ጋሬ ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርበው ፡ ክርክራቸውን ፡ ቀጠሉ ።

በመጀመሪያ ፡ የእኛ ፡ ጠበቃ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ከተማ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ እዚህ ፡ አገር ፡ የሚኖሩትን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ስደተኞች ፡ ተስፋ ፡ እንዲቆርጡና ፡ ልብ ፡ እንዲወርዳቸው ፡ እያደረጉ ፡ የሚረዱበት ፡ መብታቸውን ፡ ያለፍርድ ፡ እንዲያጡ ፡ ለማድረግ ፡ በፖሊስ ፡ እያስፈራሩ ፡ ያዟቸዋል ። ስለዚህ ፡ ያለሕግ ፡ ከሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ እንዲታገዱ ፡ ባለፈውም ፡ እንዲጠየቁ ፡ ሲል ፡ አመለከተ ። የኢየሩሳሌም ፡ የመንግሥቱም ፡ ጠበቃ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ መንግሥት ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ከሕግ ፡ የወጣ ፡ ሥራ ፡ አልሠራም ፡ ሲል ፡ መልስ ፡ ሰጠ ። የስደተኞቹም ፡ ጠበቃ ፡ ሚስተር ፡ ማንቴራ ፡ የተባለው ፡ የከተማው ፡ ሹም ፡ የኢጣልያኑን ፡ ቆንስል ፡



አስከትሎ ፡ መጥቶ ፡ ስደተኞቹ ፡ የሚረዱበትን ፡ ቤት ፡ ለኢጣልያ ፡ ቆንስል ፡ እንዲያስረክቡ ፡ ቢያዝ ፡ ያለፍርድ ፡ አናስረክብም ፡ ቢሉት ፡ በፖሊስ ፡ ቤቱ ፡ እንዲጠበቅ ፡ አድርጎ ፡ መሄዱን ፡ ማስረጃ ፡ ላቅርብ ፡ ሲል ፡ አስረዳ ።

የመንግሥቱም ፡ ጠበቃ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ መንግሥት ፡ አላዘዘም ፤ ሚስተር ፡ ማንቴራ ፡ ይህን ፡ አድርጎ ፡ እንደሆነ ፡ ተሳስቷል ፡ ሲል ፡ መልስ ፡ ሰጠ ፤ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ዳኛው ፡ የእኛን ፡ ጠበቃ ፡ መንግሥቱ ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡ አልሠራም ፡ አንድ ፡ ሠራተኛ ፡ ሠርቶ ፡ እንደሆን ፡ የሠራተኛው ፡ ስህተት ፡ እንጂ ፡ የመንግሥቱ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ፡ ብሏልና ፡ ምን ፡ ይሁንልኝ ፡ ትላለህ ፡ ሲል ፡ ጠየቀው ። ጠበቃችንም ፡ ወደፊት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሚገኘውን ፡ የኢትዮጵያኖችን ፡ መብትና ፡ ጥቅም ፡ ያለፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔና ፡ ትእዛዝ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ምንም ፡ ከመሥራት ፡ እንዲታገዱ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በትእዛዝ ፡ እንዲያግድልኝ ፡ ነው ፡ የምለምነው ፡ ሲል ፡ አመለከተ ።

ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ያለፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ በባለሥልጣኖች ፡ ትእዛዝ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩ ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ስደተኞች ፡ መብትና ፡ ጥቅም ፡ እንዳይነካ ፡ አዘዘ ። በዚህ ፡ ፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ጠበቃችን ፡ ደስ ፡ ሲለው ፡ ሳይታዘዝ ፡ ሠራ ፡ የተባለው ፡ የከተማው ፡ ሹም ፡ እንዲቀጣ ፡ ባለመደረጉ ፡ የስደተኞቹ ፡ ወኪል ፡ እኔ ፡ አዝኜ ፡ ጠበቃውን ፡ ለምን ፡ እንዲቀጣ ፡ አልጠየቅህም ፡ ብዬ ፡ ብጠይቀው ፤ ከጠበቃው ፡ ያገኘሁት ፡ መልስ ፡ አንተ ፡ የእንግሊዞችን ፡ ጠባይ ፡ ባለማወቅህ ፡ ነው ፡ ይህን ፡ መሹለኪያ ፡ በር ፡ ባልተውላቸው ፡ ይህን ፡ ፍርድ ፡ ባላገኘንም ፡ ነበር ። ለወደፊቱም ፡ ልትጠብቀው ፡ የሚገባህ ፡ ከእንግሊዞች ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ የምትከራከር ፡ በት ፡ ነገር ፡ ቢያጋጥምህ ፡ በሩን ፡ ዘግተህ ፡ አትከራከር ፤ ጥቂት ፡ የሚሾልኩበት ፡ በር ፡ ካገኙ ፡ ለመፈቱን ፡ የሚጀምሩትን ፡ ክርክር ፡ የማያጥጡ ፡ ናቸውን ፡ ሲረዱት ፡ ተወት ፡ አድርገው ፡ በዚያች ፡ ቀዳዳ ፡ ሾልከው ፡ ይሄዳሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ መሹለኪያ ፡ ቀዳዳ ፡ አሳጥተህ ፡ ልከራከር ፡ ያልክ ፡ እንደሆነ ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ ማምለጥ ፡ ስለሚያስቡ ፡ በርም ፡ ቢያጡ ፡ ጠንካራውን ፡ ግንብ ፡ ቀደው ፡ ነው ፡ የሚሄዱት ፤ ስለዚህ ፡ ማንቴራ ፡ ይቀጣ ፡ ብዬ ፡ ጠንክሬ ፡ ቢሆን ፡ ሳይታዘዝ ፡ የሠራ ፡ ስለማይሆን ፡ ነገሩ ፡ መንግሥቱን ፡ የሚነካ ፡ ስለሆነ ፡ ቤቱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ስለሆነ ፡ ነው ፡ በሚል ፡ መንገድ ፡ ተመርተው ፡ መንግሥቱን ፡ ከጥፋት ፡ ለማዳን ፡ የእኛን ፡ ነገር ፡ ያበላሹብን ፡ ነበር ፡ አለኝ ።

ለዳኞቹ ፡ ይህን ፡ መሹለኪያ ፡ በር ፡ ስለ ፡ ተውኩላቸው ፡ ነው ፡ ይህን ፡ ፍርድ ፡ ያገኘሁት ፡ በማለት ፡ ለወደፊቱ ፡ የሚሆነኝን ፡ ትምህርት ፡ ጭምር ፡ አስረዳኝ ፤ እኛም ፡ እውነተኛውን ፡ ፍርድ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ለማግኘት ፡ እንጠባበቅ ፡ ስለነበረ ፡ የጊዜውን ፡ ፍርድ ፡ በዚህ ፡ ዓይ

ነት ፡ ተቀበልንና ፡ በጠቅላላው ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሚፈረደውን ፡ ፍርድ ፡ እስክናገኝ ፡ ድረስ ፡ ከኢጣልያኖች ፡ ጋራ ፡ የፖሊቲካ ፡ ትግል ፡ ያለበትን ፡ ክርክር ፡ በሙግት ፡ ገጥሙን ፡ ስንከራከር ፡ የኢጣልያ ፡ ቆንስል ፡ ከስደተኛም ፡ ሆኖ ፡ ከመናኝያን ፡ መነኮሳት ፡ በገንዘብ ፡ እያባበለ ፡ ማስከዳት ፡ ጀመረና ፡ ይህን ፡ ጉዳይ ፡ እየተከታተለ ፡ የሚፈጽምለት ፡ አንድ ፡ ሎሬንዚኒ ፡ የተባለ ፡ የእስፓኝ ፡ ተወላጅ ፡ አዘጋጀና ፡ በግራና፡ በቀኝ ፡ እየተራወጠ ፡ ያዋክበን ፡ ጀመር ፡ የሙግቱም ፡ ነገር ፡ ከጊዜ ፡ ወደ ፡ ጊዜ ፡ እየተራዘመ ፡ ቶሎ ፡ አለመፈጸሙን ፡ ከተረዳ ፡ በኋላ ፡ ተከራዮቹን ፡ ቤቱ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ስለሆነ ፡ ኪራዩ ፡ ሊገባ ፡ የሚገባው ፡ ለኢጣልያ ፡ መንግሥት ፡ ነውና ፡ ኪራዩን ፡ ለስደተኞች ፡ እንዳ ትከፍሉ ፡ እያለ ፡ ይሰብክ ፡ ጀመረ ።

ከዕለታት ፡ ባንደኛው ፡ ቀን ፡ በላይኛው ፡ መስመር ፡ የጠቀስኩት ፡ የኢጣልያኖች ፡ ተላላኪ ፡ የሆነው ፡ የእስፓኝ ፡ ተወላጅ ፡ ክርክር ፡ በተነ ሳበት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ተከራዮች ፡ ስምና ፡ የቤቱን ፡ የመ ለያ ፡ ቁጥር ፡ እየቦረ ፡ ሲጽፍ ፡ ስለ ፡ አገኘሁት ፡ ይዞ ፡ የወንድ ፡ እጅ ፡ ለማሳየት ፡ ክርቅ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ቤት ፡ እሱ ፡ወዳለበት ፡ ስደርስ ፡ እን ዴት ፡ እንደሮጠና ፡ አውቶሞቢሉ ፡ ውስጥ ፡ እንደገባ ፡ በጽሕፈት ፡ ልገ ልጸው ፡ ባልችልም ፡ የፍርሐት ፡ ሽሽቱ ፡ የተገለጸ ፡ ነበር ። ከዚያን ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ይህ ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ እንጂ ፡ እንደውትሮው ፡ በዚያ ፡ ቤትና ፡ በገዳሙም ፡ አቅራቢያ ፡ ሊታይ ፡ አልቻለም ፡ ተደርሶ በት ፡ የታሰበለትን ፡ ከዘራ ፡ ቀምሶ ፡ ቢሆን ፡ ከኢጣልያ ፡ ቆንስሉ ፡ አገል ግሎት ፡ ውጭ ፡ መሆኑ ፡ የማያጠራጥር ፡ በሆነ ፡ ነበር ፡ ከሁሉም ፡ የሚ ገርመው ፡ የዚህ ፡ የስፓኝ ፡ ተወላጅ ፡ ታሪክ ፡ ነው ። ይህ ፡ ሰው ፡ እኛ ፡ ስናውቀው ፡ የኢጣልያ ፡ ቆንስል ፡ ሠራተኛነቱን ፡ ነበር ።

ነገር ፡ ግን ፡ የኢጣልያ ፡ ጉዳይ ፡ ወደ ፡ ቅሉቱ ፡ አዘንብሎ ፡ የእንግ ሊዝን ፡ ወዳጅነት ፡ ከድቶ ፡ ወደ ፡ ጀርመን ፡ ጓደኝነት ፡ ሲዛወርና ፡ ተጠቂ፡ የነበሩት ፡ ኢትዮጵያውያኖች ፡ ወደ ፡ ጦር ፡ ጓደኛነት ፡ ተቃርበን ፡ የስደ ተኞቹ ፡ ወኪል ፡ የነበርኩት ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ወደሚገኙበት ፡ ወደ ፡ ካርቱም ፡ ተጠራሁ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የፓስፖርት ፡ ጉዳይ ፡ ለማዘጋጀት ፡ እኔና ፡ ኰሎኔል ፡ ታምራት ፡ ወደ ፡ ፓስፖርት ፡ ክፍል ፡ ሠራተኞች ፡ ስንሄድ ፡ ያ ፡ እላይ ፡ ስሙ ፡ የተጠቀሰው ፡ የኢጣልያ ፡ የምስጢር ፡ ሠራ ተኛ ፡ ነው ፡ የምንለው ፡ ሰው ፡ ዓይነተኛው ፡ የእንግሊዝ ፡ የምስጢር ፡ ሠራተኛ ፡ ኖሮ ፡ የምስጢር ፡ ዶኪማዎች ፡ ሲመረምር ፡ አገኘነውና ፡ ደግሞ ፡ እዚህ ፡ ምን ፡ አመጣህ ፡ ብዬ ፡ ብጠይቀው ፡ እናንተ ፡ አታው ቁም ፡ እንጅ ፡ እኔ ፡ ዓይነተኛው ፡ ሥራዬ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ሠራ ተኛ ፡ ነኝ ፡ አለን ። በነገሩ ፡ እየተደነቅን ፡ በሳቅ ፡ አሳለፍነውና ፡ የፓስፖ ርታችንን ፡ ጉዳይ ፡ ጨርሰው ፡ ወደ ፡ ካርቱም ፡ ጉዞዋችን ፡ ተዘጋጀን ።



እዚህ ፡ ታሪክ ፡ ማስታወሻ ፡ ላይ ፡ ሳልጠቅሰው ፡ የማላልፈው ፡ ኢየሩ ሳሌም ፡ በስደቱ ፡ ዘመን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወጣቶች ፡ የተሰኙ ፡ ማኅበር ፡ ተብሎ ፡ በልጅ ፡ ታምራት ፡ ይገዙ ፡ (ዛሬ ፡ ሌተና ፡ ኰሎኔል) ፡ ሊቀ ፡ መንበርነት ፡ ተቋቁሞ ፡ የነበረውን ፡ ማኅበር ፡ ያቋቋሙንና ፡ ይሠራም ፡ የነበረውን ፡ አገልግሎት ፡ ነው ።

ይህን ፡ ማኅበርና ፡ ለስደተኞችም ፡ አንድ ፡ የመረዳጃ ፡ ማኅበር ፡ ለማቋቋም ፡ ስናስብ ፡ የማኅበሩን ፡ ደንብ ፡ አስቀድሞ ፡ ማዘጋጀት ፡ ስለ ሚያስፈልግ ፡ ከሕግ ፡ አዋቂ ፡ ተነጋግሮ ፡ ሐሳብ ፡ ለማግኘት ፡ ጃንሆይ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ በመጀመሪያ ፡ ቤቱን ፡ ተከራይተው ፡ ያረፉበት ፡ ባለቤት ፡ አቡካሪዎስ ፡ ቤይ ፡ የተባለ ፡ የዓረብ ፡ ተወላጅ ፡ ሚስቱ ፡ እሥራኤላዊ ፡ የነበረች ፡ ሰው ፡ ይህም ፡ ሰው ፡ ሕግ ፡ አዋቂ ፡ ስለሆነና ፡ ጃንሆይም ፡ ቤቱ ፡ በኪራይ ፡ ገብተው ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ተዋውቆን ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ለማኅበሩ ፡ አቋቋም ፡ ምክር ፡ እንዲሰ ጠንና ፡ ሕጉንም ፡ እንዲያዘጋጅልን ፡ ልንጠይቅ ፡ ደጃዝማች ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው ፡ (ክቡር ፡ ቢትወደድ) ፡ ልጅ ፡ ታምራት ፡ ይገዙ ፡ እኔም ፡ ሄደን ፡ ስንጠይቀው ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ እኛ ፡ የሄድንበትን ፡ ጉዳይ ፡ ትቶ ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ ወ ስጣችንንና ፡ አቅማችንን ፡ ለማወቅ ፡ ይጠይቀን ፡ ጀመር ። እኛም ፡ ትንሽም ፡ ሆነ ፡ ትልቅ ፡ ባለው ፡ አቅሙ ፡ ተረዳድቶ ፡ ለመኖር ፡ ነውና ፡ የምናስበው ፡ የመረዳጃ ፡ ማኅበር ፡ የሚቆምበት ፡ ደንብ ፡ ነው ፡ የሚሠሩልን ፡ አልነው ፡ እሱም ፡ ካፒታላችሁን ፡ ካልነገ ራችሁኝ ፡ መሥራት ፡ አልችልም ፡ ብሎ ፡ መልስ ፡ ሰጠንና ፡ ከእሱ ፡ ዘንድ ፡ ስንወጣ ፡ የኢጣሊያን ፡ ቆንስል ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ዘንድ ፡ መጥቶ ፡ ኖሮ ፡ እበሩ ፡ ላይ ፡ ተገናኘን ፤

ይህ ፡ አቡካሪዎስ ፡ ቤይ ፡ የተባለ ፡ ሰው ፡ ለኢጣሊያኖች ፡ ዋና ፡ ሠራተኛ ፡ ኖሮ ፡ የእኛን ፡ አቅም ፡ ለመመርመርና ፡ ውስጣችንን ፡ ሲያ ውቅ ፡ ለኢጣሊያ ፡ ቆንስል ፡ ለማስታወቅ ፡ መሆኑን ፡ ተረዳንና ፡ ሁለ ተኛ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ዘንድ ፡ ሳንመለስ ፡ ቂስ ፡ ማቲው ፡ በተባሉ ፡ እንግሊ ዛዊ ፡ አማካይነት ፡ አንድ ፡ የመረዳጃ ፡ ማኅበር ፡ እንድናቋቁም ፡ የኢየሩ ሳሌምን ፡ መንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ እንዲያስፈቅዱልን ፡ የማኅበሩም ፡ ስም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወጣቶች ፡ የተሰኙ ፡ ማኅ በር ፡ እንዲባል ፡ ጠይቀናቸው ፡ እሳቸው ፡ ከባለሥልጣኖች ፡ ተነጋግረው ፡ ያመጡልን ፡ መልስ ፡ ተሰኙ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ፖሊቲካ ፡ ነክ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እሱ ፡ ይሰረዝና ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንዲሁ ፡ እንዳለ ፡ መፍቀድ ፡ አይቻልም ፡ ብለዋል ፡ ብለው ፡ መለሱልን ፡ እንደገና ፡ ይህንኑ ፡ ስም ፡ እንደያዘ ፡ እን ዲያስፈቅዱልን ፡ ናታን ፡ ማሬን ፡ የተባለው ፡ ጠበቃችንን ፡ ጠየቅነው ፡ እሱም ፡ ጥቂት ፡ ለውጥ ፡ በማድረግ ፡ ባማርኛ ፡ ተሰኙ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ እንዲኖር ፡ አድርጐ ፡ በእንግሊዝኛው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወጣቶች ፡ ማኅበር ፡

በማለት ፡ አሻሽሎ ፡ አስፈቀደልንና ፡ ማኅበሩ ፡ እንዲቆም ፡ ሆነ ፡ ለዚህ ፡ ማኅበር ፡ አባል ፡ የሚሆኑት ፡ በየጊዜው ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሄደው ፡ የተገኙት ፡ ጥቁር ፡ ራስ ፡ በሚባል ፡ ስም ፡ የሚጠሩት ፡ ኢትዮጵያውያኖችና ፡ እንደዚሁም ፡ በትምህርት ፡ ላይ ፡ የነበሩት ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ከጦርነቱ ፡ በስደት ፡ የሄዱት ፡ መኳንንቶች ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በገቡበት ፡ ጊዜ ፡ የፖለቲካም ፡ ሆነ ፡ ሌላም ፡ ራሳቸውን ፡ የሚረዱበት ፡ ሥራ ፡ እንኳን ፡ ሠርተው ፡ እንዳይኖሩ ፡ የተከለከሉ ፡ ነበርና ፡ በግልጥ ፡ የማኅበሩ ፡ አባል ፡ ሆኖ ፡ ለመመዝገብ ፡ አልተቻለም ፡ ነበረ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ልጅ ፡ ታምራት ፡ ይገዙ ፡ (ሌተና ፡ ኰሎኔል) ፡ በትምህርት ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ለዚህ ፡ ማኅበር ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ሆኖ ፡ እንዲመራ ፡ ሆነና ፡ ማኅበሩ ፡ ወዲያው ፡ ተቋቁመና ፡ በገዳሙ ፡ ላይ ፡ ደርሶ ፡ ለነበረው ፡ ችግር ፡ ለመርዳት ፡ ይህ ፡



የተሰፋ ፡ ኮከብ ፡ ማኅበር ፡ አባሎች ፡

ማኅበር ፡ ጠቃሚ ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ ፤ ጠቃሚነቱን ፡ ያሳየው ፡ የኤርትራ ፡ ተወላጅ ፡ የሆኑት ፡ መነኮሳት ፡ ወደ ፡ ኢጣልያ ፡ ቆንስል ፡ ሄደው ፡ ስለ ፡ ገቡና ፡ በምዕራፍ ፡ ፲፫ ፡ በገጽ ፡ ፲፬ ፡ ገልጸን ፡ እንደጻፍነው ፡ ባስቸገሩበት ፡ ጊዜ ፡ እንደዚሁም ፡ በስደተኞች ፡ ይጠበቅ ፡ የነበረውን ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ያሠሩትን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ቤት ፡ የኢጣልያን ፡ ቆንስል ፡ ካገሩ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ጋራ ፡ በመስማማት ፡ ያደርስብን ፡ የነበረውን ፡ ችግር ፡ በዘብ ፡ ጥበቃና ፡ ጉልበትም ፡ በሚያስፈልግበት ፡ ጊዜ ፡ ተገቢውን ፡ ዕርዳታ ፡ ሳያጓድሉ ፡ በፕሬዚዴንታቸው ፡ እየተመሩ ፡ ያገለግሉና ፡ ይረዱ ፡ ነበር ፡ የዚህን ፡ ማኅበር ፡ ዕርዳታ ፡ ለማደናቀፍና ፡



ማኅበሩንም ፡ ለማፍረስ ፡ ወደጠላት ፡ የተጠጉት ፡ የኤርትራ ፡ ተወላጅ ፡ የሆኑት ፡ መነኮሳት ፡ ለኢጣሊያን ፡ ቆንስል ፡ እየነገሩ ፡ ማስቸገራቸው ፡ አልቀረም ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የሚያቀርቡት ፡ ምክንያት ፡ አጥጋቢ ፡ ሳይሆን ፡ እየቀረ ፡ አቤቱታቸው ፡ እየከሸፈ ፡ እንዲያውም ፡ በሩቅ ፡ ሲያዩዋቸው ፡ አቀለሉዋቸውና ፡ መደመጥን ፡ እየነሡ ፡ ያባርሯቸው ፡ ጀመር ፡፡

የኢትዮጵያ ፡ ወጣቶች ፡ የተስፋ ፡ ማኅበር ፡ አባሎች ፡ የነበሩት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፉት ፡ ናቸው ፡፡

፩ ፡ ልጅ ፡ ታምራት ፡ ይገዙ ፡ (ሌተና ፡ ኰሎኔል) ፡ የማኅበሩ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ (ሊቀ ፡ መንበር)
፪ ፡ አቶ ፡ ኃይለማርያም ፡ ግዛው ፡ (ብ/ጄኔራል)፡ አባል ፡
፫ ፡ አቶ ፡ ዱባለ ፡ ሽፈራው ፡ »
፬ ፡ አቶ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሣህሉ ፡ »
፭ ፡ » ኪዳነ ፡ ማርያም ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ »
፮ ፡ » ይፍሩ ፡ ሸዋ ፡ »
፯ ፡ » የማነ ፡ ብርሃን ፡ አምበሴ ፡ »
፰ ፡ » አረፈ ፡ ዓይኔ ፡ ሰለባ ፡ »
፱ ፡ አባ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ አገው ፡ »
፲ ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ ሰጡኝ ፡ »
፲፩ ፡ አባ ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስ ፡ ሞገሴ ፡ »
፲፪ ፡ አቶ ፡ አስፋው ፡ ኤጉታ ፡ »
፲፫ ፡ » አስፋው ፡ አበበ ፡ »
፲፬ ፡ » ገብረሥላሴ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ »
፲፭ ፡ » ገብረ ፡ ኪዳን ፡ »
፲፮ ፡ » አቶ ፡ ዓለሙ ፡ ኃይሉ ፡ »
፲፯ ፡ አባ ፡ አቢየ ፡ እግዚእ ፡ »
፲፰ ፡ አቶ ፡ ከበደ ፡ ዓለሙ ፡ »
፲፱ ፡ » ከበደ ፡ ቀማው ፡ »
፳ ፡ » ተሰማ ፡ ዘሩ ፡ »
፳፩ ፡ » ዮሴፍ ፡ ቦሼ ፡ »
፳፪ ፡ » አብራሂም ፡ ባኪቅ ፡ »
፳፫ ፡ » ዮሴፍ ፡ ወረሂመኑ ፡ »
፳፬ ፡ » ወርቁ ፡ አድማሴ ፡ »
፳፭ ፡ » ያዕቆብ ፡ »
፳፮ ፡ » ኃይለጊዮርጊስ ፡ »
፳፯ ፡ » ኢዮብ ፡ ግሼን ፡ »
፳፰ ፡ » ወልደሥላሴ ፡ ሾሎም ፡ »
፳፱ ፡ » ባራኪ ፡ ኪዳኔ ፡ »

| | | |
|---|---|---|
| ፴፡ | » መሸሻ ፡ | አባል ፡ |
| ፴፩፡ | » ከምሱር ፡ | » |
| ፴፪፡ | » ተገኝ ፡ ቢአድግልኝ ፡ | » |
| ፴፫፡ | » አበራ ፡ እጅጉ ፡ | » |
| ፴፬፡ | » ወልደ ፡ ሰንበት ፡ ሰርዶ ፡ | » |



ልጅ ፡ ታምራት ፡ ይገዙ ።



አቶ ፡ ኪዳነ ፡ ማርያም ፡ ወልደ፡ ማርያም ።



አቶ ፡ የማን ፡ ብርሃን ፡ አፍረሴ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፬ ።

## በአገር ፡ ውስጥ ፡ ላሉ ፡ አርበኞች ፡ በየጊዜው ፡ መልእክት ፡ ያደረሱ ።

የኢትዮጵያ ፡ ጉዳይ ፡ ለጄኔብ ፡ ጉባኤ ፡ ቀርቦ ፡ በቀጠሮ ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፡ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ እየገቡ ፡ በአርበኞችና ፡ በስደተኞች ፡ መሐከል ፡ መገናኛ ፡ ማለት ፡ መሸጋገሪያ ፡ ድልድይ ፡ ሆነው፡ ግንኙነት ፡ የመሠረቱትን ፡ ታሪክ ፡ ሲያስታውሳቸው ፡ እንዲኖር ፡ ማድረግ ፡ ስለሚገባ ፡ ስማቸውን ፡ በሚቀጥለው ፡ መስመር ፡ በመግለጽ ፡ ታሪኩን ፡ የመከተል ፡ ፍቅር ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ እንዲያውቃቸው ፡ አቅርቤያለሁ ።



አቶ ፡ ሎሬንስ ፡ ታእዛዝ ፡ (ብላቴን ፡ ጌታ) ፡

አቶ ፡ ሎሬንስ ፡ ታእዛዝ ፡ (ብላቴን ፡ ጌታ) ፡ የአርበኝነትና ፡ የስደተኝነት ፡ ስማቸው ፡

ሀ/ ለአንዱ ፡ ክፍል ፡ ፊታውራሪ ፡ መብራቱ ፡

ለ/ ደግሞ ፡ ላንደኛው ፡ ክፍል ፡ አቶ ፡ ገብርኤል ፡ በመባል ፡ ይጠሩ ፡



አቶ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡



ባላምባራስ ፡ አሸብር ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡



አቶ ፡ የፍታሔ ፡ ንጉሤ ፡



የነበር ፡ (ባርማጭሆ ፡ ጎጃም) ፡
አቶ ፡ የፍታሔ ፡ ንጉሤ ፡ (በጎጃም)
አቶ ፡ ጌታሁን ፡ ተሰማ ፡ (ባርማጭሆ ፡ በጭልጋ ፡ በጎጃም)
አቶ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ ሃብተማርያም ፡ (በጎጃም)
አቶ ፡ ታደሰ ፡ ገብረመድኅን ፡ (በጎጃም)
በላምባራስ ፡ አሸብር ፡ ገብረሕይወት ፡ (ባርማጭሆ)
አቶ ፡ አማኑኤል ፡ መንገሻ ፡ (ባርማጭሆ ፡ በጭልጋ ፡ በጎጃም ፡ በቤጌምድር) ፡
አቶ ፡ አሰጋኸኝ ፡ አርአያ ፡ (በጎጃም ፡ በበጌምድር ፡ በየሌላ ወም ፡ ሥፍራ ፡ ሁሉ) ፡
ካፒቴን ፡ ከበደ ፡ ወልደ ፡ ሰማዕት ፡ (በጎጃም) ፡
ልጅ ፡ ይገባሃል ፡ (በጎጃም) ፡
አቶ ፡ ወልደጊዮርጊስ ፡ ተድላ ፡ (በበጌምድር ፡ በጎጃም)

እነዚህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ስማቸው ፡ የተጠቀሰውና ፡ ሌሎችም ፡ አሁን ፡ ስማቸው ፡ የተዘነጋኝ ፡ የእነዚህ ፡ ተከታዮችና ፡ ረዳት ፡ ሆነው ፡ በስደት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ከወጡ ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ በበጌምድርና ፡ በጎጃም ፡ በወሎ ፡ በኩል ፡ እየወጡ ፡ የግርማዊነታቸውን ፡ የፖለቲካ ፡ ትግል ፡ ለአርበኞች ፡ በማስረዳት ፡ ማበረታታትና ፡ እንዲሁም ፡ የአርበኞችን ፡ ተጋድሎና ፡ ብርታት ፡ ለግርማዊነታቸው ፡ እንዲደርስ ፡ በማድረግ ፡ ራሳቸውን ፡ መሥዋዕት ፡ በማድረግ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ነፃነት ፡ የተጋደሉ ፡ ናቸው ፡ ለተከታዩ ፡ መግቢያ ፡ የሆነው ፡ በር ፡ በመጀመሪያ ፡ በእነዚህ ፡ ጀግኖች ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ።

## ጃንሆይ ፡ ከሎንዶን ፡ ካርቱም ፡ እንደደረሱ ፡ ወደጎጃም ፡ የተላኩ ።

በጎጃም ፡ ላሉ ፡ አርበኞች ፡ የግርማዊነታቸውን ፡ አዋጅ ፡ በሐምሌ ፡ በመጀመሪያው ፡ ወር ፡ ተልከው ፡ ያደረሱ ፡ በመጀመሪያም ፡ ወደ ፡ ካርቱም ፡ በስደት ፡ ከመግባታቸው ፡ በፊት ፡ በአርበኝነት ፡ ከነሻለቃ ፡ መስፍን ፡ ስለሺና ፡ ከነብላታ ፡ ታከለ ፡ ወልደ ፡ ሐዋርያት ፡ ጋራ ፡ የነበሩትን ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ መስመር ፡ እገልጻለሁ ።

፩/ አቶ ፡ አየለ ፡ ጀርመን ፡
፪/ አቶ ፡ መኰንን ፡ ደስታ ፡

፫/ ሻምበል ፡ ተሰማ ፡ ገብሬ ፡
፬/ አቶ ፡ እንግዳ ፡ ወልደማርያም ፡
፭/ አቶ ፡ ተስፋዬ ፡ በላቸው ፡
፮/ አቶ ፡ ጢጋዬ ፡ ዳምጠው ፡
፯/ አቶ ፡ ዘመድኩን ፡
፰/ አቶ ፡ የማነ ፡
፱/ አቶ ፡ ነጋሽ ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ፡
፲/ አቶ ፡ በዛብህ ፡ ደስታ ፡



አቶ ፡ አሰጋኸኝ ፡ አርአያ ፡ (ደጃዝማች) ።

## ከኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ሱዳን ፤

ኒውማን ፡ የተባለው ፡ አንድ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ የፀጥታ ፡ ክፍል ፡ ሠራተኛ ፡ (የእንቴሌጀንት ፡ ሰርቪስ) ፡ ከምኖርበት ፡ ቤት ፡ መጥቶ ፡ በሩን ፡ አንኳኳ ፡ ማነህ ፡ብዬ ፡ ከፍቼ ፡ ብቅ ፡ ብል ፡ ይህን ፡ ስሙን ፡ እላይ ፡





አቶ ፡ አየለ ፡ ጀርመን ፡



አቶ ፡ እንግዳ ፡ ተሰማ ፡
እሸቴ ፡

የተጻፈውን ፡ ሰው ፡ አገኘሁት ፡ እሱም ፡ እንዳየኝ ፡ አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ማለት ፡ አንተ ፡ ነህን ፡ ሲል ፡ ጠየቀኝ ፡ እኔም ፡ አዎን ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ አልኩት ። ከዚህ ፡ ጥያቄ ፡ በኋላ ፡ ከግርማዊ ፡ ጌታዬ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የተጻፈ ፡ የጥሪ ፡ ደብዳቤ ፡ ከኪሱ ፡ አውጥቶ ፡ ሰጠኝ ። ደብዳቤውን ፡ ከተመለከትሁ ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ መንገዴ ፡ አኳኋን ፡ ተነጋገርንና ፡ በቀጠሮ ፡ ተለያየን ። የደብዳቤውም ፡ ቃል ፡ ባጭሩ ፡


«አንተ ፡ ትሠራበት ፡ የነበረውን ፡ ማስረጃና ፡ ዶኪማ ፡ በሙሉ ፡ ለአቶ ፡ ዓለሙ ፡ ቸኰል ፡ የቤቱን ፡ ዕቃ ፡ ለበጅሮንድ ፡ ረታ ፡ አስረክብና ፡ አንተ ፡ እኛ ፡ ወዳለንበት ፡ በቶሎ ፡ ና» ፡ የሚል ፡ ነው ፤ እንደትእዛዙ ፡ ዶኪማውን ፡ ለአቶ ፡ ዓለሙ ፡ ቸኰል ፤ ዕቃውን ፡ ለበጅሮንድ ፡ ረታ ፡ አስረከብኩ ፡ በቀጠሮ ፡ የተለያየነውም ፡ እንግሊዛዊ ፡ በማግሥቱ ፡ መጣና ፡ ወደ ፡ ፓስፖርት ፡ ክፍል ፡ ወሰደኝና ፡ ስለ ፡ መተላለፊያዬ ፡ አስፈላጊውን ፡ ፈጸመልኝና ፡ የምትሄደው ፡ ነገ ፡ ጧት ፡ ስለሆነ ፡ ተዘጋጅተህ ፡ ቆየኝ ፡ ብሎ ፡ ተለያየን ።

በማግሥቱ ፡ ሐምሌ ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ዓርብ ፡ ጧት ፡ መጣና ፡ ዕቃዬንና ፡ እኔን ፡ በመኪና ፡ እስከ ፡ ባቡር ፡ ጣቢያ ፡ ወስዶ ፡ እኔም ፡ እሱም ፡ በባቡር ፡ ተሳፈርንና ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ እስክልዳ ፡ ሸኘኝና ፡ ተመለሰ ። እኔም ፡ ጉዞዬን ፡ ቀጥዬ ፡ በፖርትሳይድ ፡ በኩል ፡ ካይሮ ፡ ስደርስ ፡ ዶክተር ፡ አምባዬንና ፡ ቄስ ፡ ማቴውን ፡ አገኘኋቸው ። እነሱም ፡ እኔን ፡ ሊቀበሉ ፡ የመጡ ፡ ኖረው ፡ ከባቡር ፡ ስወርድ ፡ ወደኔ ፡ መጥተው ፡ ዕቃዬንም ፡ እኔንም ፡ በመኪና ፡ ወስዱኝና ፡ ባንድ ፡ ሆቴል ፡ አሳረፉኝ ። ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትን ፡ ስለ ፡ ማግኘቴ ።

ተከታዩም ፡ ቀን ፡ እሁድ ፡ ስለሆነ ፡ ካይሮ ፡ ዋልኩና ፡ አደርኩ ። በሶስተኛው ፡ ቀን ፡ ሰኞ ፡ ከጧቱ ፡ በ፲፪ ፡ ሰዓት ፡ ከካይሮ ፡ አይሮፕላን ፡ ጣቢያ ፡ ተሳፈርኩና ፡ ጉዞዬን ፡ ወደ ፡ ካርቱም ፡ ቀጠልኩ ። በ፩ ፡ ሰዓት ፡ ፖርት ፡ ሱዳን ፡ ከሚባል ፡ ቦታ ፡ ሲደርስ ፡ አይሮፕላኑ ፡ አርፎ ፡ ቤንዚን ፡ ሞላና ፡ እንደገና ፡ ጉዞውን ፡ ቀጥሎ ፡ በ፮ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ካርቱም ፡ አይሮፕላን ፡ ጣቢያ ፡ ደረስን ። ወዲያው ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ወደ ፡ አሉበት ፡ እንዲያደርሱኝ ፡ ጠየቅሁና ፡ በታክሲ ፡ መኪና ፡ ላኩኝና ፡ እነፊታውራሪ ፡ ብሩ ፡ አሉበት ፡ አደረሱኝ ። ፊታውራሪ ፡ ብሩ ፡ ገና ፡ ሲያዩኝ ፡ ብድግ ፡ ብለው ፡ ስልክ ፡ ቤት ፡ ገቡና ፡ መምጣቴን ፡ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ነገሩ ። ከግርማዊነታቸው ፡ ዘንድ ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ሎሬንሶ ፡ መጥተው ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ካሉበት ፡ አድርሰው ፡ አገናኙኝ ።



እኔም ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፊት ፡ ቀርቤ ፡ እጅ ፡ ከነሳሁ ፡ በኋላ ፡ ግርማዊነታቸውም ፡ የጠራንህ ፡ ቀዳሚ ፡ መላክተኛ ፡ ሆነህ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አገራችን ፡ እንድትገባ ፡ ነው ፡ አስቸኳይ ፡ ስለሆነ ፡ ነገ ፡ ነው ፡ የምትነሳው ፡ በማለት ፡ ተነገረኝ ፤ እኔም ፡ የግርማዊነታቸውን ፡ ትእዛዝ ፡ ተቀብዬ ፡ በደስታ ፡ የምፈጽም ፡ መሆኔን ፡ በትህትና ፡ ገለጽሁ ። በማግሥቱም ፡ እንኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ወደሚገኙበት ፡ ገዳሪፍ ፡ ወደተባለው ፡ አገር ፡ ከብላቴን ፡ ጌታ ፡ ሎሬንሶ ፡ ጋራ ፡ በባቡር ፡ ሄድን ።



ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ብቻቸውን ፡ በድንኳን ፡ በር ፡ ላይ ።

ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ሎሬንሶ ፡ ተኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ አገናኝተውኝ ፡ እሳቸው ፡ ወደ ፡ ካርቱም ፡ ሲመለሱ ፡ እኛም ፡ ወደ ፡ ዶካ ፡ ተጓዝን ። ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ለሥራ ፡ ረዳት ፡ ሆነው ፡ የተላኩት ፡ አቶ ፡ ጌታሁን ፡ ተሰማና ፡ አቶ ፡ አሰጋኸኝ ፡ አርአያ ፡ አብረውኝ ፡ ነበሩ ።

ልጅ ፡ መርዕድ ፡ መንገሻ ፡ ተንኮሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ጋራ ፡ ቀድመው ፡ ስለነበረ ፡ በዚያው ፡ ገዳረፍ ፡ አገኘናቸው ። ዶካ ፡ ስንደርስ ፡ ግን ፡ አቶ ፡ ኀብረመስቀል ፡ ሀብተማርያም ፡ ሌሎችም ፡ ሃምሳ ፡ የሚሆኑ ፡ ኢትዮጵያውያኖች ፡ ለዚሁ ፡ ጉዞ ፡ የተዘጋጁ ፡ አገኘን ፡ በማግሥቱ ፡ ሰዎቹን ፡ ሰብስበው ፡ ኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ራሳቸውን ፡ የእንግሊዝ ፡



አባቸር ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ። ኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ።

መንግሥት ፡ መላክተኛ ፡ አባቸር ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ መላክተኛና ፡ እንደራሴ ፡ መሆናችንን ፡ ገልጸው ፡ ለተሰበሰቡት ፡ ጓደኞቼ ፡ አስረዱና ፡ ወዲያው ፡ ስለመንገዳችን ፡ አኳኋን ፡ ብርቱ ፡ ጉዞ ፡ ያለብን ፡ መሆኑንና ፡ መበርታት ፡ እንዳለብን ፡ ገለጹ ። በማግሥቱ ፡ ዶካን ፡ ለቀን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለመግባት ፡ ጉዞዋችንን ፡ ቀጠልንና ፡ ሐምሌ ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የሱዳንን ፡ ወሰን ፡ አልፈን ፡ በኢትዮጵያ ፡ መሬት ፡ ገባን ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

## በሱዳን ፡ በኩል ፡ ወደኢትዮጵያ ፡ መግባት ።

የጠላት ፡ ጦር ፡ ድል ፡ ሊያገኝ ፡ ያስቻለውንና ፡ የእኛም ፡ ጦር ፡ ለመጠቃት ፡ የደረሰበትን ፡ ምክንያት ፡ የተረዳሁትንና ፡ ያወቅሁትን ፡ ያህል ፡ በመዘርዘር ፡ ያለፈውን ፡ ከረጅሙ ፡ ባጭሩ ፡ ጽፌ ፡ ያስረዳሁ ፡ ይመስለኛል ። ለወደፊቱ ፡ ግን ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ እንደሚያስፈልግ ፡ ለኔ ፡ የተሰማኝን ፡ ያህል ፡ ለአንባቢዎች ፡ ለመግለጽ ፡ እሞክራለሁ ። ቀደም ፡ አድርጌ ፡ ላንባቢዎች ፡ እንዳስረዳሁትና ፡ ምክንያቱንም ፡ ባጭሩ ፡ ገልጬ ፡ እንደተረክሁት ፡ ሁሉ ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ እኛን ፡ ሊያጠቃን ፡ የቻለው ፡ በወታደር ፡ ብዛትና ፡ በመሣሪያ ፡ ምርጥነት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በሰላሙ ፡ ጊዜ ፡ ነበር ። ይኸውም ፡ በፖለቲካ ፡ መሪዎች ፡ በኩል ፡ ይሠራና ፡ ያሠራውም ፡ በነበረው ፡ የዲፕሎማሲ ፡ አሠራር ፡ የውስጥ ፡ ሰምምንታችንን ፡ እርስ ፡ በርስ ፡ በማለያየት ፡ በረጅም ፡ ጊዜ ፡ በመሥራት ፡ ካደከመና ፡ ካበሰለ ፡ በኋላ ፡ ያሰበው ፡ እንደተፈጸመለት ፡ ሲረዳውና ፡ የኃይላችንን ፡ መቀነስ ፡ ሲያውቅ ፡ በሐረር ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ በኦጋዴን ፡ አውራጃ ፡ በወልወል ፡ በኩል ፡ ጠብ ፡ ማጫር ፡ ጀመረ ። ከዓለም ፡ ማኅበር ፡ አቤቱታ ፡ በማቅረብ ፡ ቢደከምም ፡ የዕለት ፡ ግጭት ፡ ሳይሆን ፡ በረጅም ፡ ጊዜ ፡ ሐሳቡን ፡ በጥላን ፡ የሠራው ፡ ስለሆነ ፡ ጠላታችንን ፡ የዓለም ፡ ማኅበር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔም ፡ አላገደው ፡ ብሎ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ድረስ ፡ በፖለቲካ ፡ አሠራሩ ፡ ያደከመውንና ፡ ያሳሳውን ፡ የጦር ፡ ኃይል ፡ በመርዝ ፡ ጭስና ፡ በቦምብ ፡ አጥቅቶ ፡ ለጊዜው ፡ የአገራችንን ፡ ከተማ ፡ ከተማውን ፡ በገሚስ ፡ ለመያዝ ፡ ቻለ ።

የንጉሠ ፡ ነገሥታችንም ፡ ልበ ፡ ሙሉነት ፡ የጊዜውን ፡ የጠላትን ፡ ማጥቃትና ፡ ድል ፡ ማድረግ ፡ ባለማመን ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ ተሰደው ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ድረስ ፡ ደከሙ ፡ ተጋደሉ ። ከልባቸው ፡ በእውነት ፡ የሚያምኑት ፡ ፈጣሪያቸውም ፡ የትግላቸውን ፡ ብርታትና ፡ የልመና ፡ ጸሎታቸውን ፡ ሰምቶ ፡ የተባበሩት ፡ ነገሥታት ፡ የተባሉትን ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ አጋጭቶ ፡ ለእኛ ፡ ለኢትዮጵያውያኖች ፡ ሳያስቡ ፡ ለየራሳቸው ፡ በማሰብ ፡ የጦር ፡ ጓደኛ ፡ አደረጉና ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችንን ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴን ፡ ለአገራቸው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አርበኛና ፡ ሕዝብ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የሚገኙትን ፡ አዋጆች ፡ በራዲዮ ፡ እንዲያሰሙና ፡ ወደአገራቸው ፡ እንዲገቡ ፡ አደረጉ ።

## ግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥት ፡ ለሕዝባቸው ፡ ያሰሙት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አዋጅና ፡ ትእዛዝ ።

ኢትዮጵያ ፡ እጆቿን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትዘረጋለች ።

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡

ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

### አ ዋ ጅ ፡

### የኢትዮጵያ ፡ ሹማምንት ፡ አርበኞች ።

ባለፈው ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ በጀግንነትና ፡ ተስፋ ፡ ባለመቁረጥ ፡ ዘወትር ፡ ኃይላችሁ ፡ ሳይሰበር ፡ ከአጥቂም ፡ ጠላታችን ፡ ጋራ ፡ እየተከራከራችሁ ፡ በመቆየታችሁ ፡ ነፃ ፡ የሆነ ፡ የዓለም ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ አድንቃችሁ ፡ ወዳጅነታቸውንም ፡ አገኘሁ ። የደረሰባችሁ ፡ ሥቃይና ፡ መሥዋዕትነታችሁ ፡ ጀግንነታችሁና ፡ ተስፋችሁ ፡ ከንቱ ፡ ሆኖ ፡ አልቀረም ። የመዳኛችሁ ፡ ቀን ፡ ደረሰ ። ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ የታላቂቱ ፡ ብሪታንያ ፡ መንግሥት ፡ ነፃነታችንን ፡ በሙሉ ፡ እንድናገኝ ፡ ተወዳዳሪ ፡ የሌለውን ፡ የጦር ፡ ኃይሉን ፡ ዕርዳታ ፡ ሰጠን ። ይኸው ፡ እኔም ፡ መጣሁላችሁ ። የምሕረት ፡ ፊቱን ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ ስለ ፡ መለሰ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እናመሰግናለን ። ደግሞም ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ የወደቁትን ፡ ጀግኖቻችንንና ፡ የኢጣልያ ፡ ፋሽስት ፡ በጨካኝነት ፡ የፈጃቸውን ፡ በብዙ ፡ ሺህ ፡ የሚቆጠሩትን ፡ ኢትዮጵያዊያኖች ፡ እናመሰግናቸው ፡ እናስታውሳቸውም ። የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሹማምንትና ፡ አርበኞች ፡ የኢጣልያ ፡ መንግሥት ፡ በታላቂቱ ፡ ብሪታንያ ፡ ላይ ፡ ጦርነት ፡ ማድረግ ፡ ጀምሯል ። ይህንንም ፡ ያደረገበት ፡ ምክንያት ፡ አጥቂው ፡ ጠላታችን ፡ አገራችንን ፡ በወረረ ፡ ጊዜ ፡ ስንቅና ፡ መሣሪያ ፡ እንዳያገኝ ፡ ታላቂቱ ፡ ብሪታንያ ፡ ስለከለከለችና ፡ ደግሞም ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ሕግ ፡ እንዲከበር ፡ ስለተከራከረች ፡ ነው ። አሁንም ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ እንደሚገባችሁ ፡ ታውቃላችሁ ። ወደ ፡ ጠላት ፡ የገባችሁ ፡ ሁሉ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ አርበኞች ፡ ጋራ ፡ በቶሎ ፡ በመቀላቀል ፡ አገራችሁን ፡ እርዱ ፤ ባፋችሁም ፡ በጉልበታችሁም ፡ ቢሆን ፡ አንዳችሁም ፡ መሣሪያ ፡ አትሁኑ ፡ ጠላትን ፡ በምታገኙበት ፡ ሥፍራ ፡ ሁሉ ፡ አደጋ ፡ በመጣል ፡ መንገድ ፡ በመቁረጥ ፡ እንዳይላወስ ፡ አድርጋችሁ ፡ አድክሙት ፡ አድቅቁት ።



### የኢትዮጵያ ፡ ጀግኖችና ፡ አርበኞች ።

የያንዳንዳችሁን ፡ ሞያ ፡ አውቃለሁ ። ወደፊትም ፡ የምትሠሩትን ፡ የጀግንነት ፡ ሥራ ፡ ለማየት ፡ እናፍቃለሁ ። አርበኞች ፡ በጀግንነታችሁ ፡ ካህናቶችና ፡ ሽማግሌዎች ፡ ለሕዝባችን ፡ መልካም ፡ ምክር ፡ በመስጠት ፡ ገበሬዎች ፡ ነጋዴዎች ፡ ሌሎች ፡ ሠራተኞች ፡ ስለሀገራችሁ ፡ ጥቅም ፡ በሥራችሁ ፡ በርቱ ። ሁላችሁም ፡ የድካማችሁን ፡ ዋጋ ፡ ታገኛላችሁ ።

የሐማሴን ፡ የአካለጉዛይ ፡ የሠራዬ ፡ የቤናዐምር ፡ ሕዝብ ፡ ከመረብ ፡ ወዲያ ፡ ወይም ፡ ወዲህ ፡ ያላችሁ ፡ ሁሉ ፡ ከወንድሞቻችሁ ፡ ከኢትዮጵያውያኖች ፡ ጋራ ፡ ተባበሩ ። ከእግንዲህ ፡ ወዲህ ፡ አንዳችሁም ፡ የኢጣልያ ፡ መሣሪያ ፡ አትሁኑ ። ኢትዮጵያን ፡ እናታችሁንና ፡ ወዳጆቻችንን ፡ እንግሊዞችን ፡ አትውጉ ። የልባችሁን ፡ ምኞት ፡ አውቀዋለሁ ። ይኸውም ፡ የእኔና ፡ የመላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ምኞት ፡ ነው ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በጦርነት ፡ ሥቃዩን ፡ አብራችሁ ፡ እንደምትካፈሉ ፡ እንደዚሁም ፡ በሰላም ፡ ጊዜ ፡ በመንግሥታት ፡ ማኅበርና ፡ ወዳጆችን ፡ በሆኑ ፡ መንግሥታቶች ፡ በተለይም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ በተሳሰርነው ፡ በታላቋ ፡ ብሪታንያ ፡ መንግሥት ፡ ዕርዳታ ፡ አገራችንን ፡ በማደስና ፡ በማሠልጠን ፡ የሚገኘውን ፡ ፍሬና ፡ ደስታ ፡ ተካፋዮች ፡ ትሆናላችሁ ። ስለዚህ ፡ የመንግሥታችንን ፡ ሥራ ፡ አሻሽለን ፡ ፍጹም ፡ እናደርገዋለን ፡ የአገር ፡ አስተዳደር ፡ በአዲሱ ፡ ሥልጣኔ ፡ ይለወጣል ። ከሌሎችም ፡ ሕዝቦች ፡ ጋራ ፡ ያለንን ፡ መልካም ፡ መገናኛ ፡ እናጠብቀዋለን ። ንግድ ፡ እርሻ ፡ ትምህርት ፡ እንዲስፋፋ ፡ እናደርጋለን ። ነፃና ፡ ሀብታም ፡ በሆነች ፡ ባንዲት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ነፃነት ፡ ትክክልነት ፡ አንድነትና ፡ ዕውቀት ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፡ ሆናችሁ ፡ እንድትኖሩባት ፡ እንፈልጋለን ፤ ይህም ፡ የኢትዮጵያ ፡ መልካም ፡ ዕድል ፡ ጀግኖች ፡ በሆኑ ፡ ልጆችዋ ፡ እጅ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ትልቁም ፡ ትንሹም ፡ ልጁም ፡ አጥቂውም ፡ ጠላታችንን ፡ በቆራጥና ፡ በተባበረ ፡ ልብ ፡ ወግተን ፡ ከአገራችን ፡ ሥሩን ፡ ለመንቀል ፡ ዋና ፡ ሥራችን ፡ ይሁን ። የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ታላቂቱ ፡ ብሪታንያ ፡ ስለምታደርግልን ፡ ዕርዳታ ፡ የተገባን ፡ ሆነን ፡ ለመገኘት ፡ እንወቅበት ፡ የጋራ ፡ ጠላት ፡ የሆነውን ፡ የኢጣልያ ፡ ጦር ፡ ለመደምሰስና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሙሉ ፡ ነፃነት ፡ መልሶ ፡ ለማቋቋም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንግሊዞች ፡ ከአገራችን ፡ የሚፈልጉብን ፡ ነገር ፡ የለም ። ስለዚህ ፡ በማናቸውም ፡ ቦታ ፡ ቢሆን ፡ የእንግሊዝን ፡ ጦር ፡ አለቆችና ፡ ወታደሮች ፡ ባገኛችሁ ፡ ጊዜ ፡

ነፃነትን ፡ ይዘውልን ፡ የመጡ ፡ መሆናቸውን ፡ ተረድታችሁ ፡ በወዳጅነት ፡ ተቀበሏቸው ። ለያንዳንዳችን ፡ የጦር ፡ ጓደኛና ፡ የተከበሩ ፡ እንግዶቻችን ፡ መሆናቸውን ፡ አትዘንጉ ።

ኢትዮጵያ ፡ በነፃነት ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ፤
ታላቂቱ ፡ ብሪታኒያ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ፤
ሐምሌ ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፱ ፡ ዓ ፡ ም

## የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ማኅተም ።

ኢትዮጵያ ፡ ታበጽሕ ፡ እደዊሃ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡
ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡
ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

## አ ዋ ጅ ።

ናይ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕዝቢ ፡ ሹማምንትን ፡ ሠራዊትን ፤

ብዝ ፡ ኀለፈ ፡ ሐሙሽተ ፡ ዓመት ፡ ውስጢ ፡ በጅግንነትን ፡ ተስፋ ፡ ብዘይሙቆራጽን ፡ ኩሉ ፡ ጊዜ ፡ ሐይኽሁም ፡ ከይትሰበረ ፡ አጥቃዒ ፡ ምስዝኹን ፡ ጸላኢናአና ፡ ተኸራኺርኩም ፡ ብምጽናዕኩም ፡ ነፃ ፡ ዝሁኑ ፡ ናይ ፡ ዓለም ፡ ሕዝቢ ፡ ኩሉም ፡ አድነቂም ፡ ፍቅሮምውን ፡ ሀቡኹም ፡ ዝበጽሕኩም ፡ ስቃይን ፡ መስዋዕትነትን ፤ ጅግንነትኩምን ፤ ተስፋኩምን ፡ ብኽንቱ ፡ አይቀረየን ።

እንካብ ፡ ሎሚ ፡ ጀሚሩ ፡ ናይ ፡ እንግሊዝ ፡ መንግሥቲ ፡ ሐርነትና ፡ በሙሉኡ ፡ መታንክንረክብ ፡ ተኸራኻሪ ፡ ዘይብሉ ፡ ናይ ፡ ጦር ፡ ኃይሉ ፡ እንዳእታ ፡ ሂቡና ፡ አሉ ።

እነሆ ፡ አነውን ፡ መጺአኩልኩም ፤

ናይ ፡ ምኅረት ፡ ገጽ ፡ ናባና ፡ ስለዝመለሰ ፡ ንእግዚአብሔር ፡ ነሙሰግን ፡ አብ ፡ ናይውግእ ፡ ሜዳ ፡ ዘወደቁ ፡ ጀጋኑናን ፡ ናይ ፡ ኢጣልያን ፡ ፋሽስት ፡ ብጭካኔ ፡ ዘጨረሰም ፡ በሽነት ፡ ዝቆጸሩ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ንመስግኖም ፡ ንዘክሮም ።

### ናይ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕዝቢ ፡ ሹማምንት ፡ ሠራዊትን ፤

ናይ ፡ ኢጣልያ ፡ መንግሥቲ ፡ ምስ ፡ እንግሊዝ ፡ ውግዕ ፡ ጀሚሩ ፡ አሎ ፤ ምሽንያተውን ፡ አጥቃዒ ፡ ጸላዒና ፡ ዓድና ፡ ብዝወረረ ፡ ጊዜ ፡



ስንቅን ፡ መሣሪያን ፡ ከይረክብ ፡ እንግሊዝ ፡ ስለዝኸልከሎን ፡ ናይ ፡ ዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ሕግ ፡ ንምኽባር ፡ ስለአትኸራኸረን ፡ እዩ ።

ሕጂ ፡ እንታይ ፡ ምግባር ፡ ከምዝግብኦኩም ፡ ትፈልኹ ፡ ኢሁም ፡ ናብ ፡ ጸላኢ ፡ ዝአትኩም ፡ ኰሎኹም ፡ ምስናይ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሠራዊት ፡ ብተሎ ፡ ተሐዊስኩም ፡ ንሐገርኩም ፡ ርድኡ ፤ ብስብከትም ፡ ወይ ፡ ብገልበትኩም ፡ እንካባኻትኩም ፡ ሐጂኹም ፡ ንጸላኢ ፡ መሳርሒ ፡ አይትኹኑ ፡ ጸላኢ ፡ ብትረኽቡሉ ፡ ብኹሎ ፡ ሥፍራ ፡ ሐደጋ ፡ ብምውዳት ፡ መንገዲ ፡ ብሙችራድ ፡ ከምዝይለወስ ፡ ገርኩም ፡ አድኩሙም ፡ አድትቱም ።

## ናይ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጀጋና ፡ አርበኞታት ።

ናይ ፡ ነፍሲወከፍ ፡ ሞያኹም ፡ እፈልጦ ፡ እዩ ፤ ንቅድሚትውን ፡ ናይ ፡ ጅግንነት ፡ ስራሕኩም ፡ ንምር ፡ አይ ፡ እናፍቅ ፤ ወተሃደር ፡ በጅግንነት ፤ ካህናት ፤ ሽማግሌታት ፡ ንሕዝብና ፡ ጽቡቅ ፡ ምኽሪ ፡ ብመሃብ ፡ ሐረስታይ ፡ ነጋዳይ ፡ ካልኦት ፡ ሠራሕተኛታትውን ፡ ስለሃገርኩም ፡ ጥቅሚ ፡ ብምሥራሕ ፡ በርትሁ ፤ ኩሉኽም ፡ ናይድሃም ፡ ዋጋ ፡ ክትረኽቡ ፡ ኢኽም ፤ ሃይ ፡ ሐማሴን ፤ አከለጉዛይ ፤ ስራዪ ፤ በኒዐምር ፤ ናይ ፡ ሐባብን ፡ መንሳዕን ፡ ሕዝቢ ፡ እንካብ ፡ መረብ ፡ ንገየው ፡ ወይ ፡ ንንጀው ፡ ዘለኹም ፡ ኩሉሁም ፡ ምስአሕዋትኩም ፡ ምስ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ተሐባበሩ ። ሐዲኹም ፡ ናይ ፡ ጣልያን ፡ መሳርሒ ፡ አይትሁኑ ፤ ወላዲትኩም ፡ ኢትዮጵያን ፡ ኢተወትሁም ፡ እንግሊዝን ፡ አይትውግእ ፤ ናይ ፡ ጣልያን ፡ መሳርሒ ፡ አይትኹኑ ፤ ወላዲትኩም ፡ ኢትዮጵያን ፡ ኢተወትሁም ፡ እንግሊዝን ፡ አይትውግ ፤ ናይ ፡ ልብሁም ፡ ትምኒት ፡ እፈልጦ ፡ እዩ ። ናተይን ፡ ናይ ፡ ሙሉ ፡ ሕዝቢ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ትምኒት ፡ እዩ ፤ ዕድልኩም ፡ ምስተ፡ ካልእ ፡ ናይ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕዝቢ ፡ ዕድል ፡ ዝተተሐሐዘ ፡ እዩ ፤ ናይ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕዝቢ ።

ናይ ፡ ጦርነት ፡ ስቃይ ፡ ሐቢርኩም ፡ ከምትካፋሉ ፡ ከምኢውን ፡ ብሰላም ፡ ጊዜ ፡ ብመንግሥት ፡ ማኅበርን ፡ ፈተውትና ፡ ብዝኹኑ ፡ እንግሥታትን ፡ ብተፈልዩ ፡ ድማ ፡ ብቃልኪዳን ፡ እተአሳስርናይ ፡ ናይ ፡ እንግሊዝ ፡ መንግሥቲ ፡ ግዝ ፡ አድና ፡ ብምሕዳስን ፡ ብምሥልጣንን ፡ ብዝርክብ ፡ ፍሬን ፡ ደስታን ፡ ተኻፈልቲ ፡ ክትኩኑ ፡ ኢኹም ፤ ስለዚ ፡ ናይ ፡ መንግሥትና ፡ ሥራህ ፡ አተሐያይሻና ፡ ኅድለት ፡ ዘይብሉ ፡ ክንገብሮ ፡ ኢና ፡ ሃይ ፡ ሐገር ፡ አተሐዳድራ ፡ ብሐዲሱ ፡ ሥልጣኔ ፡ ክልወጥ ፡ እዩ ፤ ምስካልእት ፡ ሕዝቢ ፡ ዘሎና ፡ መራኽቢ ፡ ከነጥብቆ ፡ ኢና ፤ ንገድ ፡ ማሕረስ ፡ ጥበብ ፡ ትምህርት ፡ ከምዝስፋሕ ፡ ክንገብር ፡ ኢና ፡ ነጻን ፡ ሃብታምን ፡ ብዝኩነት ፡ ሐንቲ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነፃነትን ፡ ተኸክልነትና ፡ ፍልጠትን ፡

ዘለዊ ፡ ሐደ ፡ ሕዝቢ ፡ ኩይን ፡ ኩም ፡ ብትንብሩ ፡ ድላይና ፡ እዩ ፡ ከምዚ ፡ ዘበለ ፡ ናይኢትዮጵያ ፡ ጽቡቅ ፡ ዕድል ፡ ጀጋኑ ፡ ብዝሁኑ ፡ ደቃኢድ ፡ እዩ ፡ ዘሎ ፡ ስለዚ ፡ ዓቢይን ፡ ንእሽቶይን ፡ ጉበዛዝትን ፡ ሽማግሌታትን ፡ ብሕቡር ፡ ልቢ ፡ ጸላኢና ፡ ወረእና ፡ እንካብ ፡ ዓድና ፡ ሰሩንምንቃል ፡ ዋና ፡ ሥራሕና ፡ ይሁን ።

## ናይ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕዝቢ ፤

ናይ ፡ ዓባይ ፡ ብሪታኒያ ፡ መንግሥቲ ፡ ስለዝግብረልና ፡ ሐንዝ ፡ አትገበአና ፡ ኩይና ፡ ንትምርኮብ ፡ ናፈለጠሉ ፡ ናይ ፡ ክልቲና ፡ ጸላኢ ፡ ዝኩነ ፡ ናይ ፡ ኢጣልያን ፡ ጦር ፡ ንምድምሳስን ፡ ናይ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሙሉእ፡ ነፃነት ፡ መሊሱ ፡ ንመሕዳልን ፡ እምበር ፡ እንግሊዝ ፡ እንካብ ፡ አድና ፡ ዝደልዩ ፡ ነገር ፡ ይብሉን ። ስለዝ ፡ አብዝ ፡ ኹነ ፡ ቦታ ፡ ናይ ፡ እንግሊዝ ፡ ጦር ፡ ወይ ፡ አሐሎቶ ፡ ብዝረኸብኩም ፡ ጊዜ ፡ ነፃነት ፡ ጠዘሙልና ፡ ዝመጸ ፡ ምኳኖም ፡ ተረዲእኹም ፡ በፍቅረ ፡ ተቀበልዎም ፡ ናይ ፡ ጦር ፡ መሐዙትና ፡ ዝትኽብሩ ፡ ኢጋይሽና ፡ ምኳኖም ፡ አይትዘንግዑ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በነፃነት ፡ ንዘለዓለም ፡ ትንበር ። ናይ ፡ እንግሊዝ ፡ መንግሥቲ ፡ ንዘለዓለም ፡ ይንበር ።

ሐምሌ ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፪ ፡ ዓ ፡ ም

## የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ማኅተም ።

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፤

ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፤

ይድረስ ፡ ለጐጃም ፡ ሕዝብ ፡ ሹማምንትና ፡ አርበኞች ፤ እንደምን ፡ ሰንብታችኋል ፡ እኛ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ደህና ፡ ነን ፤ እኛም ፡ እናንተም ፡ ባንድ ፡ ሐሳብ ፡ ስንጠባበቀው ፡ የነበረ ፡ ተስፋ ፡ ስለ ፡ ተፈጸመ ፡ ለሀገራችን ፡ አብቅቶን ፡ የምንናፍቀውን ፡ ደጉን ፡ ስመ ፡ ጥሩውን ፡ አርበኛውን ፡ ሕዝባችንን ፡ ልናያችሁ ፡ የምንችልበትና ፡ ከመካከላችሁ ፡ የምንገኝበት ፡ ሰዓት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ይኸው ፡ ደረሰ ። በጥቂት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ሁላችሁንም ፡ በደህና ፡ እንድናገኛችሁ ፡ ተስፋ ፡ አለን ፤ እስከዚያ ፡ ድረስ ፡ ጀግናውም ፤ ገበሬውም ፤ ካህናቱም ፡ ሽማግሌውም ፡ ትልቁም ፡ ትንሹም ፡ ጠላት ፡ የሚጠቃበትን ፡ አገር ፡ የማይረብበትን ፡ በርትታችሁ ፡ ስትሠሩ ፡ ቆዩን ፤ ሁላችሁንም ፡ በደህና ፡ ጠብቋችሁ ፡ እንዳያችሁ ፡ ፈቃዱ ፡ ይሁን ፡ አዋጅም ፡ ተልኮላችኋል ።

ሐምሌ ፡ ፲፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተጻፈ ።



## የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ማኅተም ።

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእም ፡ ነገደ ፡ ይሁዳ

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡

ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡

ይድረስ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሹማምንትና ፡ አርበኞች ፡ እንደምን፡ ሰንብታችኋል ፡ እኛ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ደህና ፡ ነን ፡ ተስፋችን ፡ ተፈጽሞልን ፡ ወደ ፡ ሀገራችን ፡ ስለተመለስን ፡ ኢትዮጵያን ፡ በሙሉ ፡ ነፃነት ፡ ለማውጣትና ፡ በጦርነት ፡ ለመረዳዳት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ከተጋባ ነው ፡ ከታላቁ ፡ ከእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ የኢትዮጵያን ፡ አርበኞች ፡ ለመርዳት ፡ የታዘዙትን ፡ የእንግሊዝን ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንዲገባና ፡ የምሥራቹንም ፡ እንዲነግራችሁ ፡ አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡ እንዲቀድም ፡ አዘነው ፡ መጥቷልና ፡ እርሱንም ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ያሉትን ፡ የእንግሊዝ ፡ መኳንንቶች ፡ ከተከታዮቻቸው ፡ ጋራ ፡ በመልካም ፡ እንድትቀበሉዋቸው ፤ ስለሥራውም ፡ ማናቸውም ፡ ችግር ፡ እንዳያገኘው ፡ በተቻላችሁ ፡ ሁሉ ፡ እየረዳችሁ፡በቶሎ ፡ እንድታስተላልፉት፡ አደራ ፡ እንላችኋለን ።

ሐምሌ ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተጻፈ ።

ጠላት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ እንዳለ ፡ ቀዳሚ ፡ መላክተኛ ፡ ሆኜ ፡ ስላክ ፡ ከግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ የተሰጠኝ ፡ የሥራ ፡ ማስታወሻ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ።

## ለአዛዥ ፡ ከበደ ፡ ማስታወሻ ።

፩ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ (ጐጃም) ፡ ለመሄድ ፡ ከኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ጋራ ፡ የመንገዱን ፡ ፕሮግራም ፡ ማቆም ፤

፪ ፡ በምታልፍበት ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ የጃንሆይን ፡ አዋጅ ፡ ማስነበብ ፡ ያልደረሰው ፡ እንዲደርሰው ፡ ማድረግ ፤

፫ ፡ ጃንሆይ ፡ መምጣታቸውንና ፡ ከእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ሙሉ ፡ ዕርዳታ ፡ ማግኘታቸውን ፡ መሣሪያው ፡ በወሰን ፡ ላይ ፡ መደራጀቱን ፡ ማስረዳት ፤

፬ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ምንም ፡ ኢትዮጵያን ፡ እንደማይፈልግ ፡ ማስረዳት ፤ ጃንሆይ ፡ የሚመጡት ፡ በሙሉ ፡ ያገራቸውንና ፡ የሕዝባቸውን ፡ ነፃነት ፡ ለማቆም ፡ መሆኑን ፡ ማስረዳት ፤

፭፡ ሕዝቡ ፡ ጃንሆይ ፡ እስኪደርሱ ፡ አንድነትና ፡ መተባበር ፡ እንዲያ ገኝ ፡ ምክር ፡ መስጠት ፤

፮ ፤ ጃንሆይ ፡ ለመቀመጥ ፡ የሚችሉበትን ፤ ለተከታዮ ፡ ስንቅ ፡ የማይቸግርበትን ፡ መሣሪያ ፡ ጥይት ፡ ገንዘብ ፡ ለማስቀመጥ ፡ የሚቻልበትን ፡ አገር ፡ መመርመር ፤ ይኸውም ፡ ለአውሮፕላን ፡ የሚያሰጋ ፡ እንዳይሆን ፤

፯ ፤ የሕዝቡን ፡ ሐሳብ ፡ በአገር ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ጉልበት ፡ ወደፊት ፡ ጠላትን ፡ ለመግፋት ፡ ለማድረግ ፡ የሚቻለውን ፡ የጦርነት ፡ አኳኋን ፡ መመርመርና ፡ ከነኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ እየተነጋገሩ ፡ ሐሳብን ፡ ጨምሮ ፡ መጻፍ ፤

፰፡ በየመንገዱ ፡ ፖስታ ፡ ተቀባይ ፡ መላክተኛ ፡ በመሳፈሪያ ፡ ወስኖ ፡ ማቆምና ፡ ካገር ፡ ሰውም ፡ ነዋሪ ፡ ሹማምንት ፡ ኃላፊ ፡ አድርጎ ፡ ወሬያቸውና ፤ የተደረገው ፤ የመንገድህ ፤ የዕለት ፡ የዕለት ፡ ማስታወሻ ፡ እየተጠቃለለ ፡ በየጊዜው ፡ እንዲያደርስን ። የወሬ ፡ ማጣት ፡ ነገር ፡ እዚህ ፡ ለሚቆረጠው ፡ አስቸጋሪ ፡ ነውና ፡ ደንበኛ ፡ ፖስተኛ ፡ በተቀባይ ፡ ለማቆም ፡ ብርቱ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ።

፱ ፤ ጐጃም ፡ ስትደርስ ፡ እንጊሊዝ ፡ ጊዮርጊስና ፡ መሥፍን ፡ በቶሎ ፡ እንዲመጡ ፤ (የምርኰኞቹ ፡ ወደዚህ ፡ መምጣት ፡ ምሥጢር ፡ እንዲሆን ፡ የእኛ ፡ ሰዎች ፡ ሳያውቁ ፡ ከኢጣልያኖች ፡ ሳይላላኩ ፡ አይቀርምና ፡ አደጋ ፡ እንዳያስጥሉባችሁ ፡ ለነደጃች ፡ መንገሻ ፡ ተጽፏል) ።

፲ ፤ አሁን ፡ ለጊዜው ፡ የታሰበው ፡ ለጃንሆይ ፡ መሣፈሪያ ፡ እንዲሆን ፡ ጐጃም ፡ ነው ፤ ሌላው ፡ አገር ፡ እንዳይቀናና ፡ በምታልፍበት ፡ አገር ፡ ይመጣሉን ፡ እንጂ ፡ ይህን ፡ እንዲታሰማ ። አንተም ፡ በጐጃም ፡ መደብህን ፡ ለማድረግ ፡ መታሰቡን ፡ አለመንገር ፤

፲፩ ፤ ከነፊታውራሪ ፡ ገረሱ ፡ ዱኪ ፤ ከነአበበ ፡ አረጋይ ፤ በተቻለህ ፡ በርትተህ ፡ በልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ በኩል ፡ መገናኛ ፡ አለ ፡ ስለተባለ ፡ ተላልከህ ፡ አዋጁንም ፡ የጃንሆይንም ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መግባት ፡ እንዲያውቁ ። ጃንሆይም ፡ የመጡት ፡ በሙሉ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ነፃ ፡ ለማውጣት ፡ መሆኑን ፡ ማስረዳት ። መላክተኞቻቸውንም ፡ እንዲልኩ ፡ መጠየቅ ፤

፲፪ ፤ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ዙሪያ ፡ ላሉ ፡ ጦረኞች ፡ መላክት ፡ እንዲደርሳቸውና ፡ ሰው ፡ ጐጃም ፡ ድረስ ፡ እንዲልኩ ፡ መላላክ ፤

፲፫ ፤ በምታልፉበት ፡ መንገድ ፡ የተገባው ፡ ታማኝ ፡ ጦረኛ ፡ ሲገኝ ፡ በጃንሆይ ፡ ስም ፡ ከተያዘው ፡ ጠመንጃ ፡ መሸለም ። ገንዘብም ፡ እንደትልቅነትና ፡ ትንሽነቱ ፡ እየመዘኑ ፡ መስጠት ፤



፲፬ ፡ እኛ ፡ ገብተን ፡ በመድፍና ፡ በአውሮፕላን ፡ ምሽጉ ፡ ሳይፈርስ ፡ በመምጣታችን ፡ ወሬ ፡ ስም ፡ ይዞ ፡ ለመቆየት ፡ በምሽግ ፡ እየገባ ፡ ጦረኞችን ፡ እንዳያልቅ ፡ መንገድ ፡ በመቁረጥ ፡ ዘወትር ፡ በማባረርና ፡ በመተንኰስ ፡ ጤና ፡ እንዲያሳጡት ፡ እረፍት ፡ እንዲነሱት ፡ ኑሮውን ፡ እንዲያስለቅት ፡ ማድረግ ፤

፲፭፡ በየጊዜው ፡ እየለቀቀ ፡ የሚተወውም ፡ ምሽግ ፡ ብዙ ፡ ስለሆነ ፡ አሁን ፡ የያዘውን ፡ በግምት ፡ በውስጡ ፡ ካለው ፡ ወታደር ፡ ቁጥር ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ ማስታወቅ ፤

፲፮ ፡ በሙሉ፡ መሣሪያ ፡ የጐደለውን ፤ መሣሪያ ፡ ኖሮት ፡ ጥይት ፡ የጐደለውን ፡ አገር፡ ከነመሣሪያው ፡ ዓይነት ፡ መርምሮ ፡ ማስታወቅ ፤

፲፯ ፤ ና ፡ ሲባል ፡ ወደ ፡ ወሰን ፡ መጥቶ ፡ መሣሪያ ፡ የሚወስድ ፡ በያለበት ፡ ተዘጋጅቶ ፡ እንዲጠብቅ ፤

፲፰፡ ለአውሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡ የሚመቹ ፡ ቦታዎች ፤

፲፱ ፤ ጃንሆይን ፡ ለመቀበል ፡ በድንገት ፡ የሚደርስ ፡ ወታደር ፡ የሚዘጋጅበትን ፡ ከጐጃሞች ፡ ጋራ ፡ መመካከርና ፡ ድረስ ፡ ሲባል ፡ እንዲመጣ ፡ የሚመጣበትንም ፡ በር ፡ ፕላን ፡ አድርጎ ፡ ወደዚህ ፡ መላክ ፤

## በጠቅላላም ፤

ሹማምንት ፤ ሕዝብ ፡ የሚፋቀርበትን ፤ ጦር ፡ ሳይጎዳ ፡ ጃንሆይ ፡ እስኪደርሱ ፡ ጠላት ፡ የሚጠቃበትን ፤ ጃንሆይ ፡ የሚገቡበትን ፡ መንገድ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በሙሉ ፡ ነፃነቷን ፡ የምታገኝ ፡ መሆኑዋን ፤ እነዚህን ፡ ፬ ፡ ነገሮች ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ በፊትህ ፡ እንደሚቀርበው ፡ አጋጣሚ ፡ እስፋፍቶ ፡ መሥራት ፡ ነው ።

ሐምሌ ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፪ ፡ ዓ ፡ ም ፤

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈውን ፡ የሥራ ፡ ማስታወሻ ፡ ተቀብዬ ፡ ጕዞዬን ፡ ቀጠልሁ ። ማስታወሻውን ፡ ካጠናሁት ፡ በኋላም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ደብዳቤ ፡ ለሥራው ፡ አፈጻጸም ፡ የሚጠቅም ፡ መስሎ ፡ ስለታየኝ ፡ ሐምሌ ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ዶካ ፡ ላይ ፡ ሳለሁ ፡ ጻፍሁ ።

ለግርማዊ ፡ ጌታዬ ፤

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፤

ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

መድኃኒ ፡ ዓለም ፡ ዕድሜ ፡ ከጤና ፡ አስተባብሮ ፡ ይስጥልኝ ፡ እያልሁ ፡ ባሪያዎ ፡ መሬት ፡ እስማለሁ ።

በተሰጠኝ ፡ የሥራ ፡ ማስታወሻ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ አነበብሁትና ፡ ነገሩንም ፡ የሚጠቅም ፡ ማድረግም ፡ የሚቻል ፡ ስለመሰለኝ ፡ በሸዋ ፡ ክፍልና ፡ በጋላ ፡ አገር ፡ ከመኳንንቶች ፡ ለመላላክ ፡ ስማቸውን ፡ ከዚህ ፡ ደብዳቤ ፡ ጋራ ፡ ልኬዋለሁና ፡ በየስማቸው ፡ ደብዳቤ ፡ ተጽፎ ፡ በገሥጋሽ ፡ ሰው ፡ እንዲላክልኝ ። በቃሉም ፡ ላይ ፡ ሌላው ፡ አጻጻፍ ፡ እንደሌላው ፡ ሁሉ ፡ ሆኖ ፡ ከአዛዥ ፡ ከበደ ፡ ጋራ ፡ እየተላላክህ ፡ ግንኙነት ፡ አድርግ ፡ ያለንበትን ፡ ሥፍራ ፡ እሱ ፡ ይነግርሃል ፡ እየተባለ ፡ እንዲጻፍ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ስለመሰለኝ ፡ አስታውሳለሁ ። ስማቸውንም ፡ ሳናውቀው ፡ ቀርተን ፡ ላልጻፍነው ፡ ለዚህ ፡ አገር ፡ ባላባቶችና ፡ መኳንንቶች ፡ እየተባለ ፡ እንዲጻፍ ፡ አስታውሳለሁ ።

ሐምሌ ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡
ፊርማ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ።

## የሰው ፡ ቁጥር ፡ ማመልከቻ ፡

፩ ፡ ለባላምባራስ ፡ አበበ ፡ አረጋይ ፡
፪ ፡ ለፊታውራሪ ፡ ዘውዱ ፡ አባኮራን ፡
፫ ፡ ለደጃዝማች ፡ አውራሪስና ፡ በጠቅላላው ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ ስማቸው ፡ ለታወቀው ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ አስፈላጊነቱ ።
፬ ፡ ለፊታውራሪ ፡ ገረሱ ፡ ዱኪ ፡
፭ ፡ ወላና ፡ (ወላኔ) ፡ ጩልያ ፡
፮ ፡ ቀኛዝማች ፡ ዱጋሳ ፡ ጉርሙ ፡ ትቤ ፡
፯ ፡ ቀኛዝማች ፡ ፌጢ ፡ ወለጋ ፡ ጉድሩ ፡
፰ ፡ ለቀኛዝማች ፡ በዛብህ ፡ ስለሺ ፡
፱ ፡ ልጅ ፡ ከበደ ፡ ብዙነሽ ፡
፲ ፡ ልጅ ፡ ገርቢ ፡ ቡልቶ ፡
፲፩ ፡ እኛ ፡ ለማናውቃቸው ፡ በግርማዊነታቸው ፡ ዘንድ ፡ የታወቁ ፡ ቢኖሩ ፡ በተረፈ ፡ ለአገር ፡ ባላባቶች ፡ እየተባለ ፡ እንዲጻፍ ።
፲፪ ፡ ስለ ፡ ነፃነታቸው ፡ ያልተከራከሩ ፡ ችግርና ፡ ጭንቀት ፡ ለጠላት ፡ ያስገባቸው ፡ ሰዎች ፡ ቢኖሩ ፡ መላላክ ፡ ደህና ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርምና ፡ ይታሰብበት ።

ሐምሌ ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻ ፡ ፴፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡

ምዕራፍ ፡ ፲፯

## ወደ ፡ ጐጃም ፡ ስለመጓዛችንና ፡ በጉዞው ፡ ላይ ፡ የነበር ነው ፡ ሰዎች ፡ ስራቆ ፡ ላይ ፡ ሳለን ፡ ስለላክሁት ፡ ራፖር ፡

በዚህ ፡ ጉዞ ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ ስማችን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ተጽፎአል ።

ኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡
ኰሎኔል ፡ ድሩ ፡ (ሐኪም)
ካፒቴን ፡ ካርችሌ ፡
የ፶ ፡ አለቃ ፡ ግሬይ ፡
ወታደር ፡ ዊልትም ፡
አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡
ልጅ ፡ መርዕድ ፡ መንገሻ ፡
አቶ ፡ ጌታሁን ፡ ተሰማ ፡
አቶ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ ሀብተማርያም ፡
አቶ ፡ አሰጋኸኝ ፡ አርአያ ፡
ልጅ ፡ ዘውዴ ፡ ሙላት ፡
አቶ ፡ ዓለሙ ፡ ኑርልኝ ፡ የጭነት ፡ ሠራተኞች ፡ ኃላፊ ፡

ከነዚህም ፡ ሌላ ፡ ሃምሳ ፡ ያህል ፡ ኢትዮጵያውያኖች ፡ የሥራ ፡ እረዳቶች ፡ ነበሩን ። ከገዳሪፍ ፡ ወደ ፡ ዶይካ ፡ ሂደን ፡ ጉዞዎችንን ፡ ቀጥለን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ስናመራና ፡ መንገድ ፡ ስንጀምር ፡ ኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ አንድ ፡ ጉልህ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ነገሩኝ ። ሲነግሩኝም ፡ ለርሳቸው ፡ እንደገባቸው ፡ የኔ ፡ አማካሪና ፡ ረዳት ፡ ሳይሆኑ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ መላክተኛ ፡ እንጂ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ አለመሆናቸውን ፡ የሚገልጽ ፡ ስለሆነ ፡ ማን ፡ እንደሆኑ ፡ ቶሎ ፡ ለማወቅ ፡ ቻልኩ ። የነገሩኝም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፈው ፡ ነው ።

«ሰማህ ፡ አዛዥ ፡ ከበደ» ፡ ብለው ፡ ስሜን ፡ ጠሩና ፡ «እኔ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ መላክተኛ ፡ ነኝ ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ዱሮ ፡ በማጂ ፡ አማካሪ» ፡ ሆኜ ፡ ሄጂ ፡ እንደነበርሁበት ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ አይደለሁምና ፡ ጉዳዩን ፡ ሁሉ ፡ በቀጥታ ፡ የምነጋገረው ፡ ከእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ የጦር ፡ አዛዦች ፡ ጋራ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ እንደአማካሪ ፡ አድርገህ ፡ እንዳትመለከተኝ ፡ ሲሉ ፡ ነገሩኝና ፡ አስጠነቀቁኝ ። ይህም ፡ ንግግራቸው ፡ በኛና ፡ በነርሱ ፡ ማለት ፡ በእንግሊዞች ፡ መሐከል ፡ ልዩነት ፡ መኖሩን ፡ ስለመራኝ ፡ ወዳጅና ፡ ረዳት ፡ ናቸው ፡ ብዬ ፡ የሚያቀርቡትን ፡

ሐሳብ ፡ ሁሉ ፡ ሳላስብበት ፡ ልቀበልና ፡ ልሠራበት ፡ ሕሊናዬ ፡ አልፈቀደልኝም ፡ ነበር ። የአመራሩ ፡ ፕላን ፡ ባንድ ፡ መስመር ፡ የምንጓዝ ፡ ጓደኛነታችን ፡ ቀርቶ ፡ የበላይነትንና ፡ የበታችነትን ፡ የሚመለከት ፡ ሐሳብ ፡ ለማሳየት ፡ ሆነ ። ስለዚህ ፡ ችግራችን ፡ ምንም ፡ በብዙው ፡ ነገሮች ፡ የማያለየን ፡ ሆኖ ፡ ባንድ ፡ ገበታ ፡ ብንቀመጥና ፡ ምግባችንንም ፡ አብረን ፡ ብንበላ ፡ ቅሉ ፡ በሥራው ፡ ረገድ ፡ የማንግባባ ፡ ሆነን ፡ ተራርቀን ፡ ስለ ፡ ነበር ፤ ከላይ ፡ በስም ፡ የተጠቀሱት ፡ እንግሊዛዊ ፡ የሚያቀርቧቸው ፡ ሐሳቦች ፡ ሁሉ ፡ መተባበርን ፡ የሚቀንሱ ፡ ስለነበሩ ፡ በሐሳብ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ እንለያይ ፡ ነበር ። በሐሳብ ፡ ከምንለያይባቸው ፡ ነገሮች ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ሁሉንም ፡ ዘርዝሬ ፡ ባልጽፈው ፡ ለተመልካች ፡ ሐሳብ ፡ መግለጫና ፡ ማስታወሻ ፡ እንዲሆን ፡ በጥቂቱ ፡ ገልጾ ፡ ለመጻፍ ፡ አስባለሁ ።



ከግራ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ኮሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡ ፊታውራሪ ፡ ወርቁ ፡ ስንቄ ፡ ከቀኝ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ የቆሙት ፡ አቶ ፡ ጌታሁን ፡ ተሰማ ።

በመጀመሪያ ፡ ጉዞዎችን ፡ የሱዳንን ፡ ወሰን ፡ አልፈን ፡ የመተማን ፡ በረሃ ፡ ጨርሰን ፡ አለፍንና ፡ ጣቁሳ ፡ ማዛት ፡ ሰራቆ ፡ እስክንደርስ ፡ አገሩ ፡ እልም ፡ ያለ ፡ በረሃ ፡ ጠፍ ፡ ሰው ፡ የሌለበት ፡ ነው ። ጉዞዎችንም ፡ ሌትም ፡ ቀንም ፡ ስለነበረ ፡ ሐሳባችን ፡ በረሃውን ፡ አቋርጦ ፡ ከጠላት ፡ ጠረፍ ፡ በር ፡ ጠባቂ ፡ ለማምለጥና ፡ ሰው ፡ ማለት ፡ አርበኛ ፡ በሚገኝበት ፡ አገር ፡ ለመድረስ ፡ ብቻ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ሐሳብ ፡ ጣልቃ ፡ ለማግባት ፡ አልተቻለም ፡ ነበር ።

ነገር ፡ ግን ፡ ሰራቆ ፡ ከተባለው ፡ ቀበሌ ፡ ስንደርስ ፡ ፊታውራሪ ፡ ወርቁ ፡ ስንቄ ፡ የተባሉ ፡ አርበኛ ፡ መጥተው ፡ ተገናኙተን ። ቋራ ፡ ላይ ፡



ስለነበረው ፡ የጠላት ፡ ምሽግ ፡ እንደምን ፡ መስበር ፡ እንደሚቻል ፡ ሐሳብ ፡ ለሐሳብ ፡ በመለዋወጥ ፡ ከተነጋገርን ፡ በኋላ ፡ ተካርቱም ፡ ስንነሳ ፡ ከተሰጠነው ፡ መስመር ፡ መውጣት ፡ ጀመርን ፤ ከኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ጋራ ፡ የሥራ ፡ ረዳት ፡ ሆነው ፡ የታዘዙትን ፡ ልጅ ፡ መርዕድ ፡ መንገሻን ፡ ኰሎኔል ፡ ድሩ ፡ ከተባሉት ፡ ሐኪም ፡ ጋራ ፡ ቋራ ፡ እንዲቀሩ ፡ አደረጉና ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ረዳት ፡ ሆነው ፡ እንዲሠሩ ፡ የታዘዙትን ፡ አቶ ፡ ጌታሁን ፡ ተሰማን ፡ ለሁላታችንም ፡ እረዳት ፡ ሆነው ፡ ይሥሩ ፡ ሲሉ ፡ ጠየቁ ። እኔም ፡ በማንኛውም ፡ በኩል ፡ ቢሆን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ አሰብኩና ፡ ተስማማሁ ።

## ሠራቆ ፡ ላይ ፡ ሳለን ፡ የላክሁት ፡ ራፖር ፤

ከገዳሪፍ ፡ እስከ ፡ ሰራቆ ፡ ባደረግነው ፡ ጉዞ ፡ የሥራችንን ፡ ዝርዝር ፡ በመግለጽ ፡ እኔና ፡ ልጅ ፡ መርዕድ ፡ መንገሻ ፡ ሰፊ ፡ ራፖር ፡ ጽፈን ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ላክን ፤ ራፖርቶቹም ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

ለግርማዊ ፡ ጌታዬ ፤
ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፤
ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ዕድሜ ፡ ከጤና ፡ አስተባብሮ ፡ ይስጥልኝ ፡ ብዬ ፡ ባሪያዎ ፡ የረገጡትን ፡ መሬት ፡ እስማለሁ ።

ከግርማዊነትዎ ፡ ታዝዤ ፡ ስለ ፡ መጣሁበት ፡ ጉዳይ ፡ ሰራቆ ፡ እስክንደርስ ፡ ያየሁትንና ፡ ማድረግ ፡ የሚያስፈልግ ፡ የመሰለኝን ፡ የሥራ ፡ ማመልከቻ ፡ ከዚህ ፡ ደብዳቤዬ ፡ ጋራ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ልከአለሁ ፤ አብረውኝ ፡ ያሉትም ፡ የሥራ ፡ ጓደኞቼ ፡ እየረዱኝ ፡ የግርማዊነትዎ ፡ አምላክ ፡ ጠብቆን ፡ እስከዚህ ፡ አገር ፡ ማስታወቂያው ፡ ላይ ፡ ካመለከትኩት ፡ ችግር ፡ በተቀር ፡ ያለምንም ፡ አደጋ ፡ በደህና ፡ ደርሰናል ። ወደፊትም ፡ ያለውንም ፡ የሥራ ፡ አኳኋን ፡ እንዳመለከትነው ፡ ሁሉ ፡ ጉዳዩ ፡ የተፈጸመ ፡ እንደሆነ ፡ መልክተኞችን ፡ እመንገድ ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ስለማያሰጋ ፡ በየጊዜው ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ እንዲደርስ ፡ አደርጋለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ የመንገዱ ፡ አኳኋን ፡ እንዳስታወስነው ፡ ዓይነት ፡ ሆኖ ፡ እስቸጋሪው ፡ ቦታ ፡ ካልተጠበቀ ፡ ለመልክተኛ ፡ ስለሚያሰጋ ፡ ጉዳዩ ፡ ሳይዘገይ ፡ አይቀርም ።

፩ኛ/ ይኸንን ፡ ማመልከቻ ፡ ይዞ ፡ የመጣው ፡ አቶ ፡ ፍቱይ ፡ ሐጎስ ፡ የሚባለው ፡ በቅንነት ፡ ካስቸጋሪ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ነውና ፡ ተልኮ ፡ ወደግርማዊነትዎ ፡ የመጣ ፤ መልክቱን ፡ ካደረሰ ፡ በኋላ ፤ ግርማዊነትዎ ፡ ደስ ፡

አስኝተውት ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ እንዲመጡልን ፡ ጽፈን ፡ ከነበረው ፡ ሰዎቻችን ፡ ጋራ ፡ በቶሎ ፡ እንዲላክልን ።

፪ኛ/ ኃይሌ ፡ የሚባለው ፡ መንገድ ፡ መሪ ፡ ለመልክተኞች ፡ ሁሉ ፡ መንገድ ፡ መሪና ፡ ጠባቂ ፡ እንዲሆን ፡ ተነጋግሬው ፡ አሥር ፡ ሰዎች ፡ እገዳሪፍ ፡ አሉኝና ፡ ለነዚያ ፡ ብረትና ፡ ቀለብ ፡ ካገኘሁ ፡ የታመነኩ ፡ አገልጋይ ፡ እሆናለሁ ፡ ስላለኝ ፡ ሰዎቹን ፡ አቅርቦ ፡ መሣሪያና ፡ ቀለብ ፡ ተሰጧቸው ፡ ሥራውን ፡ በቶሎ ፡ እንዲጀምሩ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ አሳስባለሁ ።

ነሐሴ ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡
ያለሐኬት ፡ ባሪያዎ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

## ማመልከቻ ፡

ለግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

ሐምሌ ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከሌሊቱ ፡ በ፬ ፡ ሰዓት ፡ ገዳሪፍ ፡ ገባን ። ጠዋት ፡ ሐምሌ ፡ ፳፮ ፡ ቀን ፡ ኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ሚጀር ፡ ቢንቲክ ፡ ሚጀር ፡ ዋትና ፡ አቶ ፡ ሎሬንሶ ፡ ሆነን ፡ ስለመንገዳችንና ፡ ስለሥራችን ፡ በጠቅላላው ፡ ተነጋገርን ። መንገዳችን ፡ መተማን ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ሸንፋን ፡ ወንዝ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ትተን ፡ መሐሉን ፡ ወደ ፡ ማኅበረ ፡ ሥላሴ ፡ ለመውጣትና ፡ በሰራቆ ፡ አድርገን ፡ እጎጃም ፡ ለመዝለቅ ፡ ተነጋግረን ፡ ከቆረጥን ፡ በኋላ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ዘበኛ ፡ ሆነው ፡ የሚሸኙ ፡ ሰዎች ፡ ከኢትዮጵያ ፡ እንዲመጡ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ነፃነት ፡ ያንድነትና ፡ የመተባበር ፡ ኰሚቴ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤትን ፡ ጠይቀው ፡ ስለነበረ ፡ ኰሚቴው ፡ ግራዝማች ፡ ረዳንና ፡ ልጅ ፡ ወንድማገኘሁን ፡ ጠይቋቸው ፡ ለዚሁ ፡ ሥራ ፡ ስለመጡ ፡ በእንዴት ፡ ያለ ፡ አኳኋን ፡ እንዲሸኙ ፡ ተጠይቀው ፡ በሚቻለን ፡ ጉልበትና ፡ ባለን ፡ እውቀታችን ፡ ሁሉ ፡ እንረዳለን ፡ ብለው ፡ ተስፋ ፡ ሰጡን ። ለኢትዮጵያ ፡ ነፃነት ፡ ያንድነትና ፡ የመተባበር ፡ ኰሚቴ ፡ ለዚሁ ፡ ሥራ ፡ ቀኛዝማች ፡ ወርቁንም ፡ እርዳታ ፡ ጠይቆ ፡ ስለነበረና ፡ ቀኛዝማች ፡ ወርቁ ፡ ቋራ ፡ ያለውን ፡ የጠላት ፡ ምሽግ ፡ ለመከበብ ፡ ወራቸውን ፡ አስከትተው ፡ ወደ ፡ ቋራ ፡ ስለ ፡ ሄዱና ፡ ሳይደርሱ ፡ ስለቀሩ ፡ ሰው ፡ እንዳያንስ ፡ በማለት ፡ ከጫቆ ፡ ባሻ ፡ አድጎ ፡ ዘለቀ ፡ እንዲረዳን ፡ ተጠይቆ ፡ ፲፪ ፡ ራሱን ፡ መጥቶ ፡ ነበርና ፡ እርሱም ፡ እንደዚሁ ፡ ተስፋ ፡ ሰጠን ።

ግራዝማች ፡ ረዳ ፡ ተሰማ ፡ ልጅ ፡ ወንድማገኘሁ ፡ የሻንውና ፡ ባሻ ፡ አድጎ ፡ ዘለቀ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ እንደተጻፈው ፡ የግርማዊነትዎን ፡ እርዳታ፡ ከተቀበሉ ፡ በኋላ ፡ ኰራኘፉብ ፡ ወጥተው ፡ እኛን ፡ እንዲጠብቁን ፡ ተደረገ ።



ግራዝማች ፡ ረዳ ፡ ተሰማ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ዲሞትፎር ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ማርቴን ፡ ከሠላሳ ፡ ሺህ ፡ ጥይት ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ ተቀበሉ ፤

ሁሉንም ፡ የሚያነሱበት ፡ በቂ ፡ ከብት ፡ ስላልነበራቸውና ፡ በጉዝ ፡ ብዛት ፡ ምክንያት ፡ እኛን ፡ ለመሸኘት ፡ ችግር ፡ እንዳይሆን ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ዲሞትፎርና ፡ ሠላሳ ፡ ማርቴን ፡ ሰው ፡ ልከው ፡ ሊያስወስዱ ፡ ትተዋል ።

ልጅ ፡ ወንድማገኘሁ ፡ አምሳ ፡ ዲሞትፎር ፡ ሃምሳ ፡ ማርቲን ፡ ከአሥር ፡ ሺህ ፡ ጥይት ፡ ጋራና ፡ ሶስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ተቀብለዋል ።

ባሻ ፡ አድጎ ፡ ዘለቀ ፡ ባንድ ፡ ክፍል ፡ በጫቆ ፡ ደጃዝማች ፡ ተብለው ፡ እባት ፡ በሆኑት ፡ ባቶ ፡ ደመር ፡ ፈለቀ ፡ ውስጥ ፡ ስለሆነ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ የመሣሪያ ፡ ዕርዳታ ፡ ባቶ ፡ ደመር ፡ ፈለቀ ፡ በኩል ፡ ደርሶት ፡ ነበርና ፡ ስላገለግሎት ፡ እንዲቀጠርለት ፡ ተብሎ ፡ አምስት ፡ ዲሞትፎር ፡ ካንድ ፡ ሺህ ፡ ጥይት ፡ ጋራ ፡ ተቀብሏል ።

የሁሉም ፡ ከገዳሪፍ ፡ እስከ ፡ ዶካ ፡ ድረስ ፡ በካሚዮን ፡ ከዶካ ፡ እስከ ፡ ኰራኘፉብ ፡ ድረስ ፡ በግመል ፡ እንዲሄድላቸው ፡ ተደረገ ፤



አቶ ፡ አማኑኤል ፡ መንገሻ ፡

አቶ ፡ አማኑኤል ፡ መንገሻም ፡ እንደ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ትእዛዝ ፡ ወደ ፡ ቤጌምድር ፡ ሄዶ ፡ የሚሠራውን ፡ ሥራና ፡ ከግርማዊነትዎና ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ የሚያደርግበትን ፡ አጭር ፡ መንገድ ፡ በየመንገዱ ፡

እየመረመረ ፡ እንዲሄድ ፡ ተነጋግረን ፡ ጨርሰናል ። እርሱም ፡ በግራዝማች ፡ ረዳ ፡ አገር ፡ በዳባ ፡ አድርጎ ፡ ዳዋን ፡ መረባንና ፡ ወገራን ፡ አልፎ ፡ በላሳ ፡ እንዲገባ ፡ ተነጋግረናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ያጠረ ፡ መንገድ ፡ ያገኝ ፡ እንደሆን ፡ ይለውጣል ፡ እንደደረሰም ፡ ከሁሉ ፡ በፊት ፡ አስቀድሞ ፡ በፊታውራሪ ፡ አስፋው ፡ ቦጋለ ፡ ሞት ፡ ምክንያት ፡ ለጠላት ፡ ለማመን ፡ ያወላውላል ፡ የተባለውን ፡ ሕዝብ ፡ ለማጽናናትና ፡ አርበኛው ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ያፈሰሰው ፡ ደም ፡ በከንቱ ፡ አለመቅረቱንና ፡ ግርማዊንትዎ ፡ ሕዝብዎን ፡ ከጠላት ፡ ቀምበር ፡ ነፃ ፡ ለማውጣት ፡ ወደ ፡ ኢውሮፓ ፡ የሄዱበት ፡ ጉዳይ ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ መድረሱን ፡ አስረድቶ ፡ ወደጠላት ፡ እንዳይገባ ፡ ለማድረግ ፡ እንዲሠራ ፡ ተነጋግረናል ።

ሐምሌ ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ ከገዳሪፍ ፡ በካሚዮን ፡ ተነሳን ። በመንገድ ፡ ብርቱ ፡ ዝናብ ፡ ስለዘነበብንና ፡ መንገዱ ፡ ጭቃ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ዶይካ ፡ ሳንገባ ፡ እመንገድ ፡ አደረን ፡ ሐምሌ ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ከጠዋቱ ፡ በ፩ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ዶይካ ፡ ገባን ። እዚያም ፡ ስንቅና ፡ መጓሪያ ፡ ያልተቀበሉ ፡ እስኪቀበሉና ፡ ኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ሥራ ፡ በዝቶባቸው ፡ በሁለተኛው ፡ ቀን ፡ ለመድረስ ፡ ገዳሪፍ ፡ ቀርተው ፡ ነበርና ፡ እርሳቸው ፡ እስኪመጡ ፡ ድረስ ፡ ዶይካ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አደርን ።

ሐምሌ ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ከእኩለ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ከዶይካ ፡ ተነሳን ፤ ስንነሳም ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ ከተነሱት ፡ ከአምስቱ ፡ እንግዶቻችንና ፡ ከአምሳ ፡ ሰዎች ፡ በስተቀር ፡ ዘበኛ ፡ የሆነው ፡ እስከ ፡ ድምበር ፡ ድረስ ፡ የሸኙን ፡ ፳፬ ፡ የሱዳን ፡ ፈረስ ፡ ዘበኞችና ፡ በጭነት ፡ የረዱን ፡ ፲፱ ፡ ጀሌ ፡ ሱዳኖች ፡ አብረውን ፡ ነበሩ ። ከብቶቹ ፡ እንደተጫኑ ፡ ፺፫ ፡ በቅሎችና ፡ ፴፬ ፡ አህዮች ፡ ነበሩ ፡ ከዶይካ ፡ ስንነሳ ፤ ለምናልባት ፡ ኢጣልያን ፡ ወሬ ፡ ሰምቶ ፡ በአውሮፕላን ፡ እንዳይከታተለንና ፡ የምንሄድበትንም ፡ መንገድ ፡ እንዳያውቅ ፡ በማለት ፡ ወደ ፡ ገለባት ፡ የሚሄደውን ፡ የካሚዮን ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ትተን ፡ በጀንግ ፡ ወደ ፡ አርማጭሆ ፡ የሚወስደውን ፡ መንገድ ፡ ይዘን ፡ ሄድን ። ማታ ፡ በ፩ ፡ ሰዓት ፡ ሰሪፍ ፡ አልአህመር ፡ የምትባለው ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ሰፍረን ፡ አደርን ።

ነሐሴ ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ጠዋት ፡ ከሰሪፍ ፡ አልአህመር ፡ ተነስተን ፡ በ፫ ፡ ሰዓት ፡ ከሩብ ፡ መሐላ ፡ ላይ ፡ ሰፍረን ፡ ፫ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ካረፍን ፡ በኋላ ፡ በ፱ ፡ ሰዓት ፡ ሩብ ፡ ጉዳይ ፡ ከመሐላ ፡ ተነስተን ፡ ወዲያ ፡ ሰፍረን ፡ አደርን ።

ነሐሴ ፡ ፪ ፡ ቀን ፡ ከወዲያ ፡ ተነስተን ፡ ወድክላቢ ፡ አደርን ፤

ነሐሴ ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ በማለዳ ፡ ከወድክላቢ ፡ ነጋድራስ ፡ በለጠ ፡ ከኩራጕሩብ ፡ እነ ፡ ግራዝማች ፡ ረዳ ፡ ዘንድ ፡ ተላከ ፤ የተላከውም ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ የምንገናኝበትን ፡ ቀንና ፡ ቦታ ፡ ወስነን ፡ ስላልተነጋገርን ፡ ነጋድ



ራስ ፡ በለጠ ፡ እስከ ፡ ባንደጊ ፡ ድረስ ፡ ይዘዋቸው ፡ እንዲሄዱና ፡ ከዚያ ፡ ላይ ፡ እንዲጠብቁንና ፡ ወይም ፡ እንድንገናኝ ፡ ነው ። የዚያኑ ፡ ዕለት ፡ ከወድክላቢ ፡ ተነስተን ፡ ኢመከራይት ፡ የምትባለውን ፡ መንደር ፡ አልፈን ፡ በቀኝ ፡ ትተነው ፡ የነበረው ፡ የዶይካ ፡ ገለባትን ፡ የካሚዮን ፡ መንገድ ፡ ቆርጠን ፡ ግሬጋና ፡ በምትባለው ፡ መንደር ፡ አጠገብ ፡ ሰፍረን ፡ አደርን ።

ነሐሴ ፡ ፬ ፡ ቀን ፡ ከግሬጋና ፡ ተነስተን ፡ ኩርኔኪላና ፡ ወድላቅባሽ ፡ የሚባሉትን ፡ መንደሮች ፡ አልፈን ፡ ስኤፋ ፡ ሰፍረን ፡ አደርን ። ከስኤፋ ፡ ማታ ፡ ወሎና ፡ ወንዝ ፡ ላይ ፡ ከነግራዝማች ፡ ረዳ ፡ እንድንገናኝ ፡ መልክተኛ ፡ ወደ ፡ ባንደጊ ፡ ላክን ፤

ነሐሴ ፡ ፭ ፡ ቀን ፡ ጠዋት ፡ ከስኤፋ ፡ ተነስተን ፡ ሎሚና ፡ አደርን ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ የነግራዝማች ፡ ረዳ ፡ ሰፈር ፡ ጥቂት ፡ ራቅ ፡ ያለ ፡ ቢሆን ፤ ማታውኑ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ተገናኝተን ፡ ወደፊት ፡ ስለ ፡ ምንቀጥለው ፡ መንገድ ፡ ተነጋግረን ፡ ለጠዋት ፡ ለመነሳት ፡ ቆረጥን ፤ ነጋድራስ ፡ በለጠ ፡ ወደ ፡ ኩራጕሩብ ፡ ከተላከ ፡ በኋላና ፡ እነ ፡ ግራዝማች ፡ ረዳ ፡ ወደ ፡ ባንደጊ ፡ ለመሄድ ፡ ሲሰናዱ ፡ ወሬ ፡ ባክኗልና ፡ ብለው ፡ በገለባት ፡ ያሉ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ለኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ስላስታወቁ ፡ ለምናልባት ፡ አደጋ ፡ እንዳይደርስብን ፡ በማለት ፡ የነጋዴውንና ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ልጅ ፡ ወንድማገኘሁ ፡ የወረዱበትን ፡ መንገድ ፡ ትተን ፡ በደህና ፡ መሪ ፡ ባቅጣጫው ፡ ዱር ፡ እየጣስን ፡ ለመሄድ ፡ ቆረጥን ፤ ዳግም ፡ ዱር ፡ እየጣስን ፡ ለመሄድ ፡ ግዴታ ፡ የሆነብን ፡ ምክንያት ፤ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ባሻ ፡ ተሾመ ፡ የሚባለውን ፡ የቀኛዝማች ፡ ወርቁን ፡ መልክተኛ ፡ ሲሆን ፡ ቀኛዝማች ፡ ወርቁ ፡ ራሳቸው ፡ ሳይሆን ፡ በእንደራሴ ፡ አድርገው ፡ ሸኙ ፡ ዘበኞች ፡ እስከ ፡ ጠረፍ ፡ ድረስ ፡ እንዲልኩልን ፡ አቶ ፡ ጌታሁን ፡ ተሰማ ፡ ከኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ጋራ ፡ ተማክሮ ፡ በኮሚቴው ፡ ስም ፡ ደብዳቤ ፡ ሰጥቶት ፡ በሐምሌ ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ልኰት ፡ ነበርና ፡ ሰራቆ ፡ ሳይደርስ ፡ በመንገድ ፡ ሩቂ ፡ ማረጃ ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ስለ ፡ ደረሰበትና ፡ ከኩራጕሩብ ፡ እንዲሸኙት ፡ ይዟቸው ፡ ከሄዱት ፡ ፱ ፡ ሰዎች ፡ ውስጥ ፡ ሶስቱ ፡ አምልጠው ፡ ኩራጕሩብ ፡ ስለ ፡ ገቡና ፡ ወሬያቸውን ፡ ከኩራጕሩብ ፡ ያሉ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ስላስታወቁን ፡ ነው ፤

ነሐሴ ፡ ፮ ፡ ቀን ፡ ከሌሊቱ ፡ በ፲፩ ፡ ሰዓት ፡ መንገድ ፡ መሪና ፡ የፊት ፡ ዘበኛ ፡ ልጅ ፡ ወንድማገኘሁን ፡ ከደጃን ፡ ግራዝማች ፡ ረዳን ፡ አድርገን ፡ ከሎሚና ፡ ተነሳን ፤ በዝናብና ፡ በጭቃ ፤ ዱር ፡ በመጣስ ፡ አቀበት ፡ በመውጣትና ፡ ቁልቁለት ፡ በመውረድ ፡ ሰውም ፡ ከብትም ፡ ስለ ፡ ደከመብን ፡ ድምበር ፡ አልፈን ፡ የመተማ ፡ ጉባን ፡ የካሚዮን ፡ መንገድ ፡ ሳናልፍ ፡ እበረሃ ፡ ላይ ፡ አረፍን ፡ ሳናርፍ ፡ በፊት ፡ ከፊት ፡ የልጅ ፡ ወንድማገኘሁ ፡

ሰዎች ፡ ከሁለት ፡ ጉሙሮች ፡ (ሻንቅሎች) ፡ ጋራ ፡ ድንገት ፡ ተገናኝተው ፡ ሻንቅሎቹ ፡ መጥረቢያ ፡ የማር ፡ ቅልና ፡ ፉጋ ፡ ጥለው ፡ ስለሸሹ ፡ ለምናልባት ፡ ሰላዮች ፡ ይሆኑና ፡ አደጋ ፡ ያስጥሉብናል ፡ በማለት ፡ እዚህ ፡ ሳናድር ፡ የካሚዮኑን ፡ መንገድ ፡ ቆርጠን ፡ እንደር ፡ የሚል ፡ የሁሉም ፡ ሐሳብ ፡ ስለሆነ ፡ አርፈን ፡ ከብቶቹ ፡ ውኃ ፡ ከጠጡና ፡ ዝናብ ፡ ካባራ ፡ በኋላ ፡ ተነሳን ። እዚሁ ፡ አረፍንበት ፡ በረሃ ፡ ላይ ፡ ቢምባሺ ፡ ቴሲንገር ፡ የሚባሉ ፡ የኩራኅኑብ ፡ የእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ ወታደር ፡ አለቃ ፡ ከጥቂት ፡ ወታደሮች ፡ ጋራ ፡ ዱካችንን ፡ ተከታትለው ፡ በማስጋሴ ፡ ደርሰው ፡ ተገናኝተውናል ። የካሚዮኑን ፡ መንገድ ፡ ልንደርስ ፡ አቅራቢያ ፡ የብዙ ፡ ሰውና ፡ የከብት ፡ ዱካ ፡ ከመተማ ፡ ወደ ፡ ፋቂ ፡ ማረጃ ፡ ያለፈ ፡ አየን ፡ ዱካውም ፡ አዲስ ፡ ስለነበረ ፡ የዚያኑ ፡ ዕለት ፡ ወይም ፡ ከአንድ ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ ያለፈ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ገመትን ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የኛ ፡ ወሬ ፡ ስለ ፡ ተሰማ ፡ አልፎ ፡ በር ፡ ይዞ ፡ ፋቂ ፡ ማረጃ ፡ ላይ ፡ ሊጠብቀን ፡ ይሆናል ፡ መንገድ ፡ ትተን ፡ ዱር ፡ እየጣስን ፡ እንሄዳለን ፡ ብለን ፡ የተነጋገርነውን ፡ ሐሳብ ፡ አጽድቅን ፡ የካሚዮኑም ፡ መንገድ ፡ ስንሻገር ፡ እኛን ፡ ለመሸኘት ፡ ከመጡት ፡ ከፈረሰ ፡ ዘበኞች ፡ አሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ለሁለት ፡ ተከፍለው ፡ ጓዙ ፡ ሁሉ ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ መንገዱን ፡ እንዲጠብቁ ፡ ኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ አዘዙዋቸው ። እንደዚህ ፡ ሆኖ ፡ መንገዱን ፡ ካለፍን ፡ በኋላ ፡ በ፲፪ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ዳስ ፡ ላይ ፡ ሰፍረን ፡ አደርን ። ወደ ፡ ፋቂ ፡ ማረጃ ፡ የሚሄደው ፡ የጥንት ፡ ነጋዴ ፡ ጎዳና ፡ በዳስ ፡ ወንዝ ፡ በኩል ፡ የሚያልፍ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ አሁንም ፡ በመንገዱ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ዱካ ፡ አየን ፡ A. O. (አፍሪካ ፡ ኦሪየንታሌ) ፡ የተጻፈበት ፡ የኢጣልያን ፡ የሲጃራ ፡ ሳጥን ፡ እጮቃ ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ አገኘን ፡ ስለዚህ ፡ ተጠንቅቀን ፡ መስፈር ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ተረዳን ። አሰፋፈራችንም ፡ ሁልጊዜ ፡ እኛ ፡ ከመሐል ፡ ስንሆን ፡ ልጅ ፡ ወንድማገኘሁ ፡ ከነሰዎቻቸው ፡ የፊት ፡ ዘበኛ ፡ ግራዝማች ፡ ረዳ ፡ ከደጀን ፡ ሆነን ፡ ነበር ።

ነሐሴ ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ በማለዳ ፡ ከዳስ ፡ ተነሳን ። ጎዳናውን ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ትተን ፡ ዱር ፡ እየጣስን ፡ መንገዳችንን ፡ ቀጠልን ። መንገዱም ፡ መረሬና ፡ ዋልካ ፡ ብዙ ፡ ደንና ፡ ጥሻ ፡ የመላበት ፡ ስለነበረ ፡ ከብትም ፡ ሰውም ፡ በጣም ፡ ደከመ ። ዘበኛ ፡ ሆነውና ፡ በጭነት ፡ እየረዱን ፡ የሸኙን ፡ የሱዳን ፡ ሰዎች ፡ ከዳስ ፡ ተመልሰዋል ። የዚያን ፡ ለት ፡ ጂምበርጊ ፡ የምትባለውን ፡ ሥፍራ ፡ ተጠግተን ፡ አደርን ።

ነሐሴ ፡ ፰ ፡ ቀን ፡ ከጂምበርጊ ፡ ተነስተን ፡ መረውድባ ፡ አደርን ፡

ነሐሴ ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ ከመረውድባ ፡ ተነስተን ፡ ሌንጫ ፡ የሚባለውን ፡ ወንዝ ፡ ከተሻገርን ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ማኅበረ ፡ ሥላሴ ፡ የሚሄደውን ፡ የነጋዴ ፡ ጐዳና ፡ አገኘን ፡ እዚህም ፡ ጎዳና ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ሰውና ፡ ከብት ፡ የተመላለሰበት ፡ ዱካ ፡ አገኘን ፡ ጎሾ ፡ አምባ ፡ ስንደርስ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ሰፍሮበት ፡ የነበረ ፡ ሰፈር ፡ አየን ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ጦር ፡ ሰፍሮበት ፡ እንደነበር ፡ ምልክት ፡ ለማግኘት ፡ ዙረን ፡ አየን ፡ የኢጣልያን ፡ ምልክት ፡ አንድም ፡ አላገኘንም ። የተሠራው ፡ ዳስና ፡ ጎጆ ፡ ሁሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነጋዴ ፡ ወይም ፡ ጦር ፡ ሲሰፍር ፡ የሚሠራው ፡ ዓይነት ፡ ነበር ። ዳግም ፡ አንድ ፡ ፊያሽኮ ፡ ጠርሙስ ፡ ወድቆ ፡ አገኝተን ፡ ነበርና ፡ አንስተን ፡ ብናሸተው ፡ በቅመም ፡ የተሠራ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቅቤ ፡ ነበረበት ፡ የኢጣልያን ፡ ጦር ፡ ሰፍሮበት ፡ ቢሆን ፡ ኑሮ ፡ ሸራ ፡ የወታደር ፡ ድንኳን ፡ ይተከል ፡ ነበር ፡ ብዙም ፡ የምግብ ፡ ቆርቆሮ ፡ ተከፍቶ ፡ የተጣለ ፡ ይገኝ ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ማን ፡ ሰፍሮበት ፡ እንደነበረ ፡ ባናውቅ ፡ እንኳን ፡ የኢጣልያን ፡ ጦር ፡ እንዳልነበረ ፡ ለመገመት ፡ ቻልን ። እዚሁ ፡ እጐሽ ፡ አምባ ፡ ላይ ፡ መንገዱ ፡ ለሁለት ፡ ተከፍሎ ፡ አንዱ ፡ ወደ ፡ ሰራቆ ፡ አንዱ ፡ ወደ ፡ ማኅበረ ፡ ሥላሴ ፡ የሚሄድ ፡ ነበርና ፡ የሰራቆን ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ትተን ፡ ወደ ፡ ማኅበረ ፡ ሥላሴ ፡ የሚያወጣውን ፡ ይዘን ፡ ሄድን ። እምቡልቡል ፡ የሚባለው ፡ ወንዝ ፡ ላይ ፡ ሰፍረን ፡ አደርን ።

የብዙ ፡ ሰውና ፡ የከብት ፡ ዱካ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ስላጋጠመን ፡ ወደ ፡ ፊታችን ፡ ያሰጋን ፡ ይሆን ፡ በማለትና ፡ ከልጅ ፡ ወንድማገኘሁ ፡ አገር ፡ ከቻባ ፡ የሰው ፡ የከብት ፡ እርዳታ ፡ ጅራ ፡ ወንዝ ፡ ድረስ ፡ እንዲደርስልን ፡ አስቀድመን ፡ ሁለት ፡ መልክተኞች ፡ በማኅበረ ፡ ሥላሴ ፡ በኩል ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ ቻባ ፡ እንዲሄዱ ፡ ከመረውድባ ፡ ልከናል ። በእምቡልቡል ፡ ወንዝ ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ መላክተኛ ፡ ወደ ፡ ማኅበረ ፡ ሥላሴ ፡ ልከን ፡ ጠዋት ፡ ጉዋዙና ፡ የቀሩት ፡ እንግዶች ፡ ከግራዝማች ፡ ረዳ ፡ ጋራ ፡ መንገዳቸውን ፡ ሲቀጥሉ ፡ እኛ ፡ ልጅ ፡ ወንድማገኘሁን ፡ ይዘን ፡ ከኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ማኅበረ ፡ ሥላሴዎች ፡ ሄድን ፤ ከማኅበረ ፡ ሥላሴዎች ፡ የሻለቃ ፡ መስፍን ፡ ስለሺ ፡ ከብዙ ፡ የጐጃም ፡ ጦር ፡ ጋራ ፡ ብዙም ፡ ከብት ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ሱዳን ፡ መውረዳቸውን ፡ ሰማን ። ማኅበረ ፡ ሥላሴዎች ፡ በደህና ፡ ተቀበሉን ፤ የግርማዊነትዎንም ፡ ወሬ ፡ በመስማታቸው ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

መንኰሳት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ለመላክ ፡ ይቻላቸው ፡ እንደሆን ፡ ብጠይቅ ፡ እዚህ ፡ ለጊዜው ፡ ያሉት ፡ መነኮሳት ፡ ጥቂቶች ፡ ስለሆኑና ፡ የጊዜው ፡ አኳኋን ፡ እነዚህ ፡ ይታመናሉ ፡ ብለን ፡ ለመላክ ፡ ስለማይፈቅድልን ፡ አሁን ፡ አናገኝም ፡ ብለው ፡ መለሱልኝ ።

ነሐሴ ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ከግራዝማች ፡ ረዳና ፡ ከባሻ ፡ አድጎ ፡ ዘለቀ ፡ ጋራ ፡ በአምባር ፡ ውሀ ፡ ላይ ፡ ተለያየን ። ስንሰነባበትም ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ስም ፡ ለግራዝማች ፡ ረዳ ፡ ሰዎች ፡ ስላገለግሎታቸው ፡ አምሳ ፡ ብር ፡ ለፍሪዳ ፡ መግዣ ፡ ተሰጥቶዋቸዋል ።

ለባሻ ፡ አድጎ ፡ ዘለቀም ፡ እንደዚሁ ፡ ሠላሳ ፡ ብር ፡ ተሰጥቶታል ።

ሳንለያይ ፡ በፊት ፡ ግራዝማች ፡ ረዳ ፡ አገራቸው ፡ ሲገቡ ፡ ምን ፡ መሥራት ፡ እንደሚያስፈልጋቸው ፡ በሰፊው ፡ ተነጋግረናል ። የተነጋገር ነውም ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

ጥያቄ ፡ ለርዳታ ፡ በተጠየቁ ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጦር ፡ ለማስከተት ፡ ይችላሉ ፡ ብለን ፡ ብንጠይቃቸው ፤

መልስ፡ አሁን ፡ ከተቀበልኩት ፡ የመሣሪያ ፡ እርዳታ ፡ ጋራ ፡ ፳፻ ፡ ወታደር ፡ ለማስከተት ፡ እችላለሁ ፡ ብለው ፡ መለሱ ፤

ጥያቄ ፡ በዚሁ ፡ በ፳፻ ፡ ወታደር ፡ ከጭልጋ ፡ ወደ ፡ መተማ ፡ በሚሄደው ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ የኢጣልያን ፡ ጦር ፡ እንዳያልፍ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላሉ ፡ ወይ ፡ ብለን ፡ ብንጠይቃቸው ፤

መልስ፡ በዙሪያዬ ፡ ካሉት ፡ አርበኞች ፡ ጋራ ፡ እየተባበርኩ ፡ ለማገድ ፡ እችላለሁ ፤ እርዳታም ፡ ባላገኝ ፡ እንኳን ፡ ሥፍራው ፡ ለኛ ፡ የተመቸ ፡ ነውና ፡ ባለኝ ፡ ኃይልና ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ለማገድ ፡ እችላለሁ ፡ ብለው ፡ መለሱልን ፤

በጭልጋ ፡ ላይ ፡ ኢጣልያን ፡ ከሾማቸው ፡ ከፊታውራሪ ፡ ዓለማየሁ ፡ ጋራ ፡ እርቅ ፡ ለማድረግ ፡ ፈቃዳቸው ፡ እንደሆነና ፡ ፊታውራሪ ፡ ዓለማየሁ ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ ከሆነ ፡ ወይም ፡ ገለል ፡ ካለ ፡ የጭልጋ ፡ ሕዝብ ፡ ለኢጣልያን ፡ ረድቶ ፡ እኛን ፡ አይወጋኝም ፡ አሉ ፤ ፊታውራሪ ፡ ዓለማየሁም ፡ ወንድሜ ፡ ነውና ፡ በዘመድ ፡ ልታረቀው ፡ እሞክራለሁ ፤ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ጀምሬዋለሁ ፡ ብለው ፡ ነገሩን ፤

ጥያቄ ፤ የጭልጋ ፡ መተማን ፡ መንገድ ፡ ለማፍረስ ፡ ብንፈልግ ፡ የት ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ማፍረስ ፡ ይመቻል ፡ ብለን ፡ ብንጠይቃቸው ፤

መልስ፤ መንገዱ ፡ ለምናልባት ፡ ያስፈልገን ፡ ይሆናልና ፡ ባይፈርስ ፡ ይሻላል ፡ ብለው ፡ መለሱ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ለማፍረስ ፡ ከተፈለገ ፡ ዋሊ ፡ ደባ ፡ ገደል ፡ ነውና ፡ ዋሊ ፡ ደባ ፡ ላይ ፡ ለማፍረስ ፡ ይመቻል ፤ እንደዚሁ ፡ ከዘወሕቢ ፡ በታች ፡ ግመል ፡ መማለያም ፡ ላይ ፡ የተመቸ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ነገሩን ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ትእዛዝ ፡ እስኪመጣብኝ ፡ ድረስ ፡ መንገዱ ፡ እንዳይፈርስ ፡ እጠብቃለሁ ፡ ብለው ፡ አሉ ።

ጥያቄ ፤ መንገዱ ፡ ሳይፈርስ ፡ የኢጣልያንን ፡ ጦር ፡ ለማገድ ፡ ይችላሉ ፡ ወይ ፤ ብለን ፡ ብንጠይቃቸው ፤

መልስ፤ ስፍራው ፡ ለኛ ፡ የተመቸ ፡ ነውና ፡ በእግዚአብሐር ፡ ኃይል ፡ እችላለሁ ፤ ብለው ፡ መለሱልን ፤



ጥያቄ ፤ እንዴት ፡ አድርገው ፡ ነው ፡ የሚያግዱት ፡ ብንላቸው ፤

መልስ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የኛ ፡ ሰው ፡ ከጭልጋ ፡ ከተማ ፡ አይለይምና ፡ ሲነሳ ፡ መጥተው ፡ ያመለክቱናል ፤ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሳበስጊ ፡ ላይ ፡ ከዋሊ ፡ ደባ ፡ ዝቅ ፡ ብለን ፡ እንጥፊን ፡ (ተጠንቅቀን) ፡ እንጠብቀዋለን ፡ አሉ ። እርሱም ፡ ከንድ ፡ መንገድ ፡ በስተቀር ፡ ሌላ ፡ መውረጃ ፡ የለውም ፤ ብለው ፡ ነገሩን ፤

ጥያቄ ፤ በዙሪያዎ ፡ ያሉ ፡ አርበኞች ፡ በጠየቁ ፡ ጊዜ ፡ ለእርዳታ ፡ የሚደርሱልዎ ፡ እነማን ፡ እነማን ፡ ናቸው ፡ ብለን ፡ ብንጠይቃቸው ፤

መልስ፡ ከዳዋ ፡ ቀኛዝማች ፡ ከበደና ፡ ከጫቆ ፡ አቶ ፡ ይመር ፡ ፈለቀ ፡ ናቸው ፡ ብለው ፡ መለሱልን ፤

ከጭልጋ ፡ ወይም ፡ ከጎንደር ፡ ኢጣልያን ፡ ጦር ፡ ለመጫን ፡ በፈለገ ፡ ጊዜና ፡ ማንኛውም ፡ አስቀድሞ ፡ ጥንቃቄ ፡ ማድረግ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ወሬ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ በገላባት ፡ ያሉ ፡ የእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ አስቀድመው ፡ እንዲሰናዱ ፡ ወደኛ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ገለባት ፡ ላሉ ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ አርማጭሆ ፡ ለሚወጡ ፡ ለነሚጀር ፡ ቤንቲክ ፡ ከሁሉም ፡ ወደ ፡ ቀረባቸው ፡ ደብዳቤ ፡ እንዲጽፉ ፡ ነግረናቸው ፡ እሺ ፡ አደርጋለሁ ፡ ብለዋል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የቀራቸውን ፡ መሣሪያ ፡ ለማስነሳት ፡ ወደ ፡ ኩራገራብ ፡ ሰው ፡ በላኩ ፡ ጊዜ ፡ ፳ ፡ ሺህ ፡ የምንሽር ፡ ጥይትና ፡ ፱ ፡ ሺህ ፡ የእጅ ፡ ቦምብ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ እርዳታ ፡ እንዲጨመርላቸው ፡ መታዘዙን ፡ አስታውቀናቸዋል ።

ከግራዝማች ፡ ረዳ ፡ ጋራ ፡ ስንሰነባበት ፡ እነ ፡ የሻለቃ ፡ መስፍን ፡ ስለሺ ፡ ወደ ፡ ሱዳን ፡ ሲወርዱ ፡ ፋቂ ፡ ማረጃ ፡ አጠገብ ፡ ግራዊት ፡ በምትባለው ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ ከኢጣልያን ፡ ጦር ፡ ጋራ ፡ ተጋጭተው ፡ መመለሳቸውንና ፡ እንደገና ፡ መንገድ ፡ ለውጠው ፡ በጫቆ ፡ መውረዳቸውን ፤ ስለሰማን ፡ በፍጥነት ፡ ተገናኝተን ፡ ስለማንኛውም ፡ እኳኋን ፡ እንድንነጋገር ፡ በነጋድራስ ፡ በለጠ ፡ እጅ ፡ ደብዳቤ ፡ ላክሁ ፤ ደግም ፡ ከጫቆ ፡ (ደጃዝማች) ፡ አቶ ፡ ይመር ፡ ፈለቀ ፡ መጥተው ፡ እንዲገናኙንና ፡ እድንነጋገር ፡ ጽፈላቸዋለሁ ፤ ስም ፡ ስማቸው ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ለተጻፉት ፡ የጭልጋና ፡ የተንከል ፡ ባንዳዎችም ፡ ደብዳቤ ፡ ቢጸፍላቸውና ፡ ማስረጃ ፡ ምልክት ፡ ካዩ ፡ ወደኛ ፡ ይመጣሉ ፡ ብሎ ፡ ነጋድራስ ፡ በለጠ ፡ ስላመለከተኝ ፡ ቢቻላቸው ፡ አለንበት ፡ ድረስ ፡ መጥተው ፡ እንዲገናኙንና ፡ እንድንነጋገር ፡ ባይቻላቸው ፡ በቀጥታ ፡ ግርማዊነትዎን ፡ የሚገናኙበትን ፡ መንገድ ፡ እንዲመለከታቸው ፡ መልስ ፡ በቶሎ ፡ እንዲጸፍላቸው ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ አዋጅ ፡ ጋራ ፡ በነጋድራስ ፡ በለጠ ፡ እጅ ፡ ደብዳቤ ፡ ልኬላቸዋለሁ ።

ስም ፡ ስማቸው ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ፡

| | | |
|---|---|---|
| ፩ ፡ | ፊታውራሪ ፡ ዓለማየሁ ፡ ቢተዋ ፡ | (ጭልጋ) |
| ፪ ፡ | ቀኛዝማች ፡ ሁሉ ፡ ጌታ | » |
| ፫ ፡ | ግራዝማች ፡ ረዳ ፡ ዓለሚ ፡ | » |
| ፬ ፡ | ፊታውራሪ ፡ ሞላ ፡ | ተንከል |
| ፭ ፡ | ልጅ ፡ አስናቀው ፡ | » |
| ፮ ፡ | ቀኛዝማች ፡ ደፈርሻ ፡ እሸቴ ፡ | » |
| ፯ ፡ | ግራዝማች ፡ አደባ ፡ | » |

በአርበኞችና ፡ በሕዝብ ፡ ምርጫ ፡ የተሰጠ ፡ ማዕርግ ፤

ዳግም ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ለአለቃና ፡ ለጣቂሳ ፡ የተላከውን ፡ የግርማዊነትዎ ፡ አዋጅ ፡ በዚሁ ፡ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ ላለው ፡ ሕዝብ ፡ አባ ፡ ገብረ ፡ የሐንስ ፡ ስለኛ ፡ ሆነው ፡ እንዲያደርሱልን ፡ ከያይነቱ ፡ የግርማዊነትዎ ፡ አዋጅና ፡ በተለይ ፡ ለርሳቸው ፡ የተላከውን ፡ የግርማዊነትዎን ፡ ዱብዳቤ ፡ ጭምር ፡ በነጋድራስ ፡ በለጠ ፡ እጅ ፡ ልኬላቸዋለሁ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጅራን ፡ ወንዝ ፡ ተሻግረን ፡ ማጅር ፡ ማዘጊያ ፡ አደርን ። ጅራ ፡ ወንዝ ፡ ላይ ፡ ፳ ፡ የሚሆኑ ፡ የልጅ ፡ ወንድማገኘሁ ፡ ሰዎች ፡ ደርሰውልን ፡ አገኘናቸው ፤ የክብት ፡ እርዳታ ፡ ግን ፡ አልመጣልንም ።

ነሐሴ ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ማኅበረ ፡ ሥላሴዎች ፡ ከማጅር ፡ መዘጊያ ፡ በታች ፡ አራት ፡ አጋሰሶች ፡ እስከ ፡ ሰራቆ ፡ ድረስ ፡ አዘውልን ፡ ኑሮ ፡ አባ ፡ ኪዳነ ፡ ማርያም ፡ የሚባሉ ፡ መነኩሴ ፡ ከብቶቹን ፡ አስረከቡን ። ለማኅበረ ፡ ሥላሴዎች ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ የግርማዊነትዎ ፡ እርዳታ ፡ ተሰጥቷል ። ለአባ ፡ ኪዳነ ፡ ማርያም ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ ብር ። ከማጅር ፡ መዘጊያ ፡ ተነስተን ፡ በከሜል ፡ የሚባለውን ፡ ወንዝ ፡ ተሻግረን ፡ ካሣ ፡ ባድማ ፡ በሚባለው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ አደርን ።

ነሐሴ ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ከካሣ ፡ ባድማ ፡ ተነስተን ፡ አዙን ፡ የሚባለው ፡ ወንዝ ፡ ሞልቶ ፡ ልንሻገረው ፡ ስላልቻልን ፡ አፋፉ ፡ ላይ ፡ ሰፍረን ፡ አደርን።

ነሐሴ ፡ ፲፬ ፡ ቀን ፡ ከአዙሁ ፡ ወንዝ ፡ ተነስተን ፡ ሰራቆ ፡ ገባን ፤

ሰራቆ ፡ ስንገባ ፡ ቀኛዝማች ፡ ወርቄን ፡ አላገኘናቸውም ፤ የተቀበለንም ፡ እንደራሴያቸው ፡ ግራዝማች ፡ በለጠ ፡ ደራሽ ፡ ነው ። ልክ ፡ ሰራቆ ፡ ስንደርስ ፡ ስንቅ ፡ አልቆብን ፡ ነበርና ፡ ግራዝማች ፡ በለጠ ፡ እህል ፡ ሊያሸምትልን ፡ አልቻለም ። ሰራቆ ፡ ላይ ፡ እህልና ፡ ከብት ፡ አይገኝም ። የሥጋ ፡ ከብት ፡ ተፈልጎ ፡ አንድ ፡ ሙክት ፡ ፍየል ፡ ብቻ ፡ ተገኘ ። ያውም ፡ አሥር ፡ ብር ፡ አወጣ ፤ ስለዚህ ፡ ከልጅ ፡ ወንድማገኘሁ ፡ አገር ፡ ከቻባ ፡ ሽምብራና ፡ ማሽላ ፡ የሥጋም ፡ ከብት ፡ አይጠፋም ፡ ስለተባለ ፡ ከጣቂሳም ፡ ቢሆን ፡ በዘመድ ፡ አሸምተው ፡ እንዲልኩልን ፡ ገንዘብ ፡ ሰጥተን ፡ ወዳ



ገራቸው ፡ እንዲሄዱና ፡ ነሐሴ ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ተመልሰው ፡ ለሥራ ፡ ጉዳይ ፡ እንድንነጋገር ፡ ተቃጠርን ። ልጅ ፡ ወንድማገኘሁ ፡ ከነሰዎቻቸው ፡ ከግራዝማች ፡ ረዳ ፡ ሰዎች ፡ የበለጠ ፡ ስለረዱን ፡ ለሰዎቻቸውም ፡ የፍሬዳ ፡ መግዣ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ተሰጣቸው ። ለራሳቸው ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ እርዳታ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ተጨመረላቸው ፤

ስም ፡ ስማቸው ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ለተጻፈላቸው ፡ ባንዳዎች ፡ ደብዳቤ ፡ ቢጻፍላቸው ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ልጅ ፡ ወንድማገኘሁ ፡ ስላመለከቱኝ ፡ ቢቻላቸው ፡ አለንበት ፡ ድረስ ፡ መጥተው ፡ እንድንገናኝና ፡ እንድንነጋገር ፡ ባይቻላቸው ፡ በቀጥታ ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ ጋራ ፡ የሚገናኙበትን ፡ መንገድ ፡ እንዳመለከታቸው ፡ መልሱን ፡ በልጅ ፡ ወንድማገኘሁ ፡ በኩል ፡ በቶሎ ፡ እንዲልኩብኝ ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ አዋጅ ፡ ጋራ ፡ ደብዳቤ ፡ ልኬላቸዋለሁ ።

| | | |
|---|---|---|
| ፩ ፡ | ግራዝማች ፡ አደባ ፡ ማለፊያ ፡ | (ጣቁሳ) |
| ፪ ፡ | ደጃዝማች ፡ በዛብህ ፡ | » |
| ፫ ፡ | ግራዝማች ፡ መንገሻ ፡ ንጉሤ ፡ | » |
| ፬ ፡ | ግራዝማች ፡ ወርቄ ፡ | » |
| ፭ ፡ | ቀኛዝማች ፡ አዱኛ ፡ ፈለቀ ፡ | » |

ቀኛዝማች ፡ ወርቄ ፡ ቋራ ፡ ላይ ፡ የያዙትን ፡ ሥራ ፡ እንደራሴ ፡ አድርገውበት ፡ ቢመጡ ፡ የማያስጋ ፡ እንደሆነ ፡ መጥተው ፡ እንዲገናኙን ፡ ጽፈላቸው ፡ ነበርና ፡ በነሐሴ ፡ ፲፮ ፡ ቀን ፡ መጥተው ፡ ተገናኙን ፡ ከእንግዶቻችን ፡ ጋራ ፡ አስተዋውቀን ፡ የግርማዊነትዎ ፡ ደብዳቤ ፡ ከተሰጣቸው ፡ በኋላ ፡ ሰዎቻቸው ፡ እንደተሰበሰቡ ፡ ሁለት ፡ የግርማዊነትዎ ፡ አዋጅ ፡ ተነበበላቸው ፤ ከግራዝማች ፡ ረዳ ፡ ጋራ ፡ እንደተነጋገርነው ፡ እንደዚሁ ፡ ከቀኛዝማች ፡ ወርቄ ፡ ጋራ ፡ እንደሚከተለው ፡ ተነጋገርናል ። የቋራን ፡ ምሽግ ፡ ከከበቡ ፡ በኋላ ፡ የቋሬ ፡ አኳኋን ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ብንጠይቃቸው ፤ ቋራ ፡ አገሩ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ነው ፤ በቋራ ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ባላባቶች ፡ ሁሉ ፡ አቅፈውኛል ፤ አንድ ፡ መቶ ፡ ስባት ፡ ብረትም ፡ ከኢጣልያን ፡ ከድቶ ፡ ለኔ ፡ ገብቶልኛል ፡ ብለው ፡ ነገሩን ፤

በምሽጉ ፡ ውስጥ ፡ የቀሩ ፡ ባላባቶች ፡ እነማን ፡ እነማን ፡ ናቸው ፡ ብለን ፡ ብንጠይቃቸው ፤ ቀኛዝማች ፡ አቤልነህ ፡ ናደው ፤ ፊታውራሪ ፡ ገብሬ ፡ ወንድማገኘሁ ፤ ግራዝማች ፡ ስጣርገው ፡ ዋሴ ፤ ባላምባራስ ፡ ጌታሁንና ፡ የቀኛዝማች ፡ ወርቄ ፡ ያጎታቸው ፡ ልጅ ፡ ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ መንገሻ ፡ ናቸው ፡ ብለው ፡ መለሱልን ።

ስለ ፡ ቋራ ፡ ምሽግ ፡ አኳኋን ፡ የነገሩን ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ፡

ምሽጉ ፡ የተሠራው ፡ ከሁሉ ፡ ከፍ ፡ ባለችዋ ፡ ሳሊ ፡ ከምትባለው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ነው ፤ ዙሪያውን ፡ ዱርና ፡ ጫካ ፡ ነው ፤ መሐሉ ፡ ግን ፡ የተመ

ነጠረ ፡ ስለሆነ ፡ ምሽጉ ፡ ከሩቅ ፡ ፍንትው ፡ ብሎ ፡ ይታያል ፤ ቦታው ፡ ድንጋያማ ፡ ሜዳ ፡ ነው ፡ በስተምዕራብ ፡ ደቡብ ፡ በኩል ፡ ገደል ፡ ነው ፤ በስተምሥራቅ ፡ ሰሜን ፡ በኩል ፡ ሜዳ ፡ ነው ፤ አጥሩ ፡ ሁለት ፡ ዙር ፡ ነው ፤ የውስጠኛው ፡ በእንጨትና ፡ ባፈር ፡ የተሠራ ፡ ነው ፤ የውጭው ፡ ዙሪያ ውን ፡ እርድ ፡ ነው ፡ በዚህም ፡ እርድ ፡ ውስጥ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ተረኛ ፡ ወታ ደሮች ፡ ዘብ ፡ ይጠብቃሉ ፡ ቤቱ ፡ ሁሉ ፡ በውስጠኛው ፡ አጥር ፡ ውስጥ ፡ ነው ፡ ቤቱ ፡ ብዙ ፡ ስለሆነ ፡ ጥቅጥቅ ፡ ያለ ፡ ነው ። ከሁለት ፡ ሰቀላ ፡ ቤት ፡ በተቀር ፡ ሁሉም ፡ ክብ ፡ ነው ። አንድ ፡ ብቻ ፡ የቆርቆሮ ፡ ክዳን ፡ ሲሆን ፡ የቀረው ፡ ሁሉ ፡ የሣር ፡ ክዳን ፡ ነው ፤ ቆርቆሮውንም ፡ ቅጠል ፡ አልብሰውታል ።

ጥይት ፡ መጋረያ ፡ የተቀመጠው ፡ በሣር ፡ ክዳን ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ነው ። የቆርቆሮው ፡ ቤት ፡ ግን ፡ የተሰበረ ፡ ብረት ፡ የሚቀመጥበትና ፡ የሚታደስበት ፡ ነው ። አንድ ፡ ራዲዮ ፡ አለ ፤ ነጮች ፡ ስምንት ፡ ናቸው ፤ ሶስቱ ፡ የሌፍትናንት ፡ ማዕረግ ፡ አላቸው ። ጠቅላዩ ፡ ቴኔቲ ፡ ባሩዱ ፡ ይባላል ። ሶስት ፡ ሹምባሾች ፡ አሉ ፤ ባንድ ፡ ሹምባሽ ፡ ውስጥ ፡ ፹ ፡ ወታ ደር ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ባንዳ ፡ እየሆነ ፡ ከቋራ ፡ ከገባለት ፡ ሕዝብ ፡ በስ ተቀር ፡ የሠለጠነው ፡ ወታደር ፡ መቶ ፡ ሃያ ፡ ነው ፤ እነዚህም ፡ ሐማ ሴን ፤ በኒአምርና ፡ ሱማሌዎች ፡ ናቸው ። ከባንዳው ፡ ጭምር ፡ በጠቅ ላላ ፡ ካራት ፡ መቶ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ይሆናል ። ብረታቸው ፡ ሁሉም ፡ አልቢን ፡ ነው ። የሚበቃ ፡ ጥይትና ፡ የእጅ ፡ ቦንብ ፡ አላቸው ፤ ፲፰ ፡ መትረየስ ፡ አለ ፤ ፯ቱ ፡ ከባድ ፡ ባለውኃ ፡ ነው ፤ ፲፩ዱ ፡ ድግን ፡ አልቢን ፡ መትረየስ ፡ ነው ። መድፍ ፡ የለም ፤ የሚበቃ ፡ እህል ፡ በም ሽጉ ፡ ውስጥ ፡ አላቸው ። ከበርበሬና ፡ ከጨው ፡ በስተቀር ፡ የሚቸግራ ቸው ፡ ነገር ፡ የለም ። ጥሩ ፡ ውሀም ፡ በምሽጉ ፡ መካከል ፡ ያልፋል ፤

ምሽጉን ፡ የከበቡ ፡ የርስዎ ፡ ወታደሮች ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡ ብለን ፡ ብንጠይቃቸው ፡ ሶስት ፡ መቶ ፡ ናቸው ፡ ብለው ፡ መለሱልን ፤

የኢጣልያን ፡ ወታደር ፡ ለመውጣትና ፡ ለመግባት ፡ አይችልም ፡ ወይ ፡ ብለን ፡ ብንጠይቃቸው ፤ አይችልም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አንዳንድ ፡ ሴቶች፡ ሰላዮቻቸው ፡ ሆነው ፡ ይመላለሳሉ ፤ እነርሱም ፡ በሌሊትና ፡ መንገድ ፡ በማሳበር ፡ በዱር ፡ እየተሸሸጉ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ነገሩን ።

እንደዚሁ ፡ የኢጣልያን ፡ ጦር ፡ ለማምለጥ ፡ ወይም ፡ እርዳታ ፡ ከውጭ ፡ ሊጨመርለት ፡ አይችልም ፡ ወይ ፡ ብለን ፡ ብንጠይቃቸው ፤ በር ፡ በሩን ፡ በዘበኛ ፡ አስጠብቀንዋልና ፡ ከቋራ ፡ ለመውጣት ፡ ወይም ፡ ከውጭ ፡ ወደ ፡ ቋራ ፡ ለመግባት ፡ አይችልም ፡ ብለው ፡ መለሱልን ፤

ከገለባት ፡ እስከ ፡ ጐጃም ፡ ድረስ ፡ መንገድ ፡ ለመክፈት ፡ ብንፈልግ ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ይሻላል ፡ ብለን ፡ ብንጠይቃቸው ፡ መጀመሪያ ፡ የቋራን ፡



ምሽግ ፡ ማፍረስ ፡ ያስፈልጋል ፡ ይኸውም ፡ የሚፈርሰው ፡ የአውሮፕላን ፡ እርዳታ ፡ የተደረገልን ፡ እንደሆነ ፡ ነው ፤ ባውሮፕላን ፡ ቦምብና ፡ ያዋጅ ፡ ወረቀት ፡ ቢጣልበት ፡ ከእስላም ፡ በስተቀር ፡ ከምሽጉ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ወታደር ፡ ሁሉ ፡ ለኔ ፡ እንደሚገባልኝ ፡ የታወቀ ፡ ነው ፤ እስላሙ ፡ በውድ ፡ የገባልኝ ፡ እንደሆነ ፡ ገባ ፡ ያልገባ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ በኃይል ፡ እናስለቅ ቀዋለን ፡ ብለው ፡ ነገሩን ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዛሬ ፡ ለኢጣልያን ፡ ኃይል ፡ ሆነው ፡ በመንገዳችን ፡ ላይ ፡ የሚያስቸግሩን ፡ የማጠቢያ ፡ ሻንቅሎች ፡ (ጉሙዞች) ፡ ቀኛዝማች ፡ ወርቁ ፡ ቋራን ፡ አስለቀቀ ፡ ማለትን ፡ ሲሰሙ ፡ ኢጣልያንን ፡ ከድተው ፡ ወደኛ ፡ እንደሚገቡ ፡ የታወቀ ፡ ነው ፡ አሉ ፡ እነርሱንም ፡ እኔው ፡ ራሴ ፡ ወርጄ ፡ ያለጦርነት ፡ ላሳምናቸው ፡ እችላለሁ ፡ ብለው ፡ ነገሩን ፡ ቋራ ፡ ከተለቀቀና ፡ ጉሙዞች ፡ ወደኛ ፡ ከሆኑ ፡ ከመተማ ፡ እስከ ፡ ጐጃም ፡ ድረስ ፡ ያላንዳች ፡ ስጋት ፡ መንገዳችን ፡ ክፍት ፡ ይሆ ናል ፡ ብለው ፡ ነገሩን ።

አውሮፕላን ፡ ለመላክ ፡ ችግር ፡ የሆነው ፡ ምሽጉ ፡ ያለበት ፡ ሥፍራ ፡ በካርታ ፡ ላይ ፡ ስላልተጻፈና ፡ የአውሮፕላን ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ የት ፡ ብለን ፡ እንሂዳለን ፡ ብለው ፡ ስለሚጠይቁ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ነገሩዋቸው ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አውሮፕላን ፡ ቋራ ፡ ላይ ፡ ሲበር ፡ ምሽጓ ፡ ለብቻዋ ፡ ፍንትው ፡ ብላ ፡ ትታያለች ፡ ብለው ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለውን ፡ ቃል ፡ የሚበቃ ፡ ምልክት ፡ ሰጡ ፤

ዙሪያው ፡ ዱር ፡ መሐሉ ፡ የተመነጠረ ፡ ነው ፤ የተሠራውም ፡ ሁሉ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ቦታ ፡ ነው ፡ የምሽጉን ፡ ያህል ፡ ጥቅጥቅ ፡ ያለ ፡ መንደር ፡ የለም ፤ ሁለት ፡ ዙር ፡ አጥር ፡ አለው ። በስተምዕራብ ፡ ደቡብ ፡ ገደል ፡ ነው ። በስተምሥራቅ ፡ ሰሜን ፡ ሜዳ ፡ ነው ፤ የፋቂ ፡ ማረፏ ፡ የነጋዴ ፡ ጐዳና ፡ በምሽጉ ፡ መሐል ፡ ያልፋል ፤

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ወታደር ፡ ለማስከተት ፡ ይችላሉ ፡ ብለን ፡ ብንጠይቃቸው ፤ የራሴ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ብረት ፡ አሁን ፡ ከኢጣል ያን ፡ ከድቶ ፡ የገባልኝ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሰባት ፡ ብረትና ፡ ከግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ የተቀበልኩት ፡ እርዳታ ፡ ሶስት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ በጠቅላላው ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ሰባት ፡ ብረት ፡ ለማስከተት ፡ እችላለሁ ፡ አሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከሶስት ፡ መቶ ፡ የሚበልጥ ፡ ጀሌ ፡ አለኝ ፡ ብለው ፡ ስላመለከቱና ፡ በቶሎ ፡ ይኸንን ፡ መንገድ ፡ ለማሠልጠን ፡ መጋረያ ፡ ቢጨመርላቸው ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ ስለታየን ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሐምሳ ፡ ዲሞትፎር ፤ አንድ ፡ መቶ ፡ ሐምሳ ፡ ማርቲን ፤ ላንድ ፡ ብረት ፡ ከመቶ ፡ ጥይት ፡ ጋራ ፤ ፪ ፡ ሺህ ፡ የእጅ ፡ ቦምብ ፤ አሥር ፡ ሺህ ፡ የምንሽር ፡ ጥይትና ፡ አንድ ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ የግርማ ዊንትዎን ፡ እርዳታ ፡ ሰው ፡ ልከው ፡ እንዲቀበሉ ፡ አስታውቀናቸው ፡ ኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፈውላቸዋል ። እንግዲህ ፡ በጠቅላ ላው ፡ ለማስከተት ፡ የሚችሉት ፡ ጦር ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ሰባት ፡

ይሆናል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አልቤን ፤ ወጨፎና ፡ ሰናድር ፡ ስለ ፡ ተቀላቀለባ ቸውና ፡ እነዚህ ፡ ዓይነት ፡ ብረቶች ፡ የበቃ ፡ ጥይት ፡ ስለ ፡ ሌላቸው ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ብንለው ፡ ይሻላል ።

ቋራ ፡ ከተለቀቀ ፡ በኋላ ፡ ከልጅ ፡ ወንድማገኘሁ ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ ማጠቢያ ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ ሻንቅሎች ፡ (ጉሙዞች) ፡ ሰብካችሁ ፡ ወደኛ ፡ እንዲሆኑ ፡ አድርጋችሁ ፡ ከመተማ ፡ እስከ ፡ ቋራ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ መንገድ ፡ ለመጠበቅ ፡ እናቂ ፡ ማረጃ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ ባቅራቢያ ፡ ወዲህና ፡ ወዲያ ፡ እየተመላለሱ ፡ መንገዱን ፡ የሚስልሉ ፡ ወታደሮች ፡ ለማስቀመጥ ፡ ይችላሉ ፡ ወይ ፡ ብለን ፡ ብንጠይቃቸው ፤ እችላለሁ ፡ ብለው ፡ መለሱልን ።

ዳግም ፡ ለምናልባት ፡ መተማን ፡ ለማስለቀቅ ፡ ቢፈለግና ፡ ባርማጭሆና ፡ ከሜቶ ፡ ጦር ፡ ሲታዘዝ ፡ ከርስዎም ፡ እርዳታ ፡ የተፈለገ ፡ እንደ ሆን ፡ ከልጅ ፡ ወንድማገኘሁ ፡ ጋራ ፡ ተማክራችሁ ፡ ረዳት ፡ ጦር ፡ ወደ ፡ መተማ ፡ ለመላክ ፡ ይችላሉ ? ብለን ፡ ብንጠይቃቸው ፤ ቋራ ፡ ከተለቀቀ ፡ ሁሉንም ፡ እችላለሁ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ቋራ ፡ ካልተለቀቀ ፡ ቋራን ፡ ትቼ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ መሄድ ፡ በቋራ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ሕዝብ ፡ ማስፈጀት ፡ ይሆን ብኛል ፡ ብለው ፡ መለሱ ፤

ግራዊት ፡ ላይ ፡ ከነሻሌቃ ፡ መስፍን ፡ ስለሺ ፡ ጋራ ፡ የገጠመውን ፡ የኢጣልያን ፡ ጦር ፡ ወሬውን ፡ አስቀድመው ፡ ሰምተው ፡ ነበር ፡ ወይ ፡ ብለን ፡ ብንጠይቃቸው ፡ አልሰማሁም ፡ ብለው ፡ ነገሩን ፤ የኢጣልያን ፡ ጦር ፡ ሲመጣ ፡ እንዴት ፡ አድርገው ፡ ወሬ ፡ ያገኛሉ ፡ ብለን ፡ ብንጠይቃቸው ፤ በክረምት ፡ ሰው ፡ ወዲህና ፡ ወዲያ ፡ ስለ ፡ ማይመላለስ ፡ ችግር ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በበጋ ፡ ሰው ፡ ይመላለሳልና ፡ አገኛለሁ ፡ ብለው ፡ መለሱልን ፤

ከጉባ ፡ መተማ ፡ ወይም ፡ ከመተማ ፡ ጉባ ፡ የኢጣልያን ፡ ጦር ፡ ይመላለሳል ፡ ወይ ፡ ብለን ፡ ብንጠይቃቸው ፡ የሸንፋ ፡ ወንዝ ፡ ስለሞላ ፡ በክረምት ፡ ለመመላለስ ፡ አይችልም ፡ ብለው ፡ መለሱልን ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የኢጣልያን ፡ ጦር ፡ ለመውጣት ፡ መዘጋጀቱን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ አስቀድመው ፡ ጥንቃቄ ፡ ማድረግ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ወሬ ፡ ሁሉ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ለኛ ፡ ወይም ፡ በገለባት ፡ ላሉ ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ ወደሚቀርበው ፡ ወሬውን ፡ በቶሎ ፡ እንዲያስታውቁ ፡ ነግረናቸው ፤ እሺ ፡ አደርጋለሁ ፡ ብለዋል ።

የተጨመረላቸውን ፡ የግርማዊነትዎን ፡ እርዳታ ፡ ለማስነሳት ፡ በፍጥነት ፡ ሰው ፡ እልካለሁ ፡ ስላሉን ፡ የሚልኳቸውን ፡ ሰዎች ፡ ለኛም ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ብረት ፡ ከነጥይቱ ፡ እንዲያመጡልንና ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የቀሩ



ትን ፡ ሚስተር ፡ ዊንሆልድ ፡ የሚባሉትን ፡ እንግዳ ፡ ዘበኛ ፡ ሆነው ፡ ይዘውልን ፡ እንዲመጡ ፡ ከዚህም ፡ ደህና ፡ ዘበኛ ፡ አድርገው ፡ እስከ ፡ ፊታውራሪ ፡ አያሌው ፡ አገር ፡ ድረስ ፡ እንዲያደርሱልን ፡ ያደርጋሉ ፡ ወይ ፡ ብለን ፡ እርዳታ ፡ ብንለምናቸው ፡ እሺ ፡ አደርጋለሁ ፡ ብለዋል ፤

ነሐሴ ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ካፕቴን ፡ ክሩሽሉ ፡ የተባሉ ፡ የእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ ወታደር ፡ አለቃ ፡ የቋራን ፡ ምሽግ ፡ እኳኋን ፡ አይተው ፡ ለማስታወቅ ፡ ከቀኛዝማች ፡ ወርቁ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ቋራ ፡ ሄደዋል ፤ ከኛም ፡ ወገን ፡ ልጅ ፡ መርዕድ ፡ መንገሻ ፡ ተልኳል ።

ነሐሴ ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ከልጅ ፡ ወንድማገኘሁ ፡ ጋራ ፡ የሚከተለውን ፡ ተነጋግረናል ፤

ባገርዎ ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ወታደር ፡ ለማስከተት ፡ ይችላሉ ፡ ብለን ፡ ብንጠይቃቸው ፡ ሕዝቡ ፡ መተማ ፡ እየወረዳችሁ ፡ ብረት ፡ እንስ ፡ ተብሏልን ፡ ስለሰማ ፡ የደምብ ፡ ብረት ፡ እቀበላለሁ ፡ እያለ ፡ የራሱን ፡ መሸጥ ፡ ጀምሯል ፤ የሚሸጠውም ፡ በረሀቡ ፡ ምክንያት ፡ ስለተቸገረና ፡ የሚበላው ፡ ስላጣ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ነገሩን ፤

ለማነው ፡ የሚሸጠው ፡ ብለን ፡ ብንጠይቃቸው ፤ የአቸፈር ፡ ሕዝብ ፡ እየመጣ ፡ ይገዛዋል ፡ አሉኝ ፤

ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ መሣሪያ ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ያዘዙት ፡ ብረት ፡ ያልያዘው ፡ እንዲይዝና ፡ ኃይላችሁ ፡ ለጠላት ፡ ኃይል ፡ ተወዳዳሪ ፡ እንዲሆን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ የያዛችሁትን ፡ እንድትሸጡ ፡ አይደለም ፡ ብለን ፡ ከነገርናቸው ፡ በኋላ ፡ ሁለተኛ ፡ እንዳይሸጥ ፡ አዋጅ ፡ ባገርዎ ፡ ላይ ፡ ያስነግሩ ፡ ብለናቸው ፡ እሺ ፡ ብለዋል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ከሰጡኝ ፡ እርዳታ ፡ ሌላ ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ብረት ፡ አይጠፋምና ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ለማስከተት ፡ እችላለሁ ፡ አሉን ።

ስለ ፡ መንገዳችን ፡ ሐሳባቸውን ፡ ብንጠይቅ ፤ በማጠቢያ ፡ ያሉትን ፡ ሻንቅሎች ፡ (ጉሙዞች) ፡ ሰብኬ ፡ ከኢጣልያን ፡ ላስከዳ ፡ እችላለሁ ፡ ከዚህ፡ ቀደምም ፡ ልከውብኝ ፡ ነበር ፤ እኔም ፡ መንገዱን ፡ ለማስጠበቅ ፡ ወዲህና ፡ ወዲያ ፡ እየተመላለሱ ፡ የሚሰልሉ ፡ ዘበኞች ፡ ናቂ ፡ ማረጃ ፤ ዶስና ፡ መረውድባ ፡ ላይ ፡ ለማስቀመጥ ፡ እችላለሁ ፤ የማጠቢያ ፡ ሻንቅሎችም ፡ አጠገባችን ፡ ከሆናችሁ ፡ ከኢጣልያን ፡ ጋራ ፡ አንሆንም ፡ ይላሉ ፡ ብለው ፡ ነገሩን ፤

በዚህ ፡ በኩል ፡ መንገዱን ፡ ሳስጠብቅ ፡ በጀርባዬ ፡ የጣቂሳ ፡ ባንዳ ፡ አለና ፡ ብረት ፡ ያንሰኛል ፤ ባይሆን ፡ እንኳን ፡ መንገዱን ፡ ለሚጠብቁልኝ ፡ ዘበኞች ፡ የማበረታታበት ፡ ጥቂት ፡ ብረት ፡ እሰጡኝ ፡ ብለው ፡ ስላ

መለኪቱ ፡ አሥር ፡ ዲሞትሮር ፡ ከንጥይቱ ፤ አንድ ፡ ሺህ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ የምንሸር ፡ ጥይትና ፡ አንድ ፡ ሺህ ፡ የእጅ ፡ ቦምብ ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ እርዳታ ፡ እንዲጨመርላቸው ፡ አስታውቀናቸው ፡ ኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ጽፈውላቸዋል ።

የጣቁሳን ፡ ሕዝብ ፡ አኳኋን ፡ ብንጠይቃቸው ፤ ሕዝቡ ፡ ተሰብስቦ ፡ ለኔ ፡ ወረቀት ፡ ሊጽፍልኝ ፡ ይመክራል ፡ ብሎ ፡ አንዱ ፡ ነግሮኛልና ፡ ወረቀቱ ፡ ሲመጣልኝ ፡ እልክላችኋለሁ ፡ ደጃዝማች ፡ በዛብህም ፡ ወደ ፡ ጎርጎራ ፡ ተጠርተው ፡ ሄደዋል ፡ አሉን ፤

የኢጣልያን ፡ ጦር ፡ በወጣ ፡ ጊዜና ፡ ማንኛውም ፡ አስቀድሞ ፡ ጥንቃቄ ፡ ማድረግ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ወሬ ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ በቶሎ ፡ ወደ ፡ ገለባት ፡ ላሉ ፡ የእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ ጽፈው ፡ እንዲያስታውቁ ፡ ብለን ፡ ነግረናቸው ፡ እሺ ፡ ብለዋል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ አጋሰሶች ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ኰራፕሩብ ፡ እየወረዱ ፡ በኪራይ ፡ ዕቃ ፡ የሚያመላልሱልን ፡ ሰዎች ፡ ይነጋገሩልን ፡ ብለናቸው ፡ በመንገዳችን ፡ የማያስጋ ፡ መሆኑን ፡ ካረጋገጥን ፡ በኋላ ፡ በበቅሎ ፡ ፺ ፡ ብር ፡ ባህያ ፡ ፮ ፡ ብር ፡ ሒሳብ ፡ እስከ ፡ ኰራንታ ፡ ሰራቆ ፡ ድረስ ፡ እንጋገራለሁ ፡ ብለው ፡ ተስፋ ፡ ሰጥተውናል ።

የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ሆኖ ፡ ደህና ፡ መንገድ ፡ መሪ ፡ በመያዛችን ፡ ያላንዳች ፡ አደጋ ፡ ሰራቆ ፡ ለመድረስ ፡ ቻልን ፡ እንጂ ፡ የመንገዳችንስ ፡ አኳኋን ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ይቅርና ፡ በሰላሙም ፡ ጊዜ ፡ ሊደረግ ፡ የማይገባ ፡ ነው ፡ ከብት ፡ ጫኝና ፡ ሳቢ ፡ በቂ ፡ ሰው ፡ አልነበረንም ፤ በዝናብ ፡ በጭቃ ፡ ባቀበትና ፡ በቁልቁለት ፡ ዱር ፡ እየጣስን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሁለት ፡ ከብት ፡ ሲስብና ፡ ሲጭን ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ችግር ፡ እንዳለው ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ይገምታል ፡ እስከ ፡ ሰራቆ ፡ ድረስ ፡ እንዳየሁት ፡ ከብት ፡ በመጫንና ፡ ከብት ፡ በመሳብ ፡ ወይም ፡ የከብት ፡ እርዳታ ፡ በማድረግ ፡ ባላገር ፡ ይረዳናል ፡ ብሎ ፡ ተስፋ ፡ ማድረግ ፡ ከንቱ ፡ ነው ፤ ጎዳሬፍ ፡ ላይ ፡ ልጅ ፡ ወንድማገኘሁ ፡ አሥር ፡ አህዮች ፡ ግራዝማች ፡ ረዳ ፡ ጥቂት ፡ አጋሰሶች ፡ እንረዳለን ፡ ብለው ፡ ተስፋ ፡ ሰጥተውን ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ለሚና ፡ ላይ ፡ ስንገናኝ ፡ የልጅ ፡ ወንድማገኘሁ ፡ ሰዎች ፡ በኰራፕሩብ ፡ ጨው ፡ ገዝተው ፡ አህዮቻቸውን ፡ ጭነውብት ፡ ነበርና ፡ አንድም ፡ አህያ ፡ ለማግኘት ፡ አልቻልንም ፤ ግራዝማች ፡ ረዳም ፡ ከብቶች ፡ ሞተውብኝ ፡ ስለደረስኩ ፡ የከብት ፡ እርዳታ ፡ ላደርግላችሁ ፡ አልችልም ፡ አሉን ፤ ግራዝማች ፡ ረዳም ፡ ሠላሳ ፡ አጋሰሶችና ፡ አህዮች ፡ እንደተጫኑ ፤ ልጅ ፡ ወንድማገኘሁ ፡ ሃያ ፡ ስምንት ፡ አህዮች ፡ እንደተጫኑ ፡ ነበሩዋቸው ፡ የግራዝማች ፡ ረዳ ፡ ሰዎች ፡ እርሳቸው ፡ ወደ ፡ ካርቱም ፡ ወርደው ፡ እስኪመለሱ ፡ ድረስ ፡ ተበታትነው ፡ ስለ ፡ ቆዩዋቸው ፡ ፴፬ ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ነበራቸው ። ከነዚ



ህም ፡ መሐከል ፡ አሥራ ፡ አንዱ ፡ ጎዳድ ፡ ታመው ፡ ነበር ፡ ልጅ ፡ ወንድማገኘሁ ፡ ፳፺ ፡ ሰዎች ፡ ነበራቸው ፡ ከነርሱም ፡ ዘጠኙ ፡ ጎዳድ ፡ ታመው ፡ ነበር ፤ ከዶይካ ፡ ስንነሳ ፡ የእኛ ፡ ከብቶች ፡ ፶፫ ፡ በቅሎች ፡ ፴፬ ፡ አህዮች ፡ ነበሩ ፡ እስከ ፡ ድምበር ፡ ድረስ ፡ ሊሸኙን ፡ የመጡት ፡ ሱዳኖች ፡ ከዳስ ፡ ሲመለሱ ፡ ፲፬ ፡ አህዮች ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ተመልሰዋል ፤ እንግዲህ ፡ የእኛና ፡ የነግራዝማች ፡ ረዳ ፡ ከብቶች ፡ በጠቅላላው ፡ ፻፶፫ ፡ ከብቶች ፡ ነበሩ ። የሁላችንም ፡ ሰው ፡ በጠቅላላው ፡ ከዳስ ፡ ላይ ፡ ከተመለሱት ፡ ሱዳኖች ፡ በስተቀር ፡ ፶፳፬ ፡ ነበር ። ከነዚህ ፡ መሐከል ፡ ፳፬ቱ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ጎዳድ ፡ ያማቸው ፡ ነበር ፤ እንዲያው ፡ ለስሙ ፡ ከፊትና ፡ ከኋላ ፡ ዘበኞች ፡ አደረግን ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ቢደርስብን ፡ ኑሮ ፡ ምንም ፡ ለማድረግ ፡ እንደማንችል ፡ የታወቀ ፡ ነበር ፤

ባላገሮቹም ፡ የራሳቸውን ፡ ከብት ፡ ከማዳን ፡ በስተቀር ፡ የኛን ፡ እንደማያድኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ፤ እስከ ፡ ሰራቆ ፡ ድረስ ፡ ያየሁት ፡ ባላገር ፡ ሁሉ ፡ በፈቃዱ ፡ ካልሆነ ፡ በስተቀር ፡ በትእዛዝ ፡ ፈጽሞ ፡ አይሠራም ። እምቡልቡል ፡ ወንዝ ፡ ላይ ፡ የሰፈርን ፡ ጊዜ ፡ የግራዝማችን ፡ ረዳ ፡ ሰዎች ፡ ለልጅ ፡ ወንድማገኘሁ ፡ ብቻ ፡ ትተውን ፡ ባቋራጭ ፡ ወዳገራቸው ፡ ሊገቡ ፡ ነበር ። የዚህን ፡ ጊዜ ፡ ግራዝማች ፡ ረዳ ፡ ሊያዙዋቸው ፡ ስለማይችሉ ፡ ጥቂቶች ፡ ሰዎች ፡ ለምነው ፡ ጓዛቸውንና ፡ የታመሙትን ፡ ባቋራጩ ፡ መንገድ ፡ ሸኝተው ፡ እኛን ፡ እስከ ፡ አምባር ፡ ውሀ ፡ ድረስ ፡ ሸኙን ፡ እንደዚሁ ፡ ደግሞ ፡ የልጅ ፡ ወንድማገኘሁ ፡ ሰዎች ፡ ወሰናችን ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ነውና ፡ እዚሁን ፡ ወንዝ ፡ ተሻግረን ፡ እንሸኝም ፡ ብለው ፡ ብዙዎቹ ፡ ወዳገራቸው ፡ ተመለሱ ፡ ጥቂቶችን ፡ ልጅ ፡ ወንድማገኘሁ ፡ ለምነው ፡ በትእዛዝ ፡ ሳይሆን ፡ እስከ ፡ ሰራቆ ፡ ድረስ ፡ ይዘዋቸው ፡ መጡ ።

ከወሰናችን ፡ አንስቶ ፡ እስከ ፡ ሰራቆ ፡ ድረስ ፡ የሰፈርንበት ፡ ቦታ ፡ እንዲታወቅም ፡ ስም ፡ ስማቸውን ፡ ጠራሁ ፡ እንጂ ፡ አገሩ ፡ ሁሉ ፡ ጠፍ ፡ ስለሆነ ፡ አንድም ፡ መንደር ፡ አላገኘንም ።

ይኸንን ፡ ሁሉ ፡ በዝርዝር ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ማመልከቱ ፡ ብዙ ፡ ደክመናል ፡ ለማለትና ፡ አገልግሎት ፡ ለመቁጠር ፡ አይደለም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ለወደፊቱ ፡ የሚመጣ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በሙሉ ፡ ሳይሰናዳ ፡ እንዳይመጣ ፡ አስቀድሞ ፡ እንዲታሰብበት ፡ በማለት ፡ ነው ፤

ላንድ ፡ አጋሰስ ፡ ጫኝ ፡ ከሁለት ፡ ሰው ፡ በታች ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ችግር ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ ሰዎቹ ፡ ጤናማና ፡ ጠንካራ ፡ ጭነት ፡ የሚያውቁ ፡ መሆን ፡ ያስፈልጋቸዋል ፤ ከተጫኑ ፡ ከብቶች ፡ ሌላ ፡ ከብት ፡ የደከመና ፡ የሞተ ፡ እንደሆነ ፡ የሚተኩ ፡ ሌጣ ፡ ከብቶች ፡ እንዲሁ ፡ ከንዝ ፡ ጋራ ፡ መንዳት ፡ ያስፈልጋል ፤ ፳ ፡ አጋሰስ ፡ ተጭኖ ፡ እንደሆነ ፡ ቢያንስ ፡ ፭ ፡ አጋሰስ ፡ መለወጫ ፡ ያስፈልጋል ። እንደዚሁ ፡ በብዛቱና ፡ በማነሱ ፡

መጠን ፡ ማድረግ ፡ የሚጫነው ፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ በብረት ፡ ሳጥን ፡ ውስጥ ፡ ካልሆነ ፡ በቶሎ ፡ ይበላሻል ። ጭነቱም ፡ አነስ ፡ አነስ ፡ ያለ ፡ ካልሆነ ፡ ከብቱ ፡ ረጅም ፡ ጕዳና ፡ እንዲዘልቅ ፡ ለማድረግ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ። አጋሠሶቹ ፡ ቁጥራቸው ፡ ከአርባና ፡ ከሠላሳ ፡ የበለጠ ፡ እንደሆነ ፡ ከአምስት ፡ እስከ ፡ አሥር ፡ ሰዎች ፡ ፋስና ፡ መመንጠሪያ ፡ ይዘው ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ከከብቶቹ ፡ ፊት ፡ ፊት ፡ ዱሩን ፡ (ጫካውን) ፡ እየመነጠሩ ፡ እንዲሄዱ ፡ ያስፈልጋል ። ዱር ፡ ካልተመነጠረ ፡ ጭነት ፡ ይወድቃል ፡ ዕቃ ፡ ይበላሻል ፡ ከብትም ፡ ሰውም ፡ ይደክማል ።



ብላታ ፡ ደሬሳ ፡ አመንቴ ።

ስንቅ ፡ እያንዳንዱ ፡ ለየራሱ ፡ ተሰጥቶት ፡ እርሱው ፡ እንዲያልፍበት ፡ ካልተደረገ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ክርክር ፡ ያመጣል ፡ ጊዜም ፡ ያሳልፋል ። ዳግም ፡ ሰው ፡ የሚበቃውን ፡ ስንቅ ፡ ካላገኘ ፡ አመሉ ፡ ይበላሻል ፡ በሥራውም ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ፡ ማለት ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡ ስለዚህ ፡ በተቻለ ፡



መጠን ፡ ቀላል ፡ ለጭነት ፡ የማይከብድና ፡ ለሰው ፡ የሚመጥን ፡ ስንቅ ፡ ማዘጋጀት ፡ ያስፈልጋል ።

ስንቅ ፡ ከገለባት ፡ ጭኖ ፡ ጐጃም ፡ ለመድረስ ፡ የማይቻል ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ስንቅ ፡ ማዘጋጀት ፡ ዕቃም ፡ ማሳረፊያ ፡ የሚሆን ፡ ቦታ ፡ ከገለባት ፡ ተነስቶ ፡ ሰራቆ ፡ ከጐጃም ፡ ተነስቶ ፡ ሰራቆ ፡ እኩል ፡ ስለሆነ ፡ ከገዳሪፍ ፡ ዕቃ ፡ አንስቶ ፡ ሰራቆ ፡ ላይ ፡ ማሳረፍ ፡ ከጐጃም ፡ ሰውና ፡ ከብት ፡ ልኮ ፡ ማስወሰድ ፡ የሚቀና ፡ ይሆናል ፡ ሰዎቹም ፡ ሲመላለሱ ፡ ሰራቆ ፡ የማይገኘውን ፡ ከጐጃም ፡ ወደ ፡ ሰራቆ ፡ መላክ ፡ ሳይቻል ፡ ይቀር ፡ አይመስለኝምና ፡ ሰራቆ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ የሚችል ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ ከሰራቆ ፡ ዙሪያ ፡ እህል ፡ እየሸመተ ፡ ለተመላላሹ ፡ ስንቅ ፡ ለመስጠት ፡ የሚችል ፡ ማድረግ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ስለመሰለኝ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ አስታውቃለሁ ።

በኔ ፡ ሐሳብ ፡ አሁን ፡ እግርማዊነትዎ ፡ ዘንድ ፡ ካሉት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ [1] ብላታ ፡ ደሬሳን ፡ ለሥራ ፡ ረዳት ፡ የሚሆኑ ፡ ከካርቱም ፡ አብረዋቸው ፡ ከነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ስምምነት ፡ ካላቸው ፡ ውስጥ ፡ ባንድነት ፡ ሆነው ፡ በቶሎ ፡ መጥተው ፡ እንዲሠሩ ፡ ቢሆን ፡ መልካም ፡ ይመስለኛል ፡ ይኸውም ፡ ጊዜው ፡ አስቸኳይ ፡ ስለሆነ ፡ አሁኑኑ ፡ ማድረግ ፡ መልካም ፡ ነው ።

ዳግም ፡ አቶ ፡ ገብረ ፡ ሚካኤል ፡ ፍስሐዬ ፡ የሚባሉ ፡ የታመኑ ፡ ሐሳብ ፡ አዋቂና ፡ የረጉ ፡ ሰው ፡ መሆናቸውን ፡ ስለሰማሁ ፡ ለብላታ ፡ ደሬሳ ፡ መልካም ፡ ረዳት ፡ ሳይሆኑ ፡ አይቀሩም ፡ ይመስለኛልና ፡ ባንድነት ፡ ቢላኩ ፡ መልካም ፡ ነው ።

ሲመጡም ፡ ከጣቂሳ ፡ እህልና ፡ ማንኛውንም ፡ የምግብ ፡ ነገር ፡ ለማስገዛት ፡ ልጅ ፡ ወንድማገኘሁ ፡ ይረዱዋቸዋል ፡ ከቋራም ፡ እንደዚሁ ፡ ቀኛዝማች ፡ ወርቁ ፡ ይረዳሉ ፡

ብላታ ፡ ደሬሳን ፡ ለመላክ ፡ የማይቻል ፡ ቢሆንም ፡ እንደዚሁ ፡ ያለ ፡ የኀላፊነት ፡ ሥራ ፡ ተሰጥቶት ፡ ለመሥራት ፡ የሚችል ፡ ሰው ፡ ፈልጐ ፡ በቶሎ ፡ መላክና ፡ ሥራውን ፡ መጀመር ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ አመለክታለሁ ። በተረፈ ፡ በስንቅም ፡ ሆነ ፡ በሌላም ፡ አኳኋን ፡ ተሰዳን ፡ ተነስቶ ፡ በቀጥታ ፡ ጐጃም ፡ ለመድረስ ፡ ስለማይቻል ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ አስቸጋሪ ፡ መሆኑን ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ አሳስባለሁ ።

መጀመሪያ ፡ ከመተማ ፡ እስከ ፡ ሰራቆ ፡ ከሰራቆ ፡ እስከ ፡ ጐጃም ፡ ያለውን ፡ መንገዶችን ፡ በቶሎ ፡ ማልማትና ፡ ከአደጋ ፡ እንዲጠበቅ ፡ ማድረግ ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ ስለታየን ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ከተ

ኛዝማች ፡ ወርቂና ፡ ፩ ከልጅ ፡ ወንድማገኘሁ ፡ መንገዱን ፡ ለማልማትና ፡ ፋቂ ፡ ማረጃ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ ባትራቢያው ፡ መንገድ ፡ የሚያስልሉ ፡ ወታደሮች ፡ ለማቆም ፡ ፪ ከግራዝማች ፡ ረዳም ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ ከጭልጋ ፡ በታች ፡ እንዳይወርድ ፡ ለማድረግ ፡ ከቃላቸው ፡ ተስፋ ፡ ብናገኝ ፡ የጊዜውን ፡ ግምት ፡ የሥራውን ፡ መጀመሪያ ፡ አስፈላጊነትና ፡ ከባድነት ፡ የሚያውቅና ፡ የወታደር ፡ ትምህርት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ሙሉ ፡ ፕሮግራም ፡ (ማስታወሻ) ፡ በቂ ፡ ገንዘብና ፡ መሣሪያ ፡ ተሰጥቶት ፡ ከዚህ ፡ ቦታ ፡ እንዲገኝ ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

መጀመሪያ ፤ ፫ ለቀኛዝማች ፡ ወርቂ ፡ የአውሮፕላን ፡ እርዳታ ፡ ተደርጎላቸው ፡ ቋራ ፡ ከተለቀቀ ፡ በኋላ ፡ በቶሎ ፡ ከማጠቢያ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የኢጣልያን ፡ ጦር ፡ አስለቅቆ ፡ እፋቂ ፡ ማረጃ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ ባቅራቢያው ፡ ወታደር ፡ ማድረግና ፡ ከገለባት ፡ እስከ ፡ ሰራቆ ፡ መንገዱን ፡ ማስጠበቅ ፡ ያስፈልጋል ።

ሁለተኛ ፤ በጉባ ፡ ገለባት ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ የኢጣልያን ፡ ጦር ፡ እንዳይመላለስ ፡ ማገድ ፤ ከጭልጋ ፡ ወደ ፡ መተማ ፡ እንዳይወርድ ፡ መከልከል ፤ በአለፋና ፡ በጣቁሳም ፡ እንዳይወርድ ፡ መከልከል ፡ ያስፈልጋል ፡ እና ፡ አንድ ፡ የሚገፋፋቸው ፡ ሰው ፡ በመሐከላቸው ፡ ካልተገኘ ፡ ይኸንን ፡ ሥራ ፡ ቀኛዝማች ፡ ወርቂና ፡ ልጅ ፡ ወንድማገኘሁ ፡ ግራዝማች ፡ ረዳ ፡ ለብቻቸው ፡ አያይዘው ፡ ይሠራሉ ፡ ብዬ ፡ ሙሉ ፡ እምነት ፡ አላደርግም ፡ ስለዚህ ፡ ለጊዜው ፡ በሐሳቤ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ለኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድም ፡

---

፩ ልጅ ፡ ወንድማገኘሁ ፡ ስጥ ፡ አርገው ፤ በቤጌምድር ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ በማሕበረ ፡ ሥላሴ ፡ አቅራቢያ ፡ ቻባ ፡ በተባለ ፡ ቀበሌ ፡ ይገኝ ፡ የነበረ ፡ አርበኛ ፡ ነው ፡ ታማኝና ፡ ቅንነትም ፡ የነበረው ፡ መሆኑን ፡ በማወቅ ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ ቀዳሚ ፡ ሆኖ ፡ ለሚገባው ፡ መላከተኛ ፡ ጦር ፡ መንገድ ፡ መርቶ ፡ እንዲአሳልፍ ፡ ከአገሩ ፡ ወደ ፡ ሱዳን ፡ ተጠርቶ ፡ ከገዳሪፍ ፡ እስከ ፡ ሠራቆ ፡ በታማኝነትና ፡ በቅን ፡ ተግባሩን ፡ ፈጽሞ ፡ ሰራቆ ፡ ኢተባለው ፡ ቋራ ፡ ግዛት ፡ አድርሶ ፡ ከቀኛዝማች ፡ ወርቂ ፡ ስንቂ ፡ ጋር ፡ ያገናኘን ፡ ታማኝና ፡ ቅን ፡ አርበኛ ፡ የነበረ ፡ ሰው ፡ ነው ።

፪ ግራዝማች ፡ ረዳ ፡ ተሰማ ፤ የጭልጋ ፡ ባላባት ፡ የሆኑ ፡ የታመኑ ፡ አርበኛ ፡ የነበሩ ፡ ሰው ፡ ናቸው ። ቀዳሚ ፡ መላከተኛ ፡ ሆነን ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ በገባንበት ፡ ጊዜ ፡ ከጭልጋ ፡ ወደ ፡ ሱዳን ፡ ተጠርተው ፡ በቅንነትና ፡ በታማኝነት ፡ ከሱዳን ፡ እስከ ፡ ማኅበረ ፡ ሥላሴ ፡ ድረስ ፡ ከጠላት ፡ አደጋ ፡ ለማዳን ፡ የሚአስችለውን ፡ መንገድ ፡ በመምራት ፡ የአገለገሉ ፡ በአገራቸውም ፡ ውስጥ ፡ በነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ በውስጣቸው ፡ የነበረው ፡ አርበኛ ፡ ተሰብስቦ ፡ ደጃዝማች ፡ ብለንዎታል ፡ ብሎ ፡ እንደሌላው ፡ አርበኛ ፡ ሁሉ ፡ ቢሾማቸው ፡ ንጉሡ ፡ ተሰደው ፡ ነጋሪቱ ፡ ተደፍቶ ፡ ባንዲራው ፡ ታጥፎ ፡ ደጃዝማችነት ፡ አልቀበልም ፡ ብለው ፡ ቀድሞ ፡ ጠላት ፡ ከመግባቱ ፡ በፊት ፡ ተሾመው ፡ የነበረውን ፡ ግራዝማችነት ፡ አጽንተው ፡ የቆዩ ፡ ታማኝ ፡ አርበኛ ፡ ናቸው ። ጠላት ፡ ከተባረረ ፡ በኋላ ፡ የፊታውራሪነት ፡ ማዕረግ ፡ አግኝተዋል ።

፫ ቀኛዝማች ፡ ወርቂ ፡ ስንቂ ፡ (ፊታውራሪ) ፡ በቋራ ፡ ግዛት ፡ የነበረ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ አርበኛ ፡ ነው ። ከጐጃም ፡ ወደ ፡ ሱዳን ፡ ከሱዳን ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነጻነት ፡ በመላላክ ፡ ከግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ለአርበኞች ፡ ከአርበኞች ፡ ለግርማዊነታቸው ፡ መልእክት ፡ ይላላኩ ፡ የነበሩትን ፡ ሰዎች ፡ ችግር ፡ እንዳይደርስባቸው ፡ በመርዳት ፡ ያስተላልፍ ፡ የነበረ ፡ ቅንና ፡ ታማኝ ፡ አገልጋይ ፡ ነው ።



እማክሬያቸው ፡ መልካም ፡ እኔም ፡ እጽፋለሁ ፡ ያሉኝ ፡ የሻለቃ ፡ መስፍን ፡ ስለሺን ፡ ነውና ፡ ከግርማዊነትዎም ፡ እንዳይርቅና ፡ በተፈለገ ፡ ጊዜም ፡ በቶሎ ፡ እንዲደርስ ፡ ተደርጎ ፡ የግርማዊነትዎ ፡ ማኅተም ፡ ተሰጥቶት ፡ በቶሎ ፡ ወደዚህ ፡ እንዲላክ ፡ አመለክታለሁ ።

የሻለቃ ፡ መስፍን ፡ ስለሺ ፡ ከዚህ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ሲገኝ ፡ የአለፋና ፡ የጣቁሳ ፡ የጭልጋም ፡ ባንዳዎች ፡ አሁን ፡ ላሉት ፡ አርበኞች ፡ እምነው ፡ ይገቡ ፡ አይመስለኝምና ፡ ወደርሱ ፡ እንዲሚገቡለት ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ።

የአለፋና ፡ የጣቁሳ ፡ ሕዝብ ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ብቻ ፡ ካሉለት ፡ ከኢጣሊያን ፡ ሳይከዳ ፡ አይቀርም ፡ ማለትን ፡ ሰምቼአለሁና ፡ ከአቻፈርም ፡ የደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ስብከት ፡ እንዲሰማቸው ፡ ለማድረግ ፡ አስበናል ።

የቀኛዝማች ፡ ወርቂን ፤ የልጅ ፡ ወንድማገኘሁንና ፡ የግራዝማች ፡ ረዳን ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ ተማምነን ፡ ድንገት ፡ በቀኛዝማች ፡ ወርቂና ፡ በልጅ ፡ ወንድማገኘሁ ፡ በግራዝማች ፡ ረዳና ፡ በሌሎችም ፡ መሐከል ፡ የመፎካከር ፡ መንፈስ ፡ ተፈጥሮ ፡ ይህ ፡ መንገድ ፡ ሳይጠበቅ ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ኋላ ፡ ጸጸት ፡ እንዳይሆንብን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ተልኮ ፡ በቶሎ ፡ በመሐከላቸው ፡ እንዲገኝ ፡ አስፈላጊነቱን ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ አመለክታለሁ ፤

እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ያየሁት ፡ የኢትዮጵያ ፡ አርበኛና ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ የግርማዊነትዎን ፡ በቶሎ ፡ መምጣት ፡ በጣም ፡ ይናፍቃል ። ነገር ፡ ግን ፡ እጐጃም ፡ እስክንደርስ ፡ ድረስ ፡ የግርማዊነትዎን ፡ መምጫ ፡ ጊዜና ፡ መንገድ ፡ ወስኜ ፡ ለመናገር ፡ አልችልም ፤

በሰያ ፡ ላይ ፡ መልካም ፡ የሆነ ፡ የአውሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡ የሚሆን ፡ ሜዳ ፡ አለ ፤ መባሉን ፡ ሰምቼአለሁና ፡ ከኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ጋራ ፡ እንደተነጋገርነው ፡ ካርቱን ፡ ከሩሽሊ ፡ ሄደው ፡ የበላያን ፡ አኳኋን ፡ አይተው ፡ ለአውሮፕላን ፡ ይሆናል ፡ ካሉን ፡ የግርማዊነትዎ ፡ መምጣት ፡ በአውሮፕላን ፡ ቢሆን ፡ መልካም ፡ ይመስለኛልና ፡ አስቀድሞ ፡ እንዲታሰብበት ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ አሳስባለሁ ፤ ዳግም ፡ ቋራ ፡ ከተለቀቀ ፡ ጥንት ፡ ነጋዴ ፡ ይመላለስበት ፡ የነበረ ፡ መንገድ ፡ ከመተማ ፡ እንስቶ ፡ ቋራን ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ትቶ ፡ ቴምሃ ፡ ድረስ ፡ ግመል ፡ የሚያስኬድና ፡ የማያሰጋ ፡ መንገድ ፡ አለ ፡ ብለው ፡ ቀኛዝማች ፡ ወርቂ ፡ ነግረውኛልና ፡ ስለርሱም ፡ ወደፊት ፡ እንመረምራለን ።

ከግርማዊነትዎ ፡ መምጣት ፡ በፊት ፡ ብዙ ፡ ሺህ ፡ ወታደር ፡ ማደራጀት ፡ ያስፈልገናል ። ስለዚህ ፡ በሱዳን ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ ዘንድ ፡ ከሚሰናዳው ፡ ወታደር ፡ ሌላ ፡ ከጐጃም ፡ ስንደርስ ፡ የተቻለ ፡ እንደሆነ ፡ ባዲስ ፡ ሥልጣኔ ፡ ወታደር ፡ ማዘጋጀት ፡ ያስፈልገናልና ፡ አንድ ፡ የወታደር ፡

ትምህርት ፡ የተማረ ፡ ሰው ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ ዘንድ ፡ ቢገኝ ፡ በቶሎ ፡ አለንበት ፡ ድረስ ፡ ቢላክ ፡ መልካም ፡ ነው ።

ባርማጭሆ ፡ ያለውን ፡ የሕዝብ ፡ አኳኋን ፡ አገሩም ፡ ውስጥ ፡ ባል ገባ ፡ ባቅራቢያው ፡ በማለፌ ፡ እንደሰማሁትና ፡ ከያንዳንዱም ፡ ሰው ፡ እንዳገኘሁት ፡ አርበኞቹ ፡ ሁሉ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ እኔ ፡ ለእከሌ ፡ አልታ ጠቅም ፡ እኔ ፡ ለእከሌ ፡ አልታጠቅም ፡ በመባባል ፡ በየትንንሹ ፡ ምክንያት፡ ትልቁ ፡ ሥራ ፡ የሚበላሽ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ እንደሚሻል ፡ ብጠይቅ ፡ አንድ ፡ የሚፈራ ፡ ዳኛ ፡ ማለት ፡ የበላይ ፡ ገዢ ፡ ካልተደረገ ፡ ምንጊዜም ፡ ቢሆን ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ስምምነት ፡ አግኝተው ፡ ጠላትን ፡ ለማጥቃት ፡ አይችሉምና ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ አጠገብ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ ካልተላከ ፡ አይሆንም ፡ ማለትን ፡ አብረን ፡ የምንኖርባቸው ፡ ጭምር ፡ ስለሰማን ፡ ለዚህ ፡ ምን ፡ ማድረግ፡ ይሻላል ፡ ብለው ፡ ሐሳቤን፡ ቢጠይቁኝ ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለውን ፡ አመልክቻቸው ፡ ይደረጋል ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ ጀኔራሉ ፡ እጽፋለሁ ፡ እንተም ፡ ለጃንሆይ ፡ ጻፉ ፡ ብለውኛልና ፡ ነገሩ ፡ አስቀድሞ ፡ ታውቆ ፡ እንዲታሰብበት ፡ ስል ፡ አመለክታለሁ ።



ፊታውራሪ ፡ ብሩ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ (ራስ) ።

የነገርኋቸውም ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፤

አሁን ፡ እንዳየሁት ፡ ገንዘብም ፡ መሣሪያም ፡ የሚሰጡት ፡ የእንግ ሊዝ ፡ የጦር ፡ ሹማምንቶች ፡ ብቻቸውን ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ በየበኩሉ ፡ የተ በታተነ ፡ ጦር ፡ ሆኖ ፡ አውራ ፡ ያጣ ፡ ሆነ ፤ አሁን ፡ ግን ፡ ምክር ፡ ከጠየ ቁኝ ፡ ፊታውራሪ ፡ ብሩ ፡ ዶካም ፡ ቢሆን ፡ ገዳሪፍ ፡ ተቀምጠው ፡ ካገሩ ፡ ሕዝብ ፡ እየተላላኩ ፡ ሲመጣም ፡ በፈቃዳቸው ፡ የሚያዙበት ፡ መሣሪያና ፡ ገንዘብ ፡ ተሰጥቶ ፡ ሰው ፡ ሲሰበሰብላቸው ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ቢገቡ ፡ ለየብ ቻው ፡ የተበታተነው ፡ ሁሉ ፡ የርሳቸው ፡ ታዛዥ ፡ መሆን ፡ ይችላል ፤



እርሳቸውም ፡ በፈቃዳቸው ፡ የሚሰጡት ፡ የሚበቃ ፡ ገንዘብና ፡ መሣሪያ ፡ ካገኙ ፡ ሰውም ፡ ይሰማቸዋል ፡ ለመሥራት ፡ ይችላሉ ፤ አሁን ፡ በጭልጋ ፡ ላይ ፡ አስቸግሮ ፡ ያለውም ፡ የቅማንት ፡ ባንዳ፡ በቀላሉ፡ ተሰብስቦ፡ ኢጣል ያንን ፡ እንዲከዳ ፡ ሊደረግ ፡ ይቻላል ። እንደሚመስለኝ ፡ የመተማም ፡ በር ፡ በፍጥነት ፡ ሊከፈት ፡ ይቻላል ፤ ግርማዊም ፡ ባሰቡት ፡ በኩል ፡ ለመ ሄድ ፡ መንገዱ ፡ በቀላል ፡ ይከፈታል ፡ ብዬ ፡ ሐሳቤን ፡ ስለነገርኋቸው ፡ በሐሳቡ ፡ ተስማምተናልና ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ በቶሎ ፡ ቢፈጸም ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ስል ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ አመለክታለሁ ።

ሥራው ፡ ትልቅ ፡ ስለሆነ ፡ ምክትል ፡ ሠራተኛ ፡ ሆኖ ፡ ከሳቸው ፡ ጋራ ፡ የሚሠራ ፡ የሚበቃ ፡ ፕሮግራም ፡ (ማስታወሻ) ፡ ተሰጥቶት ፡ ልጅ ፡ አንዳርጋቸው ፡ ቢሆን ፡ የተሻለ ፤ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፤



ልጅ ፡ አንዳርጋቸው ፡ መሳይ ፡ (ራስ) ፡

የጊዜው ፡ ሕዝብ ፡ በፈቃዱ ፡ አዳሪ ፡ ጭምር ፡ ስለሆነ ፡ እንደጊ ዜው ፡ እንዲሠራ ፡ ለፊታውራሪ ፡ ብሩ ፡ በተለየ ፡ ትእዛዝና ፡ ምክር ፡ እንዲ ሰጣቸው ፡ አስታውሳለሁ ፤ የሚቻልም ፡ ቢሆን ፡ ደጃዝማች ፡ አምዴ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ እንዲሆኑ ፡ ማሰብ ፡ መልካም ፡ ይመስለኛል ። ይኸን ንም ፡ ማሰቤ ፡ እፊታውራሪ ፡ ብሩ ፡ ዘንድ ፡ የሌለው ፡ እደጃዝማች ፡ አምዴ ፡ ዘንድ ፡ ይገኛል ፤ እደጃዝማች ፡ አምዴ ፡ ዘንድ ፡ የሌለው ፡ እፊታውራሪ ፡ ብሩ ፡ ዘንድ ፡ ሞልቷል ።

## በመንገድ ፡ የሰማነው ፡ ወሬ ።

ሐምሌ ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ የሻለቃ ፡ መስፍን ፡ ስለሺ ፡ ኩብዙ ፡ መቶ ፡ የደ ጃዝማች ፡ መንገሻና ፡ የደጃዝማች፡ ነጋሽ፡ ሰዎች ፡ ጋራ፡ የራሱም፡ ጭምር፡ ብዙ ፡ አጋሥስና ፡ አህያ ፡ እያስነዳ ፡ ወደ ፡ ሱዳን ፡ አገር ፡ ሲወርድ ፡ ሩቂ ፡ ማረኛ ፡ አጠገብ ፡ ግራዊት ፡ በምትባለው ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ የኢጣልያን ፡ ጦር ፡ አደጋ ፡ ጥሎበት ፡ ብዙ ፡ ኩብትና ፡ ሰው ፡ የተበታተነበትን ፡ ሰማን ፡

እርሱም ፡ ተመልሶ ፡ በጫቆ ፡ በኩል ፡ መውረዱን ፡ ሰማን ፤ የጐጃም ፡
ሰው ፡ ብረት ፡ ለመቀበል ፡ ነበርና ፡ የመጣው ፡ የሚበልጠው ፡ ጀሌ ፡ ስለ
ነበረ ፡ ብረት ፡ የያዙት ፡ ከአርባ ፡ አይበልጡም ፡ ነበር፡ አሉን ፤ ስለዚህ፡
ምንም ፡ እንኳን ፡ ብረት ፡ ይዘው ፡ የነበሩቱ ፡ ደህና ፡ አድርገው ፡ ቢዋጉ ፡
ጀሌውና ፡ ከብቱ ፡ ስለተበታተነ ፡ እንደገና ፡ መንገድ ፡ ለውጠው ፡ ወደ ፡
ሱዳን ፡ ሲወርዱ፡ ከአራት፡ መቶ ፡ አይበልጡም፡ ነበር ፡ ይባላል ። የሚበል
ጠው ፡ ወዳገሩ ፡ ተመልሶ ፡ ገባ ። ጥቂቶች ፡ በሕመም ፡ ምክንያት ፡ የቀሩ ፡
ቻባ ፡ ላይ ፡ አሉ ፡ ይባላል ። እነርሱም ፡ ወደኛ ፡ እንዲመጡ ፡ ለልጅ ፡
ወንድማገኘሁ ፡ ነግረናል ። አሥሩን ፡ ሰዎች ፡ እሰራቆ ፡ ላይ ፡ አገኘናቸው ፤
ከነርሱም ፡ አንዱ ፡ ሥዩም ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ የሚባለው ፡ እጦርነቱ ፡
ላይ ፡ እግሩን ፡ ቆስሎ ፡ ተኝቷል ። እርሱም ፡ የሻለቃ ፡ መስፍን ፡ ሰው ፡
ነው ። የደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ እንደራሴ ፡ ሆኖ ፡ ተልኮ ፡ የነበረው ፡ በጅሮ
ንድ ፡ በዛብህ ፡ የሚባለው ፡ ታሞ ፡ ስለቀረና ፡ እዚህ ፡ ሆኜ ፡ በችጋር ፡
እጎዳለሁና ፡ አብሬያችሁ ፡ ልሂድ ፡ ስላለን ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ተነስቷል ፤

እነ ፡ የሻለቃ ፡ መስፍን ፡ ስለሺ ፡ ገና ፡ ከጐጃም ፡ ሲነሱ ፡ ኢጣል
ያን ፡ ሰምቶ ፡ አስቀድሞ ፡ ተጠባብቋቸው ፡ ይሆናል ፡ ብለን ፡ የምንጠረጥ
ረው ፡ በጐጃም ፡ ላይ ፡ በአውሮፕላን ፡ የተበተኑላቸውን ፡ ወረቀት ፡ ስላ
የን ፡ ነው ። ወረቀቱ ፡ የተጻፈው ፡ ሰኔ ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ነው ። እነርሱ ፡ አባ
ይን ፡ የተሻገሩት ፡ ሐምሌ ፡ ፰ ፡ ቀን ፡ ነው ፡ ወረቀቱ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡
ተልኳል ።

እነ ፡ የሻለቃ ፡ መስፍን ፡ ስለሺ ፡ ሲመለሱ ፡ ተከታትሏቸው ፡ የተመ
ለሰው ፡ የኢጣልያን ፡ ጦር ፡ ድንገት ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ከነ ፡ ባሻ ፡ ተሾመ ፡
ጋራ ፡ ተገናኝተው ፡ ተታኩሰውን ፡ ሰማን ፤ ባሻ ፡ ተሾመ ፡ ከኩራፕሩብ ፡
ሲነሱ ፡ አሥር ፡ እራሱን ፡ ነበር ፤ ፫ቱ ፡ ሸሽተው ፡ ወደ ፡ ሱዳን ፡ አገር ፡
ሲገቡ ፡ ባሻ ፡ ተሾመ ፡ ሁለት ፡ ራሱን ፡ አገሩ ፡ ሲገባ ፡ የቀሩት ፡ የሄዱ
በት ፡ አይታወቅም ፤ ባሻ ፡ ተሾመ ፡ ሲወጣ ፡ አሥር ፡ ዲሞትሮርና ፡
አንድ ፡ ጭነት ፡ ጥይት ፡ ለቀኛዝማች ፡ ወርቁ ፡ አድርስ ፡ ተብሎ ፡ ተሰጥ
ቶት ፡ ነበር ፤ ጥይቱ ፡ እንደተጫነ ፡ ተማርኳል ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ኢጣልያን ፡
በአውሮፕላን ፡ እቋራ ፡ ላይ ፡ የበተነው ፡ ወረቀት ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ተልኳል።

ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ አቦዬ ፡ እጐጃም ፡ መሬት ፡ እነሴ ፡ የሚባለው ፡
አገር ፡ መጥተዋልን ፡ ስለሰማን ፡ ተጽፎላቸው ፡ ባቶ ፡ አማኑኤል ፡ መን
ገሻ ፡ እጅ ፡ የተላከላቸው ፡ የግርማዊነትዎ ፡ ደብዳቤ ፡ ድንገት ፡ ቶሎ ፡
አይደርሳቸው ፡ ይሆናልና ፤ የርሱኑ ፡ ዓይነት ፡ ደብዳቤ ፡ በመጀመሪያ ፡
ከሚመጣው ፡ መልክተኛ ፡ ጋራ ፡ ቢላክልን ፡ መልካም ፡ ነው ።

ቀኛዝማች ፡ ይማም ፡ ተሰማ ፡ ሞተዋልን ፡ ሰምተናል ፤ ነገር ፡ ግን ፡
ያማሞታቸውን ፡ እኳ᎓ን ፡ አጣርተን ፡ አላገኘነውምና ፡ ምናልባት ፡



ግርማዊነትዎ ፡ ከሻለቃ ፡ መስፍን ፡ ስለሺ ፡ ያገኙት ፡ ይሆናል ፤ የልጅ ፡
ዮሐንስም ፡ እኳኋን ፡ እንደዚሁ ፤

ሰራቆ ፡ ስንደርስ ፡ አራት ፡ በቅሎች ፡ ስለሞቱብንና ፡ ያሉትም ፡
ስለደከሙ ፡ ወደፊት ፡ የቀረንም ፡ መንገድ ፡ ረጅም ፡ ስለሆነ ፤ ከእንግ
ዶቹ ፡ ኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድና ፡ ካፒቴን ፡ ክሩሽሊ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ሲሄዱ ፡
የቀሩት ፡ ከልጅ ፡ መርዕድ ፡ መንገሻ ፡ ጋራ ፡ የሚበልጠውን ፡ ጓዝ ፡ ይዘው፡
እቀኛዝማች ፡ ወርቁ ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ቀርተዋል ፤ ይኸውም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡
በመንገድ ፡ ላይ ፡ የምናጠፋ ፡ ስለሆነ ፡ አቾፌር ፡ ደርሰን ፡ ሰውና ፡ ከብት ፡
ብንልክላቸው ፡ ይሻላል ፡ ብለን ፡ ነው ፤

ካፒቴን ፡ ክሩሽሊና ፡ ልጅ ፡ መርዕድ ፡ መንገሻ ፡ ቋራ ፡ ሄደው ፡
የምሽጉን ፡ እኳኋን ፡ አይተው ፡ ከተመለሱ ፡ በኋላ ፡ ልጅ ፡ መርዕድ ፡
ስለምሽጉ ፡ እኳኋን ፡ የጻፈው ፡ ማመልከቻ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ተልኳል ።

ነሐሴ ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፪ ፡ ዓ ፡ ም

ሰራቆ ፡ (ኰንታ)

ከበደ ፡ ተሰማ ፤

## ስለ ፡ ጉሙዝ ፡ አሁን ፡ በማጠቢያ ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ሻንቅሎች ፡ (ሕዝብ) ፡ እኳኋን ፡ እንደሰማሁት ።

ኢጣልያ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከመግባቱ ፡ በፊት ፡ ከመተማ ፡ አን
ስቶ ፡ እስከ ፡ ቻባ ፡ ወይም ፡ ሰራቆ ፡ ድረስ ፡ ያለው ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ሰም ፡
ነበር ፤ ሻሽጌ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ መቶ ፤ እምቡልቡል ፡ ላይ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡
ጃቢት ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ መቶ ፤ መረው ፡ ደባ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሃምሳ ፡
ኩኪት ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ የሚሆኑ ፡ ጉሙዞች ፡ ነበሩ ፤ ኢጣልያ ፡
ከገባ ፡ በኋላ ፡ ካሣ ፡ ዘለቀና ፡ ታከለ ፡ ጥሩነህ ፡ የሚባሉ ፡ የጫቆ ፡ ሰዎች ፡
አሥራ ፡ ሁለት ፡ ራሳቸውን ፡ ሆነው ፡ የብዙ ፡ ጉሙዞች ፡ ከብት ፡ ነድ
ተው ፡ ሄዱ ፤ ዳግም ፡ አበበ ፡ ወንዴ ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ እንደዚሁ ፡ ከጫቆ ፡
ወርዶ ፡ ማር ፡ ካላመጣችሁ ፡ እያለ ፡ ብዙ ፡ ጉሙዞችን ፡ አስሮ ፡ ወሰዳ
ቸው ፤ በ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በመጋቢት ፡ ወር ፡ ደግሞ ፡ ኪዳ ፡ ቦጋለ ፡
የሚባል ፡ አሁንም ፡ የጫቆ ፡ ሰው ፡ እምሳ ፡ የሚሆኑትን ፡ እየነዳ ፡ ወሰዳ
ቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ለኢጣልያን ፡ ገብተው ፡ ብረት ፡ ተቀበሉ ፤ ተቀብ
ለውም ፡ ችቻ ፡ በምትባለው ፡ ባንዲት ፡ በጫቆ ፡ መንደር ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡
ጥለው ፡ ፳፯ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ሕፃናት ፡ ገደሉ ። ሼክ ፡ መድኔ ፡ እንዳጥ ፡
የሚባለው ፡ ሹማቸው ፡ ከኢጣልያን ፡ ሸሽቶ ፡ ወደ ፡ ሱዳን ፡ አገር ፡ ገብቶ ፡
ኩቴና ፡ በምትባለው ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ቤት ፡ ሠርቶ ፡ ይቀመጥ ፡ ነበር ፤ አሁን ፡



ሻለቃ ፡ መስፍን ፡ ስለሺ ፡ (ራስ) ፡

ግን ፡ ተመልሶ ፡ ለኢጣልያን ፡ ገብቷል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ለኢጣልያን ፡ ዋና ፡ መንገዱን ፡ የሚጠብቁለትና ፡ የሚስልሉለት ፡ እነርሱ ፡ ሆኑ ፤

እነርሱ ፡ ከኢጣልያን ፡ ጋራ ፡ የሆኑበት ፡ ምክንያት ፡ ኢጣልያንን ፡ ወደው ፡ አይደለምን ፡ ስለሰማሁ ፡ የሚጠብቃቸው ፡ ካገኙ ፡ ከድተው ፡ ወደኛ ፡ ይሆናሉ ፡ ብዬ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ።

ለግርማዊነትዎ ፡ እንዳመለከትኩት ፡ የሻለቃ ፡ መስፍን ፡ ስለሺ ፡ ወደዚህ ፡ የሚመጣ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ታሪካቸው ፡ ሳይጠቅም ፡ አይቀርም ። ነሐሴ ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡





ሌ/ጄኔራል ፡ መርዕድ ፡ መንገሻ ።

## የልጅ ፡ መርዕድ ፡ መንገሻ ፡ ደብዳቤዎች ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ፤
ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ
ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፤

መድኃኒ ፡ ዓለም ፡ ዕድሜ ፡ ከጤና ፡ ጋራ ፡ ይስጥልኝ ፡ እያልኩ ፡ እተከበረ ፡ ዙፋንዎ ፡ ሥር ፡ ወድቄ ፡ መሬት ፡ እስማለሁ ።

እኛም ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ሐዘን ፡ በሥላሴ ፡ ቸርነት ፡ ምንም ፡ ዱሩና ፡ ጫካው ፡ ዳገቱና ፡ ቁልቁለቱ ፡ ድረት ፡ መሻገሩ ፡ ቢያጉላላን ፡ ያላንድ ፡ አደጋ ፡ ከሱዳን ፡ ወሰን ፡ አልፈን ፡ አገራችን ፡ እስምለም ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንደኛው ፡ ክፍል ፡ ሠራቅ ፡ ደረስን ፤ በየደረስንበትም ፡ አገር ፡ ባለንበት ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ ከማጣታቸው ፡ በተቀር ፡ በደስታ ፡ እየተቀበሉ ፡ ይሸኙናል ። ሰራቅ ፡ ከደረስንም ፡ በኋላ ፡ ከእንግዶቻችን ፡ አንዱ ፡ ጋራ ፡ በቋራ ፡ ያለ ውን ፡ የምሽግ ፡ አኳኋን ፡ ለማየት ፡ ሄደን ፡ ነበር ። ከዚያም ፡ በተቻለኝ ፡ ያየሁትንና ፡ የሰማሁትን ፡ ራፖር ፡ ጽፌ ፡ ባዛኘ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡ በኩል ፡ አስተላልፌያለሁ ። ለወደፊቱም ፡ በተቻለኝ ፡ አቅሜ ፡ ሕይወቴ ፡ እስካ ለፈ ፡ ድረስ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ክብር ፡ ለሐገሬና ፡ ለነፃነቴ ፡ በታማኝነት ፡ በደስታ ፡ ለማገልገል ፡ ዝግጁ ፡ ነኝ ። እንግዲህ ፡ ለቸርነቱ ፡ ወሰን ፡ የሌ ለው ፡ አምላክ ፡ እርዳታውን ፡ ከኢትዮጵያና ፡ ካርበኞቿም ፡ ጋራ ፡ አድ ርጎ ፡ ግርማዊነትዎንና ፡ ግርማዊት ፡ እቴጌን ፡ ከነቤተ ፡ ዘመዶችዎ ፡ በሕ ይወት ፡ ጠብቆ ፡ በለምለም ፡ አገርዎ ፡ ግርማዊነትዎን ፡ በቶሎ ፡ እንዳይ ፡ ለጸሎቴና ፡ ለሐዘኔ ፡ ለተስፋዬም ፡ ወሰን ፡ የለውም ።

እግዚአብሔር ፡ ከግርማዊነትዎና ፡ ከግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ከልጆ ችዎ ፡ ጋራ ፡ ይሁን ።

እግዚአብሔር ፡ በግፍ ፡ የተጠቃችውን ፡ ኢትዮጵያን ፡ በነፃነቷ ፡ መልሶ ፡ በዱር ፡ በገደል ፡ በጦር ፡ ሥቃይ ፡ ላይ ፡ ያሉትንም ፡ የኢትዮጵ ያን ፡ አርበኞች ፡ በሕይወት ፡ ጠብቆና ፡ አበርትቶ ፡ የሰላም ፡ ጊዜ ፡ ያው ርድ ።

ነሐሴ ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፪ ፡ ዓ ፡ ም

ታዛኘ ፡ አገልጋይዎ ፤
መርዕድ ፡ መንገሻ ።

## ስለ ፡ ቋራ ፡ ምሽግ ፡ አኳኋን ፡ ማመልከቻ ።

ነሐሴ ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ካፒቴን ፡ ክሪችሊይ ፡ ከሚባ ሉት ፡ ከእንግዶቻችን ፡ አንዱ ፡ ጋራ ፡ በቋራ ፡ ያለውን ፡ የጠላት ፡ ምሽግ ፡ አኳኋን ፡ ለማየት ፡ ሄደን ፡ ያየሁትና ፡ የሰማሁት ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ፤

፩ኛ/ ስለ ፡ ምሽጉ ፡ አኳኋን ፤ ነሐሴ ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ቋራ ፡ ደርሰን ፡ ነሐሴ ፡ ፲፱ ፡ እሁድ ፡ ለት ፡ በምሽጉ ፡ ዙሪያ ፡ በምሥራቅና ፡ በሰሜን ፡ ዞረን ፡ ከመረመርን ፡ በኋላ ፡ ከምሽጉ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ምሽጉን ፡ በግ ልጽ ፡ የሚያሳይ ፡ ሥፍራ ፡ አለ ፡ ብለው ፡ ስለወሰዱን ፡ ጉንደና ፡ ማር



ያም ፡ ከምትባለው ፡ ደብር ፡ ሥር ፡ ዝም ፡ ብለን ፡ ፩ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ርቀት ፡ ያለው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ሆነን ፡ ባይኔ ፡ እንዳየሁት ፤ ምሽጉ ፡ ያለበት ፡ ሥፍራ ፡ ሳሊያ ፡ በሚባል ፡ ወንዝ ፡ ላይ ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ ወንዝ ፡ በበጋ ፡ አይደርቅም ፡ ሠፈሩም ፡ እሁለት ፡ ተከፍሎ ፡ ከወንዝ ፡ ወዲያና ፡ ከወንዝ ፡ ወዲህ ፡ ነው ፤ ምሽጉ ፡ ያለበትም ፡ ምንም ፡ ከፍታነት ፡ ያለው ፡ ቦታ ፡ አይደለም ፤ ስለሆነ ፡ ግን ፡ ቋራ ፡ ሞላውን ፡ ዱር ፡ ስለሆነ ፡ ምሽጉ ፡ ያለበ ትን ፡ ቦታ ፡ ብቻ ፡ አስመንጥሮት ፡ በምሽጉ ፡ ውስጥ ፡ ጥቅጥቅ ፡ ብሎ ፡ የተሠራው ፡ የሣር ፡ ክዳን ፡ ቤት ፡ ለብቻ ፡ በዱር ፡ ተከቦ ፡ ቁልጭ ፡ ብሎ ፡ ይታያል ፤ በምሽጉ ፡ ውስጥም ፡ እመሐል ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ወርካ ፡ አለ ፤ ዕቃ ፡ የሚያድስበት ፡ አንድ ፡ ቆርቆሮ ፡ ቤት ፡ አለ ፡ አሉ ፡ እሱም ፡ ቅጠል ፡ ስላለበሱት ፡ አይታይም ፤ አንድ ፡ ትልቅ ፡ የሣር ፡ ክዳን ፡ ሰቀላ ፡ ቤት ፡ አለ ፤ እሱ ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ነው ፡ አሉ ። እምሽጉ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ከዚህ ፡ ካንዱ ፡ ቆርቆሮ ፡ በቀር ፡ ሁሉም ፡ የሣር ፡ ክዳን ፡ ቤት ፡ ነው ፡ ቤቱ፡ በጠቅላላ ፡ ከ፪፻፶ ፡ እስከ ፡ ፫፻ ፡ ይሆናል ፤ ከምሽጉ ፡ በስተሰሜን ፡ በማጠ ቢያ ፡ ግምባር ፡ ሲል ፡ ከምሽጉ ፡ ፪ ፡ ማይል ፡ ርቀት ፡ አለው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ በብዙ ፡ ዛፍ ፡ የተከበበ ፡ ፍታ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የሚባል ፡ ደብር ፡ አለ ፡ በደ ቡብ ፡ በኩልም ፡ ጉንደና ፡ ማርያም ፡ የምትባለው ፡ በዛፍ ፡ የተከበበች ፡ ደብር ፡ አለች ፡ በምዕራብ ፡ ደቡብ ፡ በኩልም ፡ ገዶሉን ፡ ታክኮ ፡ ነው ፡ የተመሸገው ፡ ደግሞ ፡ በመላው ፡ ቋራ ፡ ባንድ ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ እንኳ ፡ እንደምሽጉ ፡ እጅብ ፡ ብሎ ፡ የተሠራ ፡ መንደር ፡ ስለሌለ ፡ ይህ ፡ መልካም ፡ ምልክት ፡ ነው ፤

፪ኛ/ እቋራ ፡ ካለው ፡ ምሽግ ፡ ወደ ፡ መተማ ፡ የሚወስደው ፡ ትልቅ ፡ የተጠረገ ፡ መንገድ ፡ አለ ፤ የመንገዱም ፡ አካሄድ ፡ ምሽጉ ፡ ካለበት ፡ ከሳሊያ ፡ ተነስቶ ፡ በዎፍታ ፡ ጊዮርጊስና ፡ በዘረባይና ፡ ጀንግ ፡ የሚባለ ውን ፡ ወንዝ ፡ ተሻግሮ ፡ ገውላ ፡ የሚባለውን ፡ ከዎፍታ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ በስተሰሜን ፡ በኩል ፡ ፫ ፡ ማይል ፡ ርቀት ፡ ያለው ፡ ተራራ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ይተውና ፡ በአምዳዮ ፡ በርና ፡ በበዶላኩሌትና ፡ አደከላውሳን ፡ ሸንፋን ፡ እነዚሁ ፡ ወንዞች ፡ ይሻገርና ፡ በማጠቢያ ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ ጋላባት ፡ የሚወስደው ፡ መንገድ ፡ የሚበቃ ፡ ምልክት ፡ ነው ። መንገዱም ፡ እላይ ፡ ሆኖ ፡ ሳይለይ ፡ አይቀርም ፤

፫ኛ/ ሁለት ፡ ወንዞች ፡ በምሽጉ ፡ በስተ ፡ ሰሜንና ፡ በስተደቡብ ፡ በኩል ፡ አሉ ፤ በስተደቡብ ፡ ያለው ፡ በጉንደና ፡ ማርያም ፡ ከምሽጉ ፡ መሐከል ፡ ገበላ ፡ የሚባል ፡ ወንዝ ፡ ነው ። በስተሰሜን ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ከዎፍታ ፡ ጊዮርጊስና ፡ ከምሽጉ ፡ መሐል ፡ ፈንገጫ ፡ የሚባለው ፡ ወንዝ ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ ወንዝ ፡ ለአውሮፕላን ፡ ይታያል ፡ አሉ ። ምሽጉም ፡ አንድ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ አቀረበ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ነው ።

፬ኛ/ ከቋራ ፡ በስተምዕራብ ፡ በኩል ፡ በኢትዮጵያና ፡ በሱዳን ፡ ወሰን ፡ አጠገብ ፡ እበረሃው ፡ ውስጥ ፡ ለብቻው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነፍስ ፡ ገበያ ፡ የሚባል ፡ ሹል ፡ ተራራ ፡ አለ ፤ ከሱ ፡ ቀጥሎ ፡ የሚገኘውም ፡ የሱዳን ፡ ወሰን ፡ አልሃዘራ ፡ ይባላል ፡ አሉ ፤ በዚያ ፡ በኩል ፡ አኤሮፕላን ፡ ቢመጣ ፡ በቀላሉ ፡ ያንን ፡ ተራራ ፡ ያያል ፡ እንደዚሁም ፡ እዚያ ፡ ከደረሰ ፡ በኋላ ፡ ገውላ ፡ የሚባለውን ፡ ተራራ ፡ ያገኛል ፤ ከዚህ ፡ ዎፍታ ፡ ጊዮርጊስን ፡ ያለችግር ፡ ምሽጉ ፡ ይገኛል ። ከዚሁ ፡ ሁሉ ፡ መጀመሪያ ፡ ቋራ ፡ የት ፡ እንደሆነ ፡ ማወቅ ፡ ነው ፡ እሱ ፡ ከታወቀ ፡ ግን ፡ ምሽጉን ፡ ማግኘት ፡ በጣም ፡ ቀላል ፡ ነው ፤ ሁለቱም ፡ ምሽጉ ፡ በሁለት ፡ የተከበበ ፡ ነው ፡ መጀመሪያ ፡ ከውጭ ፡ ሲመጡ ፡ የሚገኘው ፡ እንጨት ፡ እየገነጠሉ ፡ ጣል ፡ ጣል ፡ አድርገውብታል ፤ የሁለተኛው ፡ ግን ፡ ትልልቅ ፡ ግንድ ፡ እያጣመሩ ፡ ተክለው ፡ በድንጋይና ፡ ባፈር ፡ ከውስጥም ፡ ዙሪያውን ፡ ቆፍረው ፡ መታኰሻ ፡ አበጅተው ፡ ነው ፡ የሠሩት ፡ አሉ ፡ በምሽጉ ፡ ውስጥ ፡ ያላቸው ፡ እህልም ፡ ማሽላና ፡ ስንዴ ፡ ነው ፡ አሉ ፤ እህልና ፡ ጥይታቸውም ፡ የሚቀመጠው ፡ በግር ፡ ክዳን ፡ ቤት ፡ ነው ፤ ቤቱ ፡ ሁሉ ፡ ተቀራርቦ ፡ ስለተሠራ ፡ የሚቃጠያ ፡ ቦምብ ፡ ቢወድቅበት ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ሁሉም ፡ የሚቃጠለው ፤ አንዳንድ ፡ ሰው ፡ እንደሚለው ፡ ይህ ፡ በምሽግ ፡ የተሰበሰበው ፡ እህል ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ያስከብበዋል ፡ ይላሉ ፤ አንዳንዶቹ ፡ ደግሞ ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ እንኳን ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ አንድ ፡ ዓመትም ፡ አያስከብብም ፡ ይላሉ ፤ ማር ፤ ቅቤ ፡ ሻይና ፡ ስኳር ፡ ሽንኩርት ፡ ጨው ፡ ቡና ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ የላቸውም ፡ ነጮች ፡ ብቻ ፡ ጥቂት ፡ ጥቂት ፡ ያገኛሉ ፡ አሉ ፤ ይኸንንም ፡ የሚያወሩት ፡ እዚያው ፡ ለጣላት ፡ ተቀጥረው ፡ ባንድነት ፡ ሲሰሩ ፡ የነበሩ ፡ ናቸው ።

ጠላት ፡ ከምሽጉ ፡ በፍጹም ፡ አይወጣም ፡ ሕዝቡም ፡ ከብቱን ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ በደጁ ፡ ነው ፡ የሚያበላው ፡ በምሽጉ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ወታደሮች ፡ ሐማሴን ፡ ሱማሌ ፡ እስላምና ፡ ከቋራም ፡ ጥቂት ፡ ባንዳዎች ፡ ናቸው ፤ የነኝህም ፡ የወታደሮች ፡ ቁጥር ፡ በጠቅላላው ፡ ከ፫፻ ፡ አይበልጥም ፡ አሉ ፤ እንደምሰማው ፡ የባንዶቹ ፡ ሐሳብ ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ መጥቶ ፡ አንድ ፡ ቦምብ ፡ በምሽጉ ፡ መውደቁን ፡ ካዩ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ይከዳሉ ፡ አሉ ። እውነትም ፡ እንደሚመስለኝ ፡ ሳይከዱ ፡ አይቀሩም ፡ ለምን ፡ የግማሾቹ ፡ ዘመዶች ፡ በውጭ ፡ ናቸውና ፡ እውነተኛውን ፡ ነገር ፡ እነሱ ፡ ሲልኩባቸው ፡ ይወጣሉ ፤ ሐማሴኑና ፡ ባንዳውን ፡ እንደ ፡ ሶማሌውና ፡ እንደ ፡ እስላሙ ፡ አያምነውም ፡ ስለዚህ ፡ የምሽጉን ፡ ዙሪያ ፡ የሚያስጠብቀው ፡ በነዚህ ፡ ታማኙ ፡ በሆኑት ፡ በሁለቱ ፡ ዘሮች ፡ ወታደሮች ፡ ብቻ ፡ ነው ።



## ስለ ፡ ቋራን ፡ ሕዝብ ፡ አኳኋን ።

የቋራ ፡ ሕዝብ ፡ እንደተመለከትኩት ፡ ነፃነቱንና ፡ መንግሥቱን ፡ ይወዳል ፤ አሁን ፡ በቋራ ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፡ በሙሉ ፡ ከቀኛዝማች ፡ ወርቁ ፡ ጋራ ፡ ነው ። ከሳቸው ፡ ጋራ ፡ ያለውንም ፡ የሰራቆ ፡ ወታደር ፡ በመንደሩ ፡ ሲመራ ፡ ባላገሩ ፡ እንደዘመዱ ፡ ነው ፡ የሚቀበለው ። ነገር ፡ ግን ፡ እስከ ሁን ፡ ሕዝቡ ፡ ተስፋ ፡ ያደረገው ፡ ኤሮፕላን ፡ መጥቶ ፡ ምሽጉን ፡ በቦምብ ፡ ይመታልና ፡ ያንጊዜ ፡ አንድም ፡ በምሽጉ ፡ ውስጥ ፡ የሚቆይ ፡ የለምና ፡ ሁሉም ፡ ለሽሽት ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ሲወጣ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አውክተን ፡ ገብተን ፡ እንፈጀው ፡ ነበር ፡ ይላሉ ፤

እኔ ፡ እንደሚመስለኝ ፡ አንድ ፡ ሦስት ፡ አውሮፕላን ፡ ቢመጣ ፡ ለምሽጉ ፡ በቂ ፡ ነው ። የግርማዊ ፡ ጃንሆይን ፡ መምጣትም ፡ በሙሉ ፡ አምኖዋል ። ይህ ፡ የሚፈለገው ፡ አውሮፕላን ፡ መጥቶ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ያንን ፡ ታስለቀቁ ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ ጦር ፡ ያላንገፈገፋቸው ፡ የቋራና ፡ የሠራቆ ፡ አርበኞች ፡ ሌላም ፡ ሥራ ፡ ሳይረዱ ፡ አይቀሩም ፤ ወታደሩም ፡ በሙሉ ፡ ወጣት ፡ ነው ። ካየኋቸው ፡ ከሌሎቹ ፡ አገሮች ፡ ይልቅ ፡ ላለታቸው ፡ ታዛዥነት ፡ ያላቸው ፡ ይመስላሉ ። ከቀኛዝማች ፡ ወርቁም ፡ ጋራ ፡ በጣም ፡ ስምምኞች ፡ ናቸው ። በተረፈ ፡ ይህ ፡ የሚፈልጉት ፡ በቶሎ ፡ ቢፈጸም ፡ መልካም ፡ ነው ። ያለዚያ ፡ ግን ፡ የጠላት ፡ አውሮፕላን ፡ በሦስት ፡ በሦስት ፡ ቀን ፡ እየመጣ ፡ ቦምብ ፡ ስለሚጥልባቸው ፡ ተቀን ፡ ብዛት ፡ ያደክማቸው ፡ ይሆናል ። ሌላውንም ፡ ሥራ ፡ እንዳይሠሩ ፡ ያዘገያል ፤ ወታደሩ ፡ እንኳ ፡ ግዴለውም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ልጅና ፡ ሴት ፡ ከብት ፡ ሁል ጊዜ ፡ ሸሽቶ ፡ አይሆንለትም ፡ አደጋውም ፡ በሴትና ፡ በሽማግሌ ፡ ነው ፡ የሚበረታው ። ስለዚህ ፡ የሚሆንን ፡ ነገር ፡ ጊዜው ፡ ሳያልፍ ፡ ነው ፡ ማድረግ ። ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ መዘግየት ፡ ፍሬ ፡ የለውም ። ሰውን ፡ አለሁ ፡ አለሁ ፡ ሲል ፡ ደገፍ ፡ ደገፍ ፡ ያደረጉት ፡ እንደሆነ ፡ ልቡም ፡ እየጎለመሰ ፡ ይሄዳል ፤ ዘግየት ፡ ያሉበት ፡ እንደሆነ ፡ አይ ፡ ይሄስ ፡ ወሬ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ልቡ ፡ እየደከመ ፡ ይሄዳልና ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ማሰብ ፡ ነው ።

ነሐሴ ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፪ ፡ ዓ ፡ ም<br>መርዕድ ፡ መንገሻ ፡